# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የል ማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅ ርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀ ረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመ ረዳት ይቻላል ።

ይ
ስቲያ
ያን አገልጋ
ከእውነት የራቀ አ
ኅብረተሰብ በሚያርፋ
ሉ ሰዓታት ፣ ማኅሌት በ
በማቅረብ የሞተ ሰው በመ
ረተሰቡን ያገለግሉና በሥራ
መ እንደሌላው ኅብረተሰብ
ሠርተው ራ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

# ትንሣኤ



መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ጠላት ዲያብሎስን ድል እንደመታው ።

www.ethiopianorthodox.org

''ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ ''ትንሣኤ'' ተብሎ ተሰይሚል ።


አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ


# ማውጫ

አርእስት — ገጽ


ደብዳቤዎች .................... ፩
ርእስ አንቀጽ .................... ፬
የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጉብኝት በቅድስት ሀገር
ኢየሩሳሌም .................... ፯
በዐለ ሃምሳ .................... ፰
ቅዱስ ሚካኤልና ተልእኮው .................... ፱
የቅኔ መምህርዋ ወይዘሪት .................... ፲፩
የአብያተ ክርስቲያናት ዜና .................... ፲፬
ወጣቶች .................... ፲፮
የምእመናን ድምፅ .................... ፲፱
ሊቃውንቶቻችን .................... ፳፮
የሃይማኖት ርምድ .................... ፳፰
ምን እንርዳዎ .................... ፳፱
ልማት በቤተ ክርስቲያን .................... ፴፩
የመጽሐፍ ቅዱስ ዐምድ


# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ከሁሉ አስቀድሜ መንፈሳዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ።

እንድ ያልገባኝ ነገር አለ ይኸውም በተለያዩ ቦታዎች ከአዲስ አበባ እስከ ክፍለ ሀገር ከአንዳንድ ደብር ያሉ ታቦቶች የተትረፈረፈ ገቢ ስላላቸው ካህናቱም ቤተ እግዚአብሔሩም በደምብ ተጠብቆ ይኖራል አልባሳቱም የእቃ ቤቱን ማስቀመጫ አጥበው የአይጥና የብል መፈንጫ እንደሆኑ ግልጽ ነው ።

በአንዳንድ አካባቢ ደግሞ በተለይም ወደገጠሩ ወጣ ብለን ስንመለከት የመቀደሻ እጣንና ጧፍ እያጡ ቅዳሴው እንደሚታጐል በአይን ምስክርነት ተመልክቻለሁ ይህም አብያተ ክርስቲያኑ ምንም ገቢ የሌላቸው መሆኑን ያስረረዳል አንዳዱም ቀዳሾቹ ሰሞነኞች ቅዳሴ ሲገቡ እሚለብሱት ልብሰ ተክኖ እያጡ የግል ልብሳቸውን ለብሰው እሚቀድሱት ታድያ አዘጋጅ እንደዚህ ያሉት በችግር የተራቆቱትን አብያተ ክርስቲያናት ቤተ ክርስቲያን የወከለቻቸው ከክርስቶስ የተሰጣቸው አላፊነት ወደኋላ ጣል አርገው መመልከቱ ለምንድነው ።?

2ኛ/ ገቢ ያላቸው የሌላቸውን ለመርዳት የሚከለክል ነገር አለን?እባክዎን መልሱን አስረዱኝ ።

ወ/አማኑኤል ዘለለው
አ.አ

★ አቶ ወ/ አማኑኤል ዘለለው በተቀዳሚ የመጽሔታችን ተከታታይ በመሆን ስላቀረቡልን ጥያቄ እናመሰግናለን ።

በዕርግጥ እርስዎ እንደተናገሩት በከተማም ሆነ በገጠር በካህናትና በንዋየ ቅድሳት የበለጸጉ አብያተ ክርስቲያናት ሲኖሩ በዚያው አንጻር ደግሞ ንዋያተ ቅድሳትና ካህናት የሌሏቸው አብያተ ክርስቲያናት መኖራቸው የተረጋገጠ ነው ። ነገር ግን ያላቸው አብያተ እርስቲያናት ለሌላቸው እንዲያካፍሉ ለማድረግ እጅግ በጣም አስቸጋሪ ነው ።

ምክንያቱም ካህናቱን የሚያስተባብራቸው ስለሌለ የሚኖሩበትን ቤተ ክርስቲያን እንደ ግል ማኅደር አድርገው ስለሚቆጥሩት ነው ፣ ቤተ ክርስቲያን አንዲት መሆኗን ከልብ የሚገነዘቡ ካህናት በቁጥር እጅግ በጣም አነስተኞች ናቸው ።

ስለዚህ በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን አንዲት መሆኗን ለካህናቱ ማስረዳት ያስፈልጋል ፣ ከዚህ በኋላ የቤተ ክርስቲያን ርእስ የሆነው ቅዱስ ሲኖዶስ አንድ አስተባባሪ ኮሚቴ ሰይሞ ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ለሌላቸው እንዲለግሡ ይደረግ ዘንድ የጠያቂውን ፍሬ ነገር በዚሁ መልእክት እናስተላልፋለን።

ገቢ ያላቸውም አብያተ ክርስቲያናት ለሌላቸው አብያተ ክርስቲያናት አይስጡ ወይም አይርዱ የሚል ሕግ ስለሌለ ብዑላን የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በልብስም በካህናትም በመንፈሳውያን ተግባራት ሁሉ ከሌላቸው አብያተ ክርስቲያን ጋር ተባብረው ቢሠሩ መልካም ነው እንላለን ።

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ከዚህ በታች የማቀርበውን ጥያቄ ተመልክተህ እንድትመልስልኝ በታላቅ ትህትና እጠይቃለሁ ። እኔ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ ነኝ የእግዚአብሔር ፍቅር ከልቦናዬ ውስጥ እንደሳት የሚያቃጥለኝ ነኝ የዘወትር ሃሣቤ ከእግዚአብሔር ቤት መለየት አልፈቅድም የአሣቤ ፈጻሚ እሱ ነውና ። በዚሁ በእናንተ አጠገብ በነበረው የማህበረ ሥላሴ የወጣት ተማሪዎች አባል ነበርኩ በአንድ አንድ ሁኔታ አቋርጫለሁ ግን ዘወትር ከቤተ ክርስቲያኑ መድረክ ሣልገኝ አልውልም በዚሁ በእናንተ መ/ቤት ውስጥ እየተዘጋጀ በሚወጣው ጋዜጣ ላይ የመንፈሳዊ ኮሌጅ በ1973 ዓ.ም. ይከፈታል የሚል ዜና እንብቤአለሁ በዚሁ ኮሌጅ ገብቶ ለመማር ፍላጐት አለኝ ነገር ግን እስከ ዛሬ ድረስ በቤተ ክርስቲያናችን አካባቢ ሴቶች ሙሉ ተሳትፎ ሲአደርጉ አላየሁም የነገሩ መንስኤ ይኀ ሲሆን እግዚአብሔር ፈቃዱ ቢሆን ዘንድሮ የ12ኛ ክፍል አጠናቅቄ የብሔራዊን ፈተና ወስጃለሁ በአልፍም በአላልፍም በዚሁ መንፈሳዊ ኮሌጅ ውስጥ ገብቼ ለመማር ሃሳብ አለኝ እንግዲህ ሴቶች በዚሁ ኮሌጅ ውስጥ ገብተው ለመማር ይችሉ እንደሆነ ወይንም የማይችሉ እንደሆነ ከተቻለ ግን የመጀመሪያ ሁኘ እንደም ቀርብ ታውቆ ማናቸውንም ጉዳይ በዓምድህ ላይ ዘርዝረህ እንድታስረዳኝ በማለት ስጠይቅ ለጉዳዩ ግን በጉጉት የምጠባበቅ መሆኔን አሣስባለሁ ።

ወ/ሪት እፀገነት ምናሴ ከዳግማዊ ምኒልክ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት

★ ወ/ት ዕፀ ገነት ምናሴ ለጥያቄሽ መልስ ለማግኘት የኮሌጁን ዲን ብፁዕ አቡነ ገብርኤልን አነጋግረን ነበር ብፁዕነታቸውም ኮሌጁ የሚከፈተው ለዲያቆናትና ለቀሳውስት ማሠልጠኛ ነው ከዚህም ሌላ በከፍተኛ ደረጃ የሚያሠለጥናቸው ካህናት ይኖራሉ ወ/ት ዕፀ ገነት መንፈሳዊ ኮሌጅ ገብታ ለመማር የፈለገችው ለክህነት አገልግሎት ነው? አላማዋን ግልጥ አላደረገችም ። በመንፈሳዊ ኮሌጅ የሚሰጠውን መንፈሳዊ ትምህርት ከተማረች በኋላ በምን አይነት ሥራ ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል እንደፈለገች አልገለጠችም ። ስለዚህ በኮሌጁ ገብተሽ ለመማር ትችያለሽ ወይም አትችይም ብሎ መልስ ለመስጠት በቅድሚያ ዓላማሽን ማወቅ ስለሚያስፈልግ ዓላማሽን ግልጽ አድርጊ ብለዋል ።

እኛም በዚህ ኮሌጅ ገብተሽ ለመማር ያሳሰበሽን ዓላማ ፣ ወይም ቤተ ክርስቲያንን በምን ዓይነት ሥራ ለማገልገል ፈልገሽ እንደሁ የጠየቅሺው ጥያቄሽን

ወደ ገጽ ፳፩ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

ርእሰ አንቀጽ

# የቅዱስ ፓትርያርኩ ታሪካዊ ጉብኝት ያስገኘው ፍሬ

ከመልካም ዛፍ መልካም ፍሬ እንደሚጠበቅ ከእውነተኛ መንፈሳዊ መሪም የሥራ ፍሬ ይጠበቃል ። ከጥንት ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጊዜያቸው ለቤተ ክርስቲያን ታሪካዊ የሆነ የሥራ ፍሬ እያበረከቱ አልፈዋል ።

ለምሳሌ ቅዱሳን አትናቴዎስ ዮሐንስ አፈ ወርቅና እነ ጎርጎርዮስ ለዘለዓለም የማይረሳ ሥራ ስለሠሩ ታሪክ ሲያስታውሳቸው ይኖራል ። በዚህ አንፃር በሐዋርያዊት መንበር የሚቀመጥ መንፈሳዊ መሪ ሁሉ በሐዋርያዊነት ዘመኑ ፍሬያማ ሥራ ይሠራ ዘንድ ቤተ ክርስቲያኑ ትፈልግበታለች ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክና የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀ መንበር ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ባለፈው መጋቢት ወር 24 ቀን እስከ ሚያዝያ 14 ቀን 1972 ዓ.ም በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምና በአቴንስ ያደረጉት ታሪካዊ ጉብኝት ፍሬማ ውጤት አስገኝቶአል ። ለምሳሌ ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ህልውና በአንዳንድ የውጭ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ዘንድ የነበረውን አጉል ጥርጣሬ አስወግዶአል ። በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያናቸው ያለ ምንም ችግር ወንጌልን እንደምታስተምርና ሥነ አምልኮትዋን እንደምታካሂድ በታሪካዊ ጉብኝታቸው ወቅት ለአኃው መንፈሳውያን መሪዎች ሁሉ አስረድተዋል እንደዚሁም ለብዙ ዓመታት በግብጽና በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት መካከል በዴር ሡልጣን ምክንያት ለነበረው ጭቅጭቅ የቅዱስነታቸው ታሪካዊ ጉብኝት የማያዳግም መፍትሔ ማስገኘቱ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ ክርስቲያን ታላቅ ፍሬ-በረከት ነው ።

ይህ ብቻ አይደለም ፣ በይዞታ ሥር የሚገኘው በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳምም በሚገባ ያልተያዘና ብዙ ጉድለት ያለበት በመሆኑ ቅዱስነታቸው በጥሩ ሁኔታ እንዲያዝ መመሪያ ከመስጠታቸውም በላይ ገዳማቱ እንዲታደሱ ከሚመለከታቸው ባለሥልጣኖች ጋር ተወያይተው ከውሳኔ ላይ ደርሰዋል ። ይህም በቅርቡ ፍጻሜን በሚያገኝበት ጊዜ ለታሪካዊ ጉብኝታቸው ፍሬያማ ውጤት ይሆናል ።

ከዚህም ጋር ቅዱስ ፓትርያርኩ ከቅድስት ሀገር ሲመለሱ ዝነኛ የሆነችውን የግሪክን ዋና ከተማ አቴናን ለ3 ቀናት በጐበኙበት ወቅት የግሪክ አብያተ ክርስቲያናት የካህናት ማሠልጠኛን ስለተመለከቱ በዚያው አንጻር ለቤተ ክርስቲያናቸው ከፍተኛ የካህናት ማሠልጠኛ ኮሌጅ እንደሚያሠሩ ፍጹም ተስፋ ተደርጎአል ። ይህን በማስመልከት ፣-ቅዱስ ፓትርያርኩ በቅድስት ሀገር ታሪካዊ ጉብኝታቸውን ፈጽመው በተመለሱ ጊዜ አንድ ባለ ቅኔ እንዲህ ብሏል "ቅዱስ ያሬድ ወደ ሰማያዊት ኢየሩሳሌም በተመስጦ ሄዶ ከተመለሰ በኋላ በዚያ የሰማውንና ያየውን ሁሉ በቤተ ክርስቲያን አሰማ ፤ በዚህም አንጻር ወደ ምድራዊት ኢየሩሳሌም ሄደው የተመለሱት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በኢየሩሳሌም ያዩትን መንፈሳዊ ሥርዓት በቤተ ክርስቲያናቸው ይሠራሉ ። በግሪክም ያነበቡትን በሀገራቸው ይተረጉማሉ"

አዎ ታሪካዊ ጉብኝታቸው ዘለዓለማዊ ታሪክ ሆኖ ይኖር ዘንድ በክብር ተዘዋውረው ከተመለከቱአቸው አብያተ ክርስቲያናት ጋር በእግዚአብሔር ኃይል ቤተክርስቲያናቸውን እንደሚያስተካክሉ እት ተስፋ እናደርጋለን ።



# የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ

## ጉብኝት በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም

ኢትዮጵያውያን የኢየሩሳሌምን ቅድስና በማወቅ ከብዙዎች የዓለም ሕዝቦች ቅድምና ያላቸው በመሆናቸው በዘመነ ብሉይም ሆነ በዘመነ ሐዲስከኢየሩሳሌም ጉዞ ያረፉበት ጊዜ የለም ። ከግለሰቦች ጀምሮ እስከ መሪዎች ድረስ የኢትዮጵያ ምዕመናን ቅድስትሀገርን ለመጐብኘት በእግርና በከብት ጀርባ በመጓዝ የረጅም ጊዜ ታሪክ አላቸው ።

ታሪክ እንደሚያስረዳው ንግሥተ ሳባ የሰሎሞንን ጥበብና ዝና በመስማት ወደ ኢየሩሳሌም ባደረገችው ጉዞ ውጤት የኢትዮጵያ እግንያን ትክክለኛውን እምነትና አምልኮተ እግዚአብሔርን ለመከተል ያበቃቸው ከመሆኑም በላይ ስለኢየሩሳሌምም በደብልጥ እንዲያውቁ ስለአደረጋቸው ይህ እውቀታቸው ጥንትም አሁንም የኢየሩሳሌም መንገደኞች እንዲሆኑ አድርጓቸዋል ።

በግብረ ሐዋርያት ም· ፰ ቍ ፳፯እንደተገለጸው የንግሥት ሕንደኬ ጃንደረባ ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም በሠረገላ የተጓዘውም በዚህ ምክንያትነበር። የቀደሙ አባቶች በእግር ይጓዙት የነበረው የኢየሩሳሌም ረጅም ጉዳና አሁን በአኤሮፕላን ማጻረጥ ስለተቻለ ኢየሩሳሌም ለኢትዮጵያ ምዕመናን ከድሮው በጣም የቀረበች ሁናለች ። ይህም ሁኔታ ወደ ኢየሩሳሌም የሚደረገውን ጉዞ ከዓመት ወደ ዕለት እያሳጠረው ስለመጣ ስለኢየሩሳሌም ማዕከልነት የተነገረው ትንቢት ሁሉ በመፈጸም ላይ ነው ።

ይህ ከሆነ ዘንድ የኢየሩሳሌም ጉብኝት ስለ ኢየሩሳሌም የተነገረው ትንቢት ሁሉ ይደረስ ይፈጸም ዘንድ የሚደረግ ጉዞ እንደመሆኑ መጠን ከዚህ በፊት የነበሩ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ኢየሩሳሌምን በይፋ መጐብኘታቸው ይታወሳል ። በአሁኑም ጊዜ ሦስተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት ቅድስት ሀገርን ለመጐብኘት የነበራቸው ዕቅድ በእግዚአብሔር ፈቃድ ተፈጽሞ የትንሣኤን በዓል ምክንያት በማድረግ ከመጋቢት ፳፬ ቀን እስከ ሚያዝያ ፲ ቀን ፸፪ ዓ· ም· በኢየሩሳሌም ይፋ ጉብኝት ሲያደርጉ ቆይተው ተመልሰዋል ። ቅዱስነታቸው ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምን የጐበኙት ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት የተውጣጡ ልዑካንን በመምራት ሲሆን እነዚህም የሚከተሉት ናቸው።

### ፩· ከቅዱስ ሲኖዶስ

ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የጐጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ፤
ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ ፤
ብፁዕ አቡነ ገብርኤል የድሬዳዋ የወበራና የጨርጨር አውራጃዎች ጳጳስ ፤

### ፪. ከጠቅላይ ቤተ ክህነት

ሊቀ ኅሩያን መርሐ ጽድቅ ገ/ሕይወት የመንበረ ፓትርያርኩ ም/ ልዩ ጸሐፊ፤ አቶ ተስፋሁን አየለ አስተርጓሚ፤ መልአከ ታቦር ተሾመ ዘርይሁን የውጭ ጉዳይ ክፍል ኃላፊ ናቸው ።

የቅዱስነታቸውን ታሪካዊ ጉብኝት በጋዜጣም በመጽሔትም ለሕዝብ መግለጽ ምዕመናን የጉብኝቱን ሁኔታ በበለጠ እንዲረዱት የሚጠቅም ከመሆኑም በላይ ለተከታቱም ትውልድ ይህንታሪክ ማቆየት የቤተ ክርስቲያን ግዴታ ስለሆነ ይህንታሪካዊ ሪፖርት ማዘጋጀት አስፈላጊ ሁኗል ጽሑፉ የሚያስረዳ ው፦

፩ኛ/ ቅዱስነታቸው ኢየሩሳሌምን በይፋ ለመጐብኘት ከአዲስ አበባ ሲነሱ በቦሌ አውሮፕላን ማቢያ የተደረገውን የክብር አሸኛኘት ።
፪ኛ/ በኢየሩሳሌም ስለተደረገው አቀባበልና አሸኛኘት ፤
፫ኛ/ ቅዱስነታቸው የጐበኟቸውን ቅዱሳት መካናት ፤
፬ኛ/ ቅዱስነታቸው ስለአነጋገሯቸው የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና የመንግሥት ባለሥልጣናት
፭ኛ/ በአቴንስ ስለተደረገው የ፫ ቀናት ጉብኝት ሲሆን ይህም በታሰበው መሠረት የጉብኝቱን ዓላማና ውጤት ለማሳወቅ እንደሚጠቅም ይታመናል ።

**ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ከአዲስ አበባ ሲነሱ በቦሌ አይሮፕላን ማቢያ የተደረገ አሸኛኘት ።**

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም የሥራ ጉብኝት ለማድረግና ቅዱሳት መካናትንም ለመሳለም የነበራቸው ዕቅድ በእግዚአብሔር ፈቃድ ተፈጽሞ መጋቢት ፳፬ ቀን ፸፪ ዓ·ም ከቀኑ በ፲ ሰዓት ከክብር ተከታዮቻቸው ጋር በኢትዮጵያ ዓየር መንገድ ከአዲስ አበባ ተነሱ ። ብፁዕ ወቅዱስነታቸውን ለመሸኘት ከጠቅላይ ቤተ ክህነት በወጣው መርሀ ግብር መሠረት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት ፤ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ባለሥልጣናት ፤ የአድባራት አለቆችና ካህናት የጠቅላይ ቤተ ክህነት መ/ቤት አባሎችና ምዕመናን በቦሌ አይሮፕላን ማቢያ ተገኝተው የክብር አሸኛኘት አድርገውላቸዋል ቅዱስነታቸው ከአይሮፕላን ማቢያው ከመነሳታቸው በፊት በአይሮፕላን ማቢያው ልዩ ሳሎን ስለጉብኝታቸው ከጋዜጠኞች ለቀረበላቸው ጥያቄ መልስ ሰጥተዋል ። በሰጡትም መልስየኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በኢየሩሳሌም በአንድ ሊቀ ጳጳስ የሚመራ የገዳም ይዞታ ስላላትና ይህም ይዞታ እንደ አንድ ሀገረ ስብከት ስለሚቆጠር ይህን ሀገረ ስብከት ለመጐብኘት መሆኑንና በጉብኝታቸውም ወቅት ስለደር ሡልጣን ገዳም ችግር ጉዳይ ከሚመለከታቸው የእሥራኤል መንግሥት ባለሥልጣናት እንደሚነጋገሩ ገልጸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩን የያዘው አይሮፕላን ከቦሌ አይሮፕላን ማቢያ ተነሥቶ አሥመራ አይሮፕላን ማቢያ ከረፈ በኋላ በቀጥታ ወደ አቴንስ በመብረር ከቀኑ በ፲፩ ሰዓት አቴንስ አይሮፕላን ማቢያ ሲያርፍ በግሪክ የኅብረተሰባዊት ኢትዮጵያ አምባሳደር አቶ አስፋው ለገሠ በግሪክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የክርስቲያን ጉዳይ መምሪያ ተወካይ ።

የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ተወካይ ብፁዕ አቡነ ክርስስቶምስ ፤ በግሪክ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተማሪዎች በአይሮፕላን ማቢያ ተገኝተው በክብር ተቀብለዋቸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስነታቸው ከአይሮፕላን ወርደው በአይሮፕላን ማቢያ ልዩ ሳሎን እንዳረፉ ከኢትዮጵያ ተማሪዎች አንዱ አለቃ ፍስሐ ጽዮን ካሣዬ በሌሎች ተማሪዎች ስም ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩን «እንኳን ደህና መጡ » በማለት አጭር ንግግር አደረጉ ።

በጉዞው መርሀ ግብር መሠረት አዳር በአቴንስ ስለሆነ በአይሮፕላን ማቢያው ልዩ ሳሎን የሚደረገው ሥነ ሥርዓት እንደተፈጸመ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አስተናጋጅነት ለማረፊያ ወደ ተዘጋጀው የፒንደሉ ገዳም አመሩ ።

የፒንደሉ ገዳም በግሪክ ከሚገኙት ታሪካውያን ገዳማት አንዱ ሲሆን የሚገኘውም በአቴንስ ከተማ ጠረፍ ላይ ነው ።

ገዳሙ የተመሠረተው እንደ እ·ኤ·አ· ፲፫፻፺፬ ዓ·ም ሲሆን ግሪክ በቱርኮች ተወራ ግሪካውያን በቱርካውያን አገዛዝ ሥር በወደቁበት ወቅት በገዳሙ የሚገኘው ምድር ቤት ለግሪካውያን እምነታቸውንና ባሕላቸውን የሚያስተምሩበት የምሥጢር ትምህርት ቤታቸው ስለነበረ ግሪካውያን ገዳሙን እንደ አንድ ከፍተኛ የታሪክ ቦታዎች አድርገው ይጐበኙታል ። በታሪክነቱም ይኮሩበታል ፤ በአሁኑ ጊዜ ገዳሙ የመላው ኦርቶዶክስ ጉባኤ መሰብሰቢያ ስለሆነም በአርኪዮሎጂ ታሪካዊና የተሟላ ድርጅት ያለው ታላቅ ገዳም ነው ።

ብፁዕ ወቅዱስነታቸው ከነተከታዮቻቸው ሌሊቱን በዚህ ገዳም ካሳለፉ በኋላ ጉዞው ቀጠለ ፤ ብፁዕ ወቅዱስነታቸው መጋቢት ፳፭ ቀን ፸፪ ዓ·ም ሐሙስ ከቀኑ በ፯ ሰዓት ከአቴንስ አይሮፕላን ማቢያ ሲነሱ በግሪክ የኅብረተ ሰብአዊት ኢትዮጵያ አምባሳደር አቶ አስፋው ለገሠና ሌሎችም የግሪክ ቤተክህነት ባለሥልጣናት ፤ በአይሮፕላን ማቢያው ተገኝተው በክብር ሸኝተዋቸዋል ብፁዕ ወቅዱስነታቸውን የያዘው የትራንስ ወርልድ አሶሲየሺን አይሮፕላን ከቀኑ ፯ ሰዓት ከአቴንስ ማቢያ ተነሥቶ ፰ ሰዓት ፲፭ ደቂቃ ቴልአቪቭ ልዳ አይሮፕላን ማቢያ አረፈ ።

በልዳ አይሮፕላን ማቢያ የተደረገ አቀባበል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩን የያዘው አይሮፕላን ቴል አቪቭ ልዩ አይሮፕላን ማቢያ አርፎ ቅዱስነታቸው ከአይሮፕላን ሲወርዱ ፤

ብፁዕ አቡነ ማትያስ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስና ማኀበሩ ።

በእሥራኤል መንግሥት የሃይማኖት ሚኒስቴር ዲሬክተር ጀኔራል ሏፒልና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ጉዳይ ክፍል ተወካይ እንዲሁም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ክርስቲያኖች ክፍል ኃላፊ በኢትዮጵያ የኢየሩሳሌም ድርጅት ተጠሪዎችና በኢየሩሳሌም የአርመን ፓትርያርክ ተወካዮች ሌሎችም ምእመናን በአይሮፕላን ማቢያው ተገኝተው የክብር አቀባበል አደረጉላቸው በዚህ ጊዜ ሕጻናት እቅፍ አበባ አበርክተውላቸዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

ተጥሎም ቅዱስነታቸው በአይሮፕላን ማቢያው ልዩ ሳሎን እንደተገኙ ሚስተር ሲፐስ በሃይማኖት ሚኒስቴር ዳይሬክተር ጀኔራል ብጽዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩን እንኳን ደህና መጡ በማለት ንግግር አደረጉ ባደረጉትም ንግግር የኢትዮጵያና የእሥራኤል ግንኙነት ከንግሥት ሳባ ጀምር ወንተ የቆየ ታሪካዊ በመሆኑ የሁላችንም አባት የሆኑትን ብፁዕ ወቅዱስነታዎን ስንቀበል ከፍተኛ ደስታ ይሰማናል ሲሉ በሕዝብ እሥራኤል ስም የተሰማቸውን ደስታ ገልፀዋል ቅዱስነታቸው ስለተደረገላቸው መልካም አቀባበል የተሰማቸውን ደስታ በመግለጽ ለንግግሩ መልስ ሰጡ ። በዚህም ጊዜ ብፁዕ ወቅዱስ ፓርትርያርኩ በጉብኝታቸው ወቅት ስለ ዴር ሡልጣን ገዳም ጉዳይ ከእሥራኤል መሪዎች ጋር ለመነጋገር እቅድ እንዳላቸውና የፈላሾችንም ጉዳይ እንዴት እንደሚመለከቱት ከጋዜጠኞች ቃለ መጠይቅ ቀርቦላቸው መልስ ሰጥተዋል በስጦም መልስ በኢትዮጵያ የሚገኙት የአይሁድ እምነት ተከታዮች በአሁኑ ሥርዓተ ማኅበር እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ እኩልነታቸው የታወቀና መብታቸው የተጠበቀ እንደ ሆነ ከማስረዳታቸውም በላይ በጉብኝታቸው ወቅት ስለዴር ሡልጣን ገዳም ችግር ጉዳይ ከሚመለከታቸው ባለሥልጣኖች ጋር እንደሚነጋገሩ ገልጸዋል ።

ከዚህ በኋላ የሻይ ግብዣ ተደርጎ በዚያ የሚደረገው የአቀባበል ሥነ ሥርዓተ እንደተፈጸመ ቅዱስነታቸው በቀረበላቸው አውቶሞቢል ሆነው ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ ጉዞ ሆነ ።

### በኢየሩሳሌም ከተማ የተደረገ አቀባበል ።

ብጹዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ከሌዳ አይሮፕላን ማቢያ በአቶሞቢል ሆነው ከቀኑ በ፲ ሰዓት ጃፋጌት እየተባለ ከሚጠራው የኢየሩሳሌም ከተማ ዋና በር እንደደረሱ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩን ለመቀበል ተራ የተደረገላቸው የሃይማኖት መሪዎች ፣ የመንግሥት ባለ ሥልጣኖች የውጭ ሀገር እንግዶች ፣ ቆንሲሎች ፣ የገዳማቱ መነኮሳትና ኢትዮጵያውያን ምእመናን እንዲሁም በጠቅላላ በጃፋጌት ተሰልፎ የብጹዕ ወቅዱስነታቸውን መድረስ ይጠባበቅ የነበረው የኢየሩሳም ሕዝብ በደስታና በክብር ተቀበላቸው በዚህ ጊዜ አንዲት ኢትዮጵያዊት ሕፃን ለቅዱስ ነታቸው አበባ አበረከተች ከዚያም ብፁዕ አቡነ ማትያስ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ፣ የሃይማኖት መሪዎችንና የመንግሥታት ባለሥልጣናትን በቅደም ተከተል ለቅዱስነታቸው አስተዋወቁ።

አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ኢየሩሳሌምን ሲጎበኝ በቅድሚያ ቅዱስ ጉልጉታን በመጎብኘት የሕሊና ጸሎት ማድረስ የተለመደ ቢሆንም በዚህ ዕለት ግን በቅዱስ ሥፍራው ባለው ጥንታዊ ሥርዓት መሠረት የጸሎተ ሐሙስ ዕለት ላቲኖቹ በዝግ በር የራሳቸውን ሥርዓተ ጸሎት ሲፈጽሙ የሚውሉ ከመሆናቸው የተነሳ የቅዱስ ጉልጉታ ዋና በር በባለይዞታዎቹ ተዘግቶ ስለነበር በጃፋጌት የሚደረገው የአቀባበል ሥነ ሥርዓት እንደተፈጸመ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ከጉልጉታ በር የሕሊና ጸሎት ካደረጉ በኋላ በሰልፍ በተቀበላቸው ሕዝብ ታጅበው ወደ ዴር ሡልጣን የኢትዮጵያ ገዳም ቤተ መቅደስ ገቡ። በዚህም ጊዜ የቅዱስነታቸውን መድረስ የሚያበስር የደወል ድምጽ ተሰማ ፣ ቅዱስነታቸው ከገዳሙ እንደደረሱ ልብሰ ተክህና የለበሱ መነኮሳትና ዲያቆናት መስቀልና ፅንሐ ይዘው በግዕጠንት ተቀብለዋቸው ወዲያው ጸሎተ ወንጌል ተጀምር ከዳዊት መዝሙር «እስመ መምሕረ ሕግ ይሁበ በረከተ» የሚለው ምስባክ ተሰበከ ፣ ቅዱስነታቸው ከዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፲ ቁጥር ፩-፲፱ በማንበብ ለተሰበሰበው ሕዝብ ቃለ ወንጌል አሰሙ ። ተጥሎም ቅዱስነታቸው የማሳረጊያ ጸሎት ሰጥተው ጸሎተ ወንጌሉ እንደተፈጸመ በመጡበት አኳኋን ከቤተ መቅደሱ ወጥተው ለማረፊያ ወደ ተዘጋጀላቸው ወደ መንበረ ቅቁስናው ጉዞ ሆነ ።

### የአርመን ቤተ ክርስቲያን መዘምራን

ብጹዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ከጾፋጌት ተነስተው በሰልፈኛው ሕዝብ ታጅበው በከተማው መካከል ወደ ዴር ሡልጣን ገዳም በክብር ሲጓዙም ሆነ ከዚያ ወጥተው ወደ መንበረ ሊቀ ቅቅስናው ሲያመሩ የሰልፍ ልብስ የለበሱ የአርመን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ኩሌጅ ተማሪዎች ፣ ወጣትና ሕፃናት መዘምራን በጉዳናው ግራና ቀኝ ተሰልፈው የደስታ ድምፅ የሚያሰማ ታምቡር በመምታትና መንፈሳዊ ሰላምታ በመስጠት ከፍ ያለ አቀባበል አድርገውላቸዋል ። ይህ ዓይነቱ አቀባበል ከዚህ ቀደም ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያልተደረገ አስደሳች የክብርአቀባበል እንደ ነበር ተረጋግጧል። የአርመን ቤተ ክርስቲያን ስለምስጢረ ሥጋዌ አንድ ዓይነት ትምህርትና እምነት ካላቸው የኦሬንዶ-ታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያን አንዱ እንደ መሆኑም መጠን አቀባበሉ በእርግጥ የሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት አኅትማማችነት በተግባር የሚያሳይ ጉልህ ማስረጃ ነበር ።

### በመንበረ ሊቀ ቅቅስናው የተደረገ አቀባበል

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በመንበረ ሊቃነ ቅቅስናው ሳሎን እንደ አረፉ ብፁዕ አቡነ ማትያስ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩን እንኳን ደኅና መጡ በማለት የሚከተለውን የደስታ መግለጫ ንግግር አደረጉ ።

## የብፁዕ አቡነ ማትያስ ንግግር ሙሉ ቃል

በአብ በወልድ ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም አንድ አምላክ አሜን ።

እስመ ኩሉ ሊቀ ካህናት እምሰብእ ይትነሣእ ወበእንተ ሰብእ ይሠየም ለኀበ እግዚአብሔር ከመ ያብእ ቁርባነ ወመሥዋዕተ ዘበእንተ ኃጢአት።

ሊቀ ካህናት ሁሉ ከሰው ወገን ይመረጣል የሕዝቡን ኃጢአት ለማስተሥረይ የሚያቀርበውን ቁርባን መሥዋዕት ወደ እግዚአብሔር ስለ ሰው ያቀርብ ዘንድ ስለ ሰው ይሾማል ዕብ ፭/፩

«ወይእዜኒ ዕቀቡ ርእሰክሙ ወኵሉ መራዕየ ዘሎቱ ሤመክሙ መንፈስ ቅዱስ ጳጳሳተ ከመ ትርአዩ ቤተ ክርስቲያኑ ለክርስቶስ እንተአጥረያ በደሙ»

በወርቀ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጐ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ ። የሐ. ሥ ፳ ፳፰ ።

### ቅዱስ አባታችን

ለመጀመሪያ ጊዜ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም መንፈሳዊ ግልጽ ጉብኝት ለማድረግ ከክብር ተከታዮችዎ ጋር እንኳን በደኅና መጡ እያልሁ ፣ በራሴ ፣ በማኅበሩና በኢትዮጵያውያን ምዕመናን ስም መንፈሳዊ ደስታዬን ለቅድስናዎ እገልጻለሁ ።

የቅዱስናዎን ጉብኝት ለረጅም ጊዜ በታላቅ ተስፋ ስንጠባበቀው የቆየን ሲሆን ፣ ምኞታችንን ከፍጻሜ ያደረሰልን እግዚአብሔር ስሙ የተቀደሰ ይሁን ።

ጉብኝቱ እያሌ ፍሬ ነገሮችን የምንጠብቅበት ፣ ከኀዘናችን የምንጽናናበት ፣ ከድካማችን የምናርፍበት ፣ችግራችንን የምናስወግድበት አቋማችንን የምናጠነክርበት ታላቅ ኃይል ከመሆኑም በላይ የዘንድሮ የ፲፱፻፸፪ ዓ/ ም/ የትንሣኤ በዓላችንን ስናከብር ቅዱስነትዎ በመካከላችን በመገኘትዎ ለብዙ ዓመታት የችግራችን ተካፋይ በሆነው በኢየሩሳሌም ምዕመናን መታሰቢያ ድርጅት አማካይነት ከኢትዮጵያ ከመጡትና በድርጅት ቅርንጫፍ አማካይነት እዚሁ ከሚገኙት እንዲሁም ጠቅላላ ማኅበርና በእሥራኤል ሀገር ካሉት ኢትዮጵያውያን ምእመናን ጋር በአንድነት ደስ ብሉናል ።

### ቅዱስ አባታችን ሆይ

ሀገራችን ኢትዮጵያ የአምልኮተ እግዚአብሔር ቀዳሚነት ካላት ከቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ጋር ያላት ታሪካዊ ግንኙነት ሦስት ሺህ ዓመታት ሊሆን ምንም አልቀረውም «ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር» ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች ተብሎ በነቢዩ እንደተነገረላት አልምኮተ እግዚአብሔርን በመቀበል ከሌላው ዓለም ትቀድማለች ፣ ይህንንም የተቀደሰ አምልኮት ያገኘችው በርችው ሀገረ እግዚአብሔር ነው ።

በዚህም አሪታዊ አምልኮ ከአንድ ሺ ዓመታት በላይ ተጠቀመችበት ከመሆኑም በላይ ፣ በእነዚያ ዓመታት ውስጥ በኦሪቱ ሕግ መሠረት ኢትዮጵያውያን ወደ ኢየሩሳሌም ይመላለሱ እንደነበር ታሪክ ያስረዳል ። ፩ኛ ነ ሥት ፲ ፣ ፩

ሐዲስ ኪዳንንም ቢሆን በሠላሳ አምስተኛው ዓመተ ምሕረት አካባቢ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ከሐዋርያዊ ፊልጶስ ተቀብሉታል ፣ ይህ ሁሉ ኢትዮጵያ ሕገ ኦሪትን ሆነ ሕገ ወንጌሉን ስትቀበል ያንድም ነቢይ ወይም ያንድም ሐዋርያ ደም አላፈሰሰችም ፣ ሌሎች አንዳንድ ሀገሮች ግን ነቢያት ሐዋርያት ሲ ኩላቸው በእሳት ሲያቃጥሏቸው ፣ በመይፍ ሲቆርጧቸው ፣ በእናብስት ሲያስብሯቸው በኩላብ ሲስቅሏቸው ኢትዮጵያ ግን ራሷ እየመጣች እምነቱንና ሕግጋቱን ትቀበለው ነበር፤በዚህም ቅድስናዋ «ንጹሐን ከቡራን ሳያቶች የሚያምኑብኝ ናቸው» ብሉ መድኃኒታችን አመስግኗታል ።

ይህ የባዕድ ስብከት ያልተቀላቀለበት የነቢያትም ሆነ የሐዋርያት ደም ያልፈሰሰበት ንጹሕ እምነት ተጥሎ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሕገ ወንጌል በሙላ ኢትዮጵያ ሲስፋፋ «ዘኢ ሐደገ እባሁ ወእሞ ኢይከል ይጸመደኒ» በሚለው አምላካዊ ቃል የተማረኩ ኢትዮጵያውያን በብዛት ወደዚች ታሪካዊት ሀገር ይጉርፉ ጀመር ፣ እነዚህ የቀን ሐሩር ፣ የሌሊት ቁር የማይበግራቸው በሥጋዊና በመንፈሳዊ እርበኝነት የተመሰከረላቸው ጥንካሬ የተፈርኡቸው የሆኑ ኢትዮጵያውያን እንደዛሬ ሰው ልጅ በዓለም ላይ ባልበዛበት ደን ባልተመነጠረበትና አውሬ ባልሸሸበት በዚያ ዘመን በእግር ጉዞ አገር እቋርጠው ሲመጡ እሾዋ ውጦአቸው ፣ አውሬ በልቶአቸው ፀሐይ አቃጥሏቸው የተረፉት በብዙ ፀዋትወ መከራ እዚህ ኢየሩሳሌም ይደርሱ ነበር።

አማልክትን ያሸነፈ ዕውነተኛው አምላክኢየሱስ ክርስቶስ በተዋሐደው ሥጋ ሕማማተ መስቀል በተቀበለበት በዋተበት ፣ በተቀረበረበትና በተነሣበት ላይ በቅዱስ ጉልጎታ በቀራንዮ ባለይዞታዎች ሆነው ገዳም መሥርተው መንፈሳዊ አገልግሉት እያበረከቱ በማኅበራዊ ኑሮ ተደራጅተው አንድ ሺህ አምስት መቶ ዓመታት ያህል ኖረዋል ።

በዚህም ቀደምትነታችን ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም (በጉልጎታ) የበዓል አከባበር ሥነ ሥርዓት ብርሃን በማውጣት ቅድሚያ ነበራት ፣ ዋትን በዋቱ ደምስሶበት መታሰቢያ የሆነው የትንሣኤን ብርሃን ለሕዝቡ በመጀመሪያ የሚያሳዩ ኢትዮጵያውያን እንደነበሩ የተረጋገጠ ነው ።



ይህ መብት እስከ አሥራ ስባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ከቀጠለ በኋላ ከኢትዮጵያ በየጊዜው ይላክ የነበረው ርዳታ በልዩ ልዩ ጦርነቶች መንገድ በመዘጋቱ ምክንያት ሲቋረጥ ባቸው መነኰሳቱከባድ ችግር ላይ ስለወደቁ በጉልጉታ (ቅዱስ መቃብር) ውስጥ የነበራቸው ይዞታ እጥተው በጎልጉታ ምሥራቃዊ ክፍል (ዴር ሡልጣን) ብቻ ተወስነው ቀሩ ።

ቦታውን የወሰዱትም በዚህ አልተወሰኑም በ፩ሺ፯፻፫ ዓ/ ም/ አካባቢ ኢብራሂም ዝቨረ የሚባል አንድ ግብጻዊ ስምንት ራሱን ሆኖ ወደ ዴር ሡልጣን መጥቶ በከተማው የሚያስጠጋኝ ስላጣሁ የሃይማኖት ወንድሞቼ ሁ ነኝና አስጠጉኝ ሲ ቸው የኢትዮጵያ መነኰሳት ፍጹም ትኖች ስለነበሩ በእንግድነት ተቀብለው ቦታ ሰጥተው ገዳማቸው ውስጥ ያስቀምጡታል ፣ ይህ ሰው በዘመኑ ኢየሩሳሌምን ይገዛ በነበረው በቱርክ መንግሥት ዘንድ ታዋቂነትና ተወዳጅነት እንዲሁም ሹመት አግኝቶ ከፍተኛ ባለሥልጣን ሆነ ፣ ወዲያው የኢትዮጵያን መነኰሳት ድካምና የዋህነት አይቶ ስለኢትዮጵያውያን ተጠያቂ እኔነኝ አለ ፣ በዚህ ጊዜ ወደ ግብጽ ልኮ አንድ ካህን አስመጥቶ ከኢትዮጵያ ገዳም ውስጥ አስገብቶ በእርሱ እንዲተካ አድርጐታል ፣ አሁንም ጨርሶ ገዳሙ የእኔ ነው ብሎ የዴር ሡልጣን ገሚሱን ሸጦ ለግብጾች ማቋቋሚያ አድርጐታል፤በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያውያን ችግራቸውን የሚገልጹበት ቋንቋ ስላልነበራቸው የመጣው ግብጻዊ ሁሉ የእኛ ጥገኞች እያለ መነኰሳቱን ያጉላላቸው ጀመር ።

ግብጾውያንም በ፲፰፻፷፰ ዓ/ ም/ ቤቱን እናሳድሳለንና ልቀቁ ብለው ዓፃቸውን አስጠቅልለው መነኰሳቱን ከመኖሪያ ቤታቸው አስወጧቸው። ከታደሰም በኋላ አናስገባም ብለው ሲያባርሯቸው አሁን ኢትዮጵያውያን መነኰሳት ካሉበት ቦታ ወጥተው ቀሩ ፣ መደበኛውን የኢትዮጵያውያንን ቦታ ግን ኮፐቶች ወርሰውት ቀርተዋል ።

እንዲሁም በ፲፰፻፸፰ ዓ/ ም/ ወረርሽኝ በሽታ ገብቶ የኢትዮጵያን መነኰሳት አንድ ሳይቀር ሲጨርሳቸው ግብጾች ግን ጊዜ ረድቷቸው የገዳሙን ቁልፍ ፈጽመው እጅ አደረጉና በበሽታው እመሻሻተው ወገናቸው ለነበረው ሀገረ ገዥ ነገረው የርስት ማስረጃዎቻቸውንና መላ መጻሕፍቶቻቸውን የያዘውን የዕቃ ግምጃ ቤት በእሳት አቃጠሉባቸው ፣ ከዚህ በኋላ የግብጾች እንጅ የሐበሻ የሚሉት ርስት እናውቅም አሉ እነሆ በዚሁ የተነሳ ጭቅጭቁ እስከ አሁን ቀጥሏል ።

እንግዲህ ጭቅጭቁ ከሁለት መቶ ዓመታት በላይ ሆኖታል ማለት ነው፤ መችም የሚያሳዝነው ኢትዮጵያ ሀገራችን በሥጋዊ አመራር ያን ያህል ዘመናት ነጻነቷን ጠብቃ ስትኖር በመንፈሳዊ ሥልጣን በኩል ለአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመታት ያህል በግብጾች ተገበር መቆየቷ ነው ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በራሷ ቋንቋ በራሷ ሊቃውንት የኖረች ነፃ ቤተ ክርስቲያን ናት ፣ ይህም ሊታወቅ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመታት ሙሉ ኢትዮጵያ ውስጥ ሲኖሩ አንድም ሕዝብ የአረብኛ ቋንቋ አጥንቶ በዓረብኛ ቋንቋ አልተሰበከም ፣ መጻሕፍትም በዓረብኛ ቋንቋ አልተጻፉም ።

### ቅዱስ ፓትረያርክ

ምንም እንኳን በኢየሩሳሌም መንፈሳዊ ይዞታችን የሚታወቀው በዴር ሡልጣን ገዳማችን ቢሆንም በዴር ሡልጣን አማካይነት ከዴር ሡልጣን በኋላ የተገኙ ለዓይናችን ማረፊያ ለመንፈሳችን ማረጋጊያ የሚሆኑ ከዴር ሡልጣን ጋር ስድስት ገዳማት አሉን ፣ እነዚህ ገዳማት የተገኙት በኢትዮጵያውያን ምእመናን በጐ አድራጊነት በየዘመኑ የተመሠረቱ ሲሆን ስማቸውና የሚገኙበት አካባቢ እንደሚከተለው ነው ።



ብፁዕ አቡነ ማትያስ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ቅዱስነታቸውን « እንኳን ደኅና መጡ » በማለት ንግግር ሲያደርጉ ።

፩ኛ/ ዴር ሡልጣን ገዳም ፣ የቅዱስ ሚካኤልና አርባዕቱ እንስሳ /ቤተ መቅደሶች የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መካነ ስቅለት ቀራንዮ ፣ መካነ መቃብር ጉልጎታ ምሥራቃዊ ክፍል ።

፪ኛ/ ደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት ገዳም በምዕራብ ኢየሩሳሌም ፣ ኢትዮጵያ መንገድ ከአዲሱ ከተማ ፣

፫ኛ/ መንበረ ሊቀ ቅቅስና /ገዳም/ ከአሮጌው ከተማ አርነት ግራ

፬ኛ/ ኢያሪኮ ቅድስት ሥላሴ ገዳም ፣ ጌታችን አርባ ሌሊትና አርባ መዓልት ከጾመበት ገዳመ ቆሮንቶስ ሥር የሚገኝ ።

፭/ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀበት መካነ ጥምቀቱ ታላቅ ገዳምና ሰፊ የአትክልት ቦታ የነበረው አሁን የጦር ሜዳ በመሆን ዝግ ሆኖ ከጥቅም ውጭ ሆኗል

፮ኛ/ ምስካበ ቅዱሳን ተክለ ሃይማኖት ገዳም ፣ ቢታንያ የመቃብር ቦታ /አልዓዛር የተነሳበት ናቸው ።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ገዳማት በጦርነቱ ምክንያት ከዮርዳኖስ በቀር በይዞታችን የሚገኙ ሲሆኑ ፣ በሙሉና በከፊል መንፈሳዊ አገልግሉት ይፈጸምባቸዋል ።

እነዚህን ገዳማት ያስገኙልንን በጐ አድራጊ የሆኑ ኢትዮጵያውያንን እግዚአብሔር አረፍተ ነፍስን እንዲሰጥልን ሁል ጊዜ በጸሎት እናስታውሳቸዋለን ።

### ብፁዕ ወቅዱስ ሆይ

ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም በመንፈሳዊ ደስታ እንደተቀበለች ሁሉ ጉብኝቱን በሚያከናውኑበት ወቅት የእግዚአብሔር ረድኤት ከእርስዎ ጋር እንዲሆን እመኛለሁ ።

መጋቢት ፳፭ ቀን ፲፭ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ. ም አባ ማትያስ ሊቀ ጳጳስ ዘኢየሩሳሌም ፤

ተጥሎም የአርመን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተወካይ ሊቀ ጳጳስ በአርመን ቤተ ክርስቲያንና በራሳቸው እንዲሁም በአቀባበሉ ሥነ ሥርዓት ላይ በተገኙት የአብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች ስም ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩን እንኳን ደኅና መጡ በማለት ንግግር አደረጉ ። ሌሎች የአብያተ ክርስቲያናት ተወካዮችም በቅደም ተከተል እየተነሡ ቅዱስነታቸው ለጉብኝት ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው በመካከላቸው በመገኘታቸው የተሰማቸውን ደስታ በንግግር ገለጹ ። በተለይም ለሥራ ጉዳይ ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው የሰነበቱ አንድ የናይጄሪያ ሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ስለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያላቸውን ከፍተኛ አክብሮት ስለ ቅዱስነታቸው የኢየሩሳሌም ጉብኝትም የተሰማቸውን ደስታ በመግለጽ ንግግር ካደረጉ በኋላ አንድ እጥር በትረ ኖላዊ ለብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ አበርክተዋል ። ይህ በትረኖላዊ የሚቶዲስት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በእርጭ ብርት ፈንታ የሚይዙት ዓይነት ነው ። በትረ ኖላዊው በሀገራችን ሠዓሊዎች በቅዱስ ወንጌል የተጻፈውን በመከተል ኖላዊ ክርስቶስን በበጐች ጠባቂ ምእመናን በመንጋ አንጻር ሲሥሉ ክርስቶስ በእጁ ይዞ የሚታየውን ዓይነት ዘንግ የሚመስል ሲሆን የእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችም ይህን ዓይነቱን በትረ ኖላዊ የሚይዙት የክርስቶስን አርአያ በመከተል የምእመናንን ታማኝ ኖሎት መሆናቸውን ለማረጋገጥ እንደሆነ ይታወቃል ።

የሌሎቹ ንግግር እንደተፈጸመ ብፁዕ ወቅዱስነታቸው ስለተደረገላቸው መልካም የወዳጅነት አቀባበል በማመስገን ለንግግሩ መልስ ሰጡ ።

## የብፁዕ ወቅዱስ ፓርያርኩ ንግግር ሙሉ ቃል


ምስጋና ለእግዚአብሔር በሰማይ ሰላምም በምድር ይሁን ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት የልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት ኃላፊዎች በክርስቶስ ወንድምና እኅቶች በጠቅላላ በእግዚአብሔር ስም ወደ ቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም በመምጣቴና በኢየሩሳሌም በሚገኙ ወንድሞች መካከል ለመገኘት በመብቃቴ የተሰማኝን ጥልቅ የደስታ ስሜት በቃላት ስገልጽ ከፍተኛ ደስታ ይሰማኛል ።

እነሆ በዚህ ሰዓት የትንሣኤን በዓል ምክንያት በማድረግ እኔና ሌሎችም የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ከእኔ ጋር ቅዱሳት መካናትን ለመጐብኘትና ለመሳለም ወደ ኢየሩሳሌም መጥተናል ፤ ከዚህም ጋር በክርስቶስ ውድ ወንድሞች በሆናችሁት በእናንተ ይህ ዓይነት መልካም አቀባበል ተደርጐልናል ፣ ይህ ለእኛ በእርግጥ ለዘለዓለሙ በኅሊና የማይጠፋ ከፍተኛ መንፈሳዊ ደስታችን ነው።

ስለዚህም ሕያው እግዚአብሔርን ስለአደረገልን ቸርነት እናከብረዋለን



www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከእስራኤል ፕሬዚዳንት ክቡር ሚስተር ይስሐቅ ናቮን ጋር ስለዶር ሡልጣን ንብረታችን ሲነጋገሩ ፤

ማዕከል ስለሆነች ትንቢቱ በትክክል ተፈጽሟል ። የእኛም አሁን በዚህ ቦታ መገኘት ከትንቢቱ ፍጻሜ አንዱ ክፍል ነው ።

በመሠረቱ ኢየሩሳሌም ለኢትዮጵያ ምዕመናን እንግዳ ሀገር አይደለችም፤ የኢትዮጵያም ምእመናን ለኢየሩሳሌም እንግዶች አይደሉም ፤ በታሪክ እንደ ተረጋገጠው ከሕጽዋ ለሕንደኬ ንግሥተ ኢትዮጵያ በፊትም ሆነ በኋላ ኢትዮጵያውያን በእግርም ሆነ በሕሊና የኢየሩሳሌም ተጓዦች ናቸው ።

ይህንም የሚያደርጉት እግዚአብሔርን በፍጹም ልባቸው ስለሚወዱና አይሁዳውያንና ክርስቲያኖች ወንድሞችንም እንደ ራሳቸው ስለሚወዱ ነው ።

የኢትዮጵያ ምዕመናን እስከ አሁን ድረስ በየዓመቱ የትንሣኤን በዓልምክንያት በማድረግ ወደ ኢየሩሳሌም የሚያደርጉት ጉዞና አሁንም የትንሣኤን በዓል ለማክበር በዚሁ ቦታ መገኘታቸው ለዚህ ታላቅ ማስረጃ ነው ።

ስለዚህ በኢየሩሳሌም ተሰብስበን እናገናኛለን ፤ በክርስቶስ ውድ ወንድሞቻችን የሆናችሁትን እናንተንም ስለአደረጋችሁልን መልካም አቀባበል ከልብ እናመሰግናለን ።

በቅዱስ መጽሐፍ እንደተጻፈ ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር ቅድስት መንበርና የዓለም ቅድስት ከተማ ናት ነቢዩ ኤርምያስ አስቀድሞ ስለ ኢየሩሳሌም ሲተነብይ«በዚያን ጊዜ ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር ዙፋን ተብላ ትጠራለች ፤ሕዝብና አሕዛብ ሁሉ የእግዚአብሔርን ስም ለማመስገን በእርሷ ይሰበሰባሉ» ሲል ተናገር ነበር ፤ ኤር·፫/፲፯ ።

በአሁን ጊዜ ኢየሩሳሌም በነገድም በቋንቋም የተለያዩ ሕዝበ ክርስቲያን ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ተጉዘው በእግዚአብሔር ስም የሚሰበሰቡባት የጌታን ስም ለማክበርና በስሙም ለመደሰት ስላበቃን እግዚአብሔርን ዘወትር እናመሰግነዋለን ።

ስለተደረገልንም መልካም አቀባበል በድጋሚ እናመሰግናለን ።

እግዚአብሔር አንድነታችንን ይባርክ ፤ ለዓለም ሰላምን ይስጥልን ።

የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ንግግር እንደተፈጸመ የለስላሳ መጠጥ ግብዣ ተደርጐ በመንበረ ሊቀ ጵጵስናው የሚደረገው የአቀባበል ሥነ ሥርዓት ፍጻሜ ሆነ ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ኢየሩሳሌም የገቡት በሰሙነ ሕማማት የጸሎተ ሐሙስ ዕለት እንደመሆኑ መጠን የጸሎተ ሐሙስ ዕለት የተደረገው አቀባበል በዚህ ዓይነት ከተፈጸመ በኋላ በበነጋው የስቅለት ዓርብ ዕለት በዶር ሡልጣን ገዳም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት ሙሉ ቀን በተካሔደው ሥርዓተ ጸሎት ተገኝተዋል ። የቀዳም ሥዑር ዕለትም በመንበረ ሊቀ ጵጵስናው በተካሔደው የገብረ ሰላም በዓል አከባበር ላይ ተገኝተው ለምዕመናኑ ቡራኬ ሰጥተዋል።

## የገብረ ሰላም አከባበር ሥነሥዓርት

ከጥዋቱ በ፫ ሰዓት ልብሰ ተክህኖ የለበሱ መነኰሳትና ዲያቆናት ፤ የትንሣኤን በዓል ምክንያት በማድረግ ቅዱሳት መካናትን ለመሳለም ወደ ኢየሩሳሌም የሔዱ ምዕመናንና በኢየሩሳሌም የሚኖሩት ኢትዮጵያውያንም ምዕመናን የሀገር ባህል ልብስ በመልበስ በመንበረ ሊቀ ጵጵስናው ተሰብሰበው፲፩ ደቂቃ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በምእመናኑ መካከል ተገኙ ወዲያው «ገብረ ሰላመ በመስቀሉ» የሚለው ሰላም ተመርቶ ሥርዓተ ማኅሌቱ ተካሂ ኘቀጥሎም በክርስቶስ ሞት የተገኘውን ደኅንነት ለማብሠር በሀገር ባህል መሠረት የድልና የነፃነት ምልክት የሆነው የወይራ ዝንጣፊ በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ለምዕመናኑ ታደለ፤ ብፁዕ አቡነ ማትያስ የበዓሉን ታሪክ ለተሰበሰበው ሕዝብ አስተማሩ ። ከዚህ በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ጸሎተ ቡራኬ ሰጥተው የበዓሉ አከባበር ፍጻሜ ሆነ ።

## የትንግኤ ሌሊት

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ መጋቢት ፳፰ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ·ም· የትንግኤ ሌሊት በዶር ሡልጣን ገዳም ተገኝተው የትንግኤን በዓል አክብረዋል ። የበዓሉም አከባበር እንደሚከተለው ነበር ።

የትንግኤ በዓል በኢትዮጵያ ገዳም የሚከበረው የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና የመንግሥት ባለሥልጣኖች በሚገኙበት እንደ መሆኑ መጠን ከማታው በሁለት ሰዓት የመንግሥት ባለሥልጣናት የአብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች ከዶር ሡልጣን ገዳም ዓውደ ምሕረት ተገኙ ፤ ልብሰ ተክህና የለበሱ መነኰሳትና ዲያቆናት የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩን መድረስ በመጠባበቅ በተሰበሰበው ሕዝብ መካከል በተራ ቆመው የትንግኤን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም የሔዱ ምዕመናን ደማቅ የሀገር ባህል ልብስ ለብሰው በዓውደ ምሕረቱ ላይ በመገኘትአካባቢውን የኢትዮጵያ ከተማ አስመስለውት ነበር ከዚህ ሁሉ በኋላም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ፓትርያርክ በጳጳሳትና መነኰሳት ታጅበው ከመንበረ ሊቀ ጵጵስናው ወደ ዶር ሡልጣን ገዳም በማምራት በዓውደ ምሕረቱ ላይ በተሰበሰበው ሕዝብ መካከል ተገኙ በአፍሪካ አህጉር የራሱዋ የሆነ ባህልና ሥርዓት እንዲሁም የጣዕመ ዜማ ስልት ያላትን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በዓል አከባበር ለማየትሲሉ ቅዱሳት መካናትን ለመሳለም ከዓለም ዙሪያ የተሰበሰበው ተሳላሚ ቦታውን ስላጣበበው በዚህ ዓመት በተለይ ከፍተኛ የቦታ መጣበብና መጨናነቅ ደርሶ ነበር ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በዓውደ ምሕረቱ ላይ እንደተገኙ «ትንግኤከ ለእለ አመነ» የሚለው እስመ ለዓለም ተቃኝቶ ከተጸነጸለ በኋላ ጧፍ ተበርቶ ለሕዝቡ ታድሎ ኡደት ተደረገ ከኡደቱ በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በዓሉን በማስመልከት ለተሰበሰበው ሕዝብ ቃለምዕዳን አደረጉ። ከዚህ በኋላ በዓውደ ምሕረቱ ላይ የሚደረገው ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞ እንግዶቹ ከተሰናበቱ በኋላ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚካሔደው ሥርዓተ ጸሎት ቀጠለ ።

ከሌሊቱ ፯ ሰዓት የጸሎተ ቅዳሴው ሥነ ሥርዓት በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ መሪነት ተጀምሮ በ፰ ሰዓት ተፈጽሞ ሰርሆተ ሕዝብ ሲሆን ቅዱስነታቸው ወደ መንበረ ሊቀ ጵጵስናው ተመለሱ በዚሁ ሌሊት ቅዱስነታቸው የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት ባዘጋጀው ግብዣ ላይ ተገኝተዋል ።

## ማዕዶት

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ መጋቢት ፳፱ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ·ም· ጥዋት የማዕዶትን በዓል ምክንያት በማድረግ በደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው አስቀድሰዋል።ከቅዳሴውም በኋላ የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት ባዘጋጀው የቁርስ ግብዣ ላይ ተገኝተዋል ።

በዚሁ ዕለት በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ልጆች የሀገራቸውን ቋንቋና ባህል እንዳያጠኑ በገዳሙ ለተከፈተው ትምህርት ቤት ማስፋፊያ ከብፁዕ አቡነ ማትያስ በቀረበው የዕርዳታ ጥያቄ መሠረት ኢትዮጵያውያን ምዕመናን ባደረጉት ሰፊ ልግስና ከመጸሕፍት ሌላ የ፵ሺህ ብር ዕርዳታ ተገኝቷል ። ይህም ልግስና የኢትዮጵያ ምዕመናን ለሀገራቸውና ለዜጎቻቸው ለእምነታቸውና ለባህላቸው ያላቸውን ጽኑዕ ፍቅርና ቀናኢነት የሚያረጋግጥ በመሆኑ ተመልካችን አስደንቋል ከዚህ በኋላ በ፬ ሰዓት ቅዱስነታቸው ወደ መንበረ ሊቀ ጵጵስናው ተመልሰዋል ።

በዚሁ ቀን ከሰዓት በኋላ በ፰ ሰዓት ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ወደ ቅዱስ መቃብር ጐልጐታ ሂደው ጸሎት አድርሰዋል ።

## በቅዱስ ጐልጐታ የተደረገ አቀባበል

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ፓትርያርክ በጳጳሳትና በመነኰሳት እንዲሁም በምዕመናን ታጅበው ከቀኑ በ፰ ሰዓት ከመንበረ ሊቀ ጳጳስናው ተነስተው ወደጐልጐታ አመሩ ፤ ጐልጐታ በር ሲደርሱ ብፁዕ ወቅዱስ የአርመን አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ከአርመን ቤተ ክርስቲያን ገዳም ማኅበር ጋር ሁነው በክብር ተቀበሏቸው ። ቀጥሎም ቅዱስነታቸው ወደ ቅዱስ ጐልጐታ ገብተው የክርስቶስን መካነ ግንዘት ፤ መካነ መቃብርና መካነ ስቅለት በመጐብኘት ጸሎት አደረሱ ፤ከዚያም በብፁዕ አቡነ ማትያስእና በአርመኑ ፓትርያርክ እንደ ራሴ መሪነት በጐልጐታ ዙሪያ የሚገኙት ቅዱሳት መካናትን የታሪክ ቦታዎችን እየተዘዋወሩ ጐበኙ ። ቅዱስነታቸው መካነ ግንዘቱን፤መካነ መቃብሩንና መካነ ስቅለቱን በጐበኙበት ወቅት በልዑካኑ የማኅበር ጸሎት ከመድረጉም በላይ « ዘበእንቲአሃ ለቤተ ክርስቲያን» የሚለውና ክርስቶስ ተንስአ እሙታን የሚለው ያሬዳዊ መዝሙር በማኅበር ተዘምሯል ። በመጨረሻም ብፁዕ ወቅዱስ የአርመን ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ስለ ቅዱስነታቸው ክብር የሻይ ግብዣ አድርገዋል ። በግብዣውም ላይ የአርመን ቤተ ክርስቲያንና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አንድነታቸው በሃይማኖት ብቻ ሳይሆን

ወደ ገጽ ፱ ዞሯል



# በዐለ ሃምሳ

በሃይማኖት ትምህርት የሚታይና የማይታይ በእግዚአቤሔር የሆነበት ሁሉ የዓለም ታሪክ መነሻ ሲሆን ፤ ጊዜን መቁጠርና መቆጣጠርም የተጀመረው ከዚያኑ ጊዜ ጀምሮ መሆኑን የሙሴ መጽሐፍ ይነግረናል ።

በአንድ ነገር ማመን የተጀመረውም ዓለምከተፈጠረዘመንከተቆጠረሲሆን፣ እስከ ዘመን ድረስ የሆነውንም ሁሉ ስንመለከት ፤ ማንም ሰው ያለ ሃይማኖት መኖር የቻለበት ጊዜ እንዳልነበረ ሁሉ ፤ የበዐላት አመሠራረትና አመጣጥም ከዕለት ፤ ከሳምንት ፤ ከወርና ከዓመት የሰው ሕይወት ጋር ተያይዘው የመጡ መሆናቸውን የሃይማኖት ታሪክ ያስረዳናል ።

በአንድ ነገር ማመን ለዚያም መሥዋዕት በማቅረብ ከሌሎቹ የሥራ ቀናት የተለዩ የጸሎተ ቅዳሴ ፤ የደስታና የኀዘን ዕለታት ሁነው ተከብረው መዋላቸውን እናውቃለን ።

ሁሉችም የሃይማኖት ድርጅቶች የእየራሳቸው የሆነ የአምልኮት አፈጻጸም ስነ ሥርዓት ያላቸው ሲሆን ፤ የሁሉችም አላማ በፈጣሪና በፍጡር መካከል የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖር በመመኘት ነበር ። በአምልኮት አፈጻጸምም ሁለት ክስተቶች ይታያሉ ። እነዚህም የሚታዩና የማይታዩ ናቸው ። ይህም ውስጣዊና የውስጥ ስሜት በገቢር ጎልቶ የሚታዩበት ናቸው ።

በእነዚህ በሁለቱ የአምልኮት አፈጻጸሞችም እጅግ በጣም የተቃረበ ግንኙነት አለ ።

ከክርስትና በፊትም ሆነ በኋላ በየጊዜው የነበሩት የአምልኮታቸው የሕግ አቋምና ስነ ሥርዓት በሚፈቅደው መሠረት እንደእየእምነታቸው አምላካቸውን የሚቀድሱበት ፤ የሚያወድሱበት ለአምላካቸው መሥዋዕት የሚያቀርቡበት የከበሩ ዕለታትና የተለያዩ ቦታዎች እንደነበሩአቸው ከታሪካቸው እንረዳለን ።

ለምሳሌ ከክርስትና በፊት የነበሩት ጥንታውያን አሲሮ - ባቢሎናውያን ፤ ፔርሺያኖች ፤ ጂቶ - ዳቾች ፤ ጋሊካኖች፣ ሜክሲካውያን ግብፃውያን፤ሕንዳውያን፤ ግሬኮ-ሮማንናየመሳሰሉትሁሉበሚለዋወጡናበተወሰኑቀናትሃይማኖታዊየዓመት በዐላቸውን ያከብሩ እንደነበር ታሪካቸው ይነግረናል ። የእነዚህም ሕዝቦች የበዐላት አከባበር ከስነ ፍጥረት ፤ ከሕይወታቸው ወይንም ከኑሮአቸው ጋር የተያያዙ ነበሩ ። እንዲሁም ከአያት ፤ ከቅድመ አያት ተያይዘው የመጡ ቤተ ሰብእን የሚመለከቱ በቤተ ሰብ ደረጃ ብቻ የሚከበሩም በዐላት ነበሩ ። ይህም በበለጠ በሮማውያን ይፈጸም እንደነበር ታሪካቸው ይነግረናል ።

የእሥራኤላውያንም የእምነት ትምህርት የተመሠረተው በብሉይ ኪዳኑ በተገለጸው በአንድ አምላክ ማመን ሲሆን ፤ በማንኛውም በኩል ሕይወታቸውን የሚገዛና የሚመራ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ደህና አድርገው በመማራቸውና በማወቃቸው በኑሮአቸው ሁሉ ተቀዳሚ የሚያደርጉት የእምነታቸውን ሕግ መፈጸም በመሆኑ ፤ እስራኤላውያን ከሳምንቱ በዓላቸው ከሰባት (ከቀዳሚት)ሌላ የፋሲካ (ኦሪት ዘፀአት 12. 14-17)

የመከር በዐለ ሃምሳ (ኦሪት ዘዳግም 16.9 - 12)

የዳስ (የእህል መከተቻ)-ኦሪት ዘሌዋውያን 23 ፤ 39 - 43)

የማሥተሥርያ ቀን (ኦሪት ዘሌዋውያን 16. 11 - 22)

የመቅደስ መታደስ (ዮሐንስ 10. 22) የዓመት በዓላት እንደነበሩአቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል ።

የክርስትና ሃይማኖት በተመሠረተበት ጊዜም እንኳ የሮሜ መንግሥት የራሱ የሆነ የአምልኮ ጣዖት የበዐል አከባበር ነበረው ። እነዚህም በዐላት የተለያየ የአከባበር ጠባይ ኑሮአቸው በየቤተ ጣዖቱ ሕዝብ በተሰበሰበበት ይከበሩ ነበር ።

የክርስትናው እምነትም ከመጀመሪያው አንሥቶ የራሱ የሆነ የበዐላት አከባበር ቢኖረውም ቅሉ ግን እነዚህ የክርስትና በዐላት ሁለት ዓይነቶች የሆኑ የመነሻ ሞዴሎች ነበሩአቸው ። እነዚህም እብራዊና ግሬኮ - ሮማን ነበሩ ። በእነዚህም ሁለት ሞዴሎች መነሻነት የክርስትናው በዐላት ዕድገትንና ስፋትን እያገኙ መጥተው ከአንድ ምዕራፍ ላይ ይደርሳሉ ። ይህም ምዕራፍ የክርስትናው አምልኮት ነፃነትን ያገኘበት ዐራተኛው መቶ ዓመት መሆን ነው ።

የክርስትናው በዐላት የአከባበር እድገትም በመጀመሪያ በግለ ሰቦች የመኖሪያ ቤት በመሰብሰብ ፤ ከዚያም በየቤተ መቅደሱና በየምኩራቡ ፤ በየቤተ ክርስቲያኑ በመንበሩና በቁሱ ዙሪያ እየተሰበሰቡ ጸሎተ ቅዳሴውን በማድረስ ክርስቲያናዊ በዐላቸውን ማክበር ጀመሩ ። (የሐ.ሥራ 21.1 ፤ 20.16)

ክርስቲያናት ከተለመደው ከአድካሚው የዘወትር ሥራቸው ተላቀውና ዐርፈው በቤተ ክርስቲያን እየተሰበሰቡ በዐሉን ለማክበር በሰዓቱ የጸሎተ ቅዳሴው ተካፋዮች ለመሆን በቤተ ክርስቲያን ካሌንደር ወይንም ቀን መቁጠሪያ ይመራ ነበር ። በቤተ ክርስቲያን ቀን መቁጠሪያ እንዲሁም በስንክሣር የዕለቱን የሳምንቱን ፤ የወሩንና የዓመቱን በዐላት ለማወቅና ለማሳወቅ ታስቦ የበዐላቱ ቀናት በቀይ ቀለም ይጻፋል ። በቀይና በጥቁር ቀለምም የመስቀል ምልክትም ይደረግባቸው ነበር ። ከዚያ ሲያያዝ በመጣው አሠራርም ቤተ ክርስቲያን አሁንም ትጠቀምበታለች ። ከክርስትናው በፊትና በኋላ የበዐሉ

### መጠሪያ ስሞች

በግሪክኛው "ፔንቲኮስቲ - ኢሚራ" በዐለ ሐምሳ ፤ የመከር በዐል ፤ በዐለ ጰራቅሊጦስ እየተባለ ይጠራል ።

በተራ አነጋገር "ታላቁ እሑድ" ይባላል ። የጰንጠቆስጤ እሑድም እየተባለ ይጠራል ።

በላቲን ቋንቋም "ሮሳሊያ" ይባላል

ወደ ገጽ ፲፫ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስ ሚካኤልና ተልእኮው

ግዙፍና ረቂቅ ዓለም አለ ፤ በግዙፍ ዓለም ግዙፋን ፍጥረታት ይኖራሉ ። በረቂቁ ዓለም ደግሞ ረቂቃን ፍጥረታት ይኖራሉ ፤ እነርሱም መላእክት ናቸው፤ የመላእክት ተፈጥሮ በዕለተ እሁድ ነው ፤ ይሁን እንጂ ፍጥረተ መላእክት አንድ ጊዜ ብቻ ነው ? ወይስ በየጊዜው ይፈጠራሉ ? የሚል ጥያቄ አንዳንድ ጊዜ ይነሣል ። ታዲያ ከአንዳንድ ሊቃውንት ከእግረ መንበሩ እንደ አሸን ይፈላሉ የሚል መልስ ሲሰጥ ከሌሎቹ ደግሞ ፍጥረተ መላእክት አንድ ጊዜ በዕለተ እሁድ ብቻ ነው ያው ግን በብዛት ነው የሚል ነው ።

መላእክት ቅርጻቸው እንደሰው ሁኖ ክንፍ እንዳላቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ታውቆአል ። ኢሳ ፣ 6 ፣ 2 ፤ ራእ. 4 ፣ 8 ቅርጻቸው እንደ ሰው ይሁን እንጂ መላእክት ረቂቃን መናፍስት ናቸው ስለዚህም እንደ ሰው አይባዙም አይወልዱም አይዋለዱም ትእምርተ ተባዕት ፤ ትእምርተ እንስትም የላቸውም ግን በተባዕታይ ፆታ ይጠራሉ እንጂ በአንስታይ ፆታ አይጠሩም ።

በሌላ በኩል ደግሞ ለመላእክት ተፈጥሮ(ባሕርይ) እንደ ሰው ሁሉ ጽድቅም ኃጢአትም ይስማማዋል ማለት በነፃ ፈቃድ በነባቢ አእምሮ ተፈጥረዋል ከዚህም የተነሣ ክደውና በድለው ከክብራቸው የተዋረዱ ከመዓረጋቸው የተለዩ መላእክት እንዳሉ በመጻሕፍት ታውቋል ። መላእክት የተፈጠሩበት አላማ ለአገልግሎትና ለምስጋና ነው (ዕብ 1 ፣ 14) የተቸገረውን ይረዳሉ ያዘነውን ያጽናናሉ ለምሳሌ አጋር ከሣራ በደረሰባት ግፍና በደል ምክንያት ከቤት ወጥታ በበረሃ በችግር ላይ ሳለች የእግዚአብሔር መልአክ እንደ አጽናናትና እንደ አገለገላት በዘፍ.16 ፣ 1 - 16 ተገልጾአል ።

እንዲሁም ሕዝበ እስራኤልን ወደ ኢያሪኮ (ምድረ ርስት) በመምራት ላይ የነበረው ኢያሱ በእግዚአብሔር መልአክ እየተረዳ ጠላቶቹን ድል አድርጎአል ማድረግ የሚገባውንም መልአኩ እየነገረው እንደ መልአኩ ቃል ይሠራ ነበር ። ኢያሱ 5 ፣ 13 - 15

መላእክት ለመዓትም ለምህረትም ይላካሉ ማለት ሐዋህነት በቅንነት የሚሠሩትን በእግዚአብሔር የሚያምኑትን ይረዳሉ ከልዩ ልዩ ሥቃይ ይታደጋሉ፡ በአንጻሩ ደግሞ በትዕቢትና በጠማማነት የሚኖሩትን ለእግዚአብሔርና ለሕጉ የማይታዘዙትን ጠላቶቻቸው ድል እንዲያደርጓቸው ያደርጋሉ ፤

መላእክት እጅግ በጣም ብዙዎችና ስፍር ቁጥራቸው የማይታወቅ ሲሆኑ ጥቂቶቹ በስም ተለይተው ይታወቃሉ ፡ በስም ተለይተው ከሚታወቁት ሊቃነ መላእክት ዋነኛው ቅዱስ ሚካኤል ነው ፤

እስራኤል ከግብጽ በወጡ ጊዜ ቀን በደመና ሌሊት በእሳት ብርሃን እየመራ የመገባቸው ባሕር ከፍሎ ያሻገራቸው ሚካኤል ነው ። በዚያው ጊዜ ለእስራኤል መልአክ ምሕረት ሲሆንላቸው በግብፃውያን መልአክ መዓት ሆኖባቸዋል ። በሚካኤል ተረዳኢነት ለእስራኤል የተከፈለው ባሕር በግብፃውያን ላይ እንዲዘጋባቸውና ግብፃውያን ሰጥመው እንዲቀሩ ያደረገ የእግዚአብሔር ትእዛዝ የመልአኩ ረዳትነት ነውና ዘጸ 14 ፣ 15 - 31

እንዲሁም ሰናክሬም ሕዝቅያስን ለመውጋት አገሩን ለመውረር በተነሣ ጊዜ በሕዝቅያስ ላይ ዘበተ በእግዚአብሔር ላይ ተገዳደረ ። እግዚአብሔር ሕዝቅያስንና አገሩን ማዳንእንደማይችል ተናገረ እግዚአብሔርን ማዳን እንደማይችሉ እንደሌሎች አማልክት ቈጠረ ። በኃይሉ ብርታት በሠራዊቱ ብዛት ተመካ ፤ ሕዝቅያስ ግን በእግዚአብሔር አዳኝነት ያምን ነበርና የሰናክሬምን ተግዳሮት በሰማ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ ። "በኪሩቤል ላይ የምትቀመጥ የእስራኤል አምላክ አቤቱ አንተ ብቻህን ሰማይንና ምድርን ፈጥረሃል ። አቤቱ ጆሮህን አዘንብልና ስማ ፤ አቤቱ ዓይንህን ክፈትና እይ በሕያው አምላክ ላይ ይገዳደር ዘንድ የላከውን የሰናክሬምን ቃል ስማ ---------------------------- የምድር ነገሥታት ሁሉ አንተ ብቻ እግዚአብሔር አምላክ እንደሆንህ ያውቁ ዘንድ ከእጁ እንድታድነን እለምንሃለሁ" 2ኛ ነገ 19 ፣ 15 - 19 እግዚአብሔርም የሕዝቅያስን እምነት ፤ የሰናክሬምን ተግዳሮት ተመለከተ ። መልአኩ ሕዝቅያስን ለመታደግ ሰናክሬምን ለመበቀል ተላከ በአንዲት ሌሊት ሰማንያ አምስት ሺህ ሠራዊተ ሰናክሬምን ገደለ ሕዝቅያስን ከሞት ሀገሩን ከጥፋት አዳነ። 2ኛ ነገሥ. 19 ፣ 35

ከዚህም ሌላ በስንክሳርና በድርሳን ተጽፎ እንደሚገኘው አፍሞያን ከሰይጣን ወጥመድ እንድታመልጥ ረድቶ አታል ፤ ባሕራን የተባለውንም ሰው ከሕፃንነቱ ጀምሮ ይጠብቀውና ይረዳው ነበረ ከስጥመተ ባሕርና ከሞትም አድኖ ለታላቅ ክብር አብቅቶታል ።

የባሕራን ታሪክ እንዲህ ነው ፤ በጉርብትና የሚኖሩ ሁለት ሰዎች ነበሩ አንደኛው እግዚአብሔርን የሚፈራ ለነዳያን የሚራራ እውነተኛ ሰው ሲሆን ሁለተኛው ግን እግዚአብሔርን የማይፈራ ድሆችን የሚጠላ በሀብቱ የሚኮራ ክፉ ባለጸጋ ሰው እንደነበረ ስለ ባሕራን የተጻፈው ታሪክ ያስረዳል ።

እውነተኛው ሰው በቅዱስ ሚካኤል ስም እንግዶችን ሲቀበል ነዳያንን ሲረዳ የታረዘ ሲያለብስ የተራበ ሲመግብ የተጠማ ሲያጠጣ እየተመለከተ ያ ክፉ ባለጸጋ ይጠላውና ይመቀኘው ነበር ክፉ ወይም ደግ ቢሆኑ መቼም ሞት ለሁሉም የማይቀር ለሁሉም የሚዳረስ የተፈጥሮ ጽዋዕ ነውና ከክፉው ባለጸጋ በፊት ዕውነተኛው ሰው ሞተ ። በሕማም ላይ ሳለ ቀደም ሲል ያደርጉት የነበረው ምግባረ ሠናይ እርሱ ሲሞት እንዳይቋረጥ የተቻላትን ሁሉ እንድታደርግ ሚስቱን

ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል



## ብፁዕ ወቅዱስ ...

ከገጽ ፯ የዞረ

አብያተ ክርስቲያናቱ እህትማማቾች እንደሆኑ ሁሉ ሰዎቹም ወንድማማቾች ስለሆኑ ግራኝ ኢትዮጵያን ለመውረር ሲዘጋጅ ከኢትዮጵያ መንግሥት ተልኮ ጦር የጠየቀው ማቴዎስ የተባለ አርመን መሆኑን ጠቅሰዋል ፤ ከ፲፱፻፲፭ ጉዞ ጀምሮ ኢትዮጵያውያን የአርመን ስደተኞችን በመቀበልና በመንከባከብ ያሳዩት የወንድማማችነት ፍቅር ምንጊዜም የማይረሳ መሆኑን ጠቅሰው ቅዱስነታቸውን እንኳን ደኅና መጡ በማለት ንግግር አድርገዋል ። ቅዱስነታቸውም ስለተደረገላቸው መልካም አቀባበል በማመስገንና የሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት የነበረና የሚኖር አንድነት በማረጋገጥ ለንግግሩ መልስ ሰጥተዋል ። ከዚህ በኋላ የጉብኝቱ ፍጻሜ ሁና ቅዱስነታቸው ወደ መንበረ ሊቀ ጵጵስናው ተመልሰዋል ። በዚሁ ዕለት በ፲፩ ሰዓት ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ጽርሐ ጽዮንን ጐብኝተዋል ። ይህ ቦታ መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት የወረደበት ፤ የጸሎተ ሐሙስ በዓለ ፋሲካ ሥነ ሥርዓት የተፈጸመበት ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንዳለ«ነያ እምኪ»ሲል እመቤታችንን ለዮሐንስ አደራ በሰጠው መሠረት እመቤታችን የነበረችበት ቤተ ዮሐንስ የሚገኝበት ቅዱስ ቦታ ነው ።

ማክሰኞ መጋቢት ፴ ቀን ፺፪ ዓ/ ም

በዚሁ ቀን ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ አስቀድሞ በወጣው መርሐ ግብር መሠረት ከጥዋቱ ፫ ሰዓት እንኳን አደረስዎ ለማለት የሚመጡትን የመንግሥት ባለሥልጣናትንና የሃይማኖት መሪዎችን ፤ ሊቃነ ጳጳሳትንና የገዳማት አስተዳዳሪዎችን በመንበረ ሊቀ ጵጵስናው ሳሎን እየተቀበሉ ሲያነጋግሩ ውለዋል ።

ከሰዓት በኋላም ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በመንግሥት የፀጥታ አስከባሪዎች ታጅበው ወደቤተልሔም በአቶሞቢል ጌታ ክርስቶስ የተወለደበትን ቅዱስ ቦታ ቤተ ልሔምን የአባ አብርሃም መቃብር የሚገኝበትን ታሪካዊ ቤተ መቅደስና አብርሃም ሥላሴን በሰው አምሳል በእንግድነት የተቀበለበትን በመምሬ የሚገኘውን ታሪካዊ የወይራ ዛፍ ጐብኝተው ተመልሰዋል ። ቤተልሔምን በጐበኙበትም ወቅት በቤተ ልሔም የአርመን ሊቀ ጳጳስ የገዳሙን ማኅበር በማሰለፍ ለብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ከፍ ያለ የአክብሮት አቀባበል አድርገዋል ።

### ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ለአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ያደረጉት አፀፋዊ ጉብኝት

ረቡዕ ሚያዝያ ፩ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ/ ም/ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ቅዱስነታቸው ወደሚገኙበት መንበረ ጵጵስና እየመጡ እንኳን ደኅና መጡ በማለት መልካም ምኞታቸውን ከገለጹላቸው በኋላ ቅዱስነታቸው አጸፋውን ለመመለስ ረቡዕ ከሰዓት በፊት ወደ አርመንኳቴንና ግሪክ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ሂደው የሁለቱን አብያተ ክርስቲያናትና ፓትርያርኮች «እንኳን አደረሳችሁ» በማለት ጠይቀዋቸዋል። በመጀመሪያ የሔዱት ወደ አርመን ፓትርያርክ ነበር ።

### በአርመን መንበረ ፓትርያርክ የተደረገ ጉብኝትና አቀባበል

ቅዱስነታቸው ከመንበረ ሊቀ ጵጵስናው ተነስተው በሊቃነ ጳጳሳት ታጅበው አርመን መንበረ ፓትርያርክ ሲደርሱ የአርመን ፓትርያርክ ብፁዕ አቡነ ያሬሺ ዴድሪያን በክብር ተቀብሏቸው ። ከዚያም ሁለቱ የሃይማኖት መሪዎች ከመንበረ ፓትርያርኩ ሳሎን እንደተገኙ ቅዱስነታቸው ስለ አርመንና የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ታሪካዊ ግንኙነትና ሃይማኖታዊ አንድነት በማውሳትና እንዲሁም ስለዴር ሡልጣን ጉዳይ በመጥቀስ የሚከተለውን ንግግር አድርገዋል ።

ለአርመን ፓትርያርክ ፤

በክርስቶስ ወንድሜ ብፁዕ ወቅዱስ ያሬሽ ዴድሪያን ፓትርያርክ ዘኢየሩሳሌም ።

በቅድሚያ እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው በሰላም አደረስዎ እያልኩ በራሴና በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ስም ሰላምታ አቀርባለሁ ።

ነቢዩ ዳዊት «እመሰ ረሳእኩኪ ኢየሩሳሌም ፤ ለትርስአኒ የማንየ» መዝ ፻፴፮-፭ ያለው በኢየሩሳሌም የተፈጸመው የክርስቶስ የማዳን ሥራው በሩቅ ታይቶት ነው ። እኛ ክርስቲያኖች ግን ኢየሩሳሌምን አለመርሳት ብቻ ሳይሆን እያተንም እንጠግባትም ፤ በሐዲስ ተፈጥሮ የተገኘንባት ስለሆነች ፤ እንናፍቃታለን ።

ብፁዕ ወቅዱስ

የኢትዮጵያና የአርመን አብያተ ክርስቲያናት ምንጊዜ የሌለባቸው ፤ የሐዋርያትን ፈለግ ተከትለው ባንድነት የሚኖሩ ናቸው ። ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ እንደሆነ እኛም አንድ ነን ፤ በክርስቶስ መከፈል እንደሌለበት እኛም መካፈል የለብንም ከሁለት ዓመት በፊት የሩሲያን ቤተ ክርስቲያን በጐበኘሁበት ወቅት ኢችሚያዚን የሚገኘውን የአርመን ኦርቶዶክስ መንበረ ፓትርያርክ እንድጐበኝ ዕድል ገጥሞኝ ነበር ፤ በዚያን ጊዜ ከፓትርያርኩና ከመላው የአርመን ምእመናን የተደረገልኝ አቀባበል ለዘለዓለም የማይረሳ ነው ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፤

በዚች ቅድስት ሀገር የአርመን ቤተ ክርስቲያን ኃይል ለእሬንጋታል አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ኩራት ነው ፤ የአርመን ደስታ የሆነውን ሁሉ እንደ ራሳችን ደስታ ነው የምንመለከተው እኛም ኢትዮጵያውያን ቅዱስነትዎ በታሪክ እንደሚያውቁት በዚህ ቅዱስ ቦታ ረዥም ጊዜ አለን ፤ ምንም እንኳ ከሀገር ርቀት የተነሣ በመጓጓዣም እጥረት በሌላም አንዳንድ ችግር ምክንያት ይዞታችንን በሚገባ ለማስከበር ባንችልም ተስፋ ባለመቁረጥና በትግሥት ከዚህ ቅዱስ ቦታ እስካሁን አልተለየንም ፤ ወደፊትም አንለይም፤ አንዳንድ ክርስቲያኖች ለምን አየናቸው በማለት እኛን ከዚህ ከቅዱስ ቦታ ነቅለው ለመጣል ብዙ መከራ ያደርጋሉ ።

ይህ ድርጊት ቢያሳዝነንም እኛ እነሱ በሚሔዱበት መንገድ ሳይሆን በፍቅርና በትሕትና እንመለከታቸዋለን ። የአርመን ቤተ ክርስቲያንም ለሁላችን የጋራ ስለሆነች ይህን ችግር በዝምታ የምትመለከተው አይመስለኝም ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፤

ለዚች አሁን ላለንባት ቦታ ብዙ መስዋዕትነት ከፍለንባታል ፤ አባቶቻችን ከኢትዮጵያ ተነስተው እዚህ ድረስ በእግር የሚጓዙት ሁለት ወርና ሦስት ወር ነበር ፤ ለዚያውም በበረሃው ረግፈው ሲቀሩ የሚደርሱት ግን ከመቶ ሁለት ብቻ ነበሩ ፤ መጥተውም የአየሩን ጠባይ ስለማይለምዱት ቶሎ ይሞቱ ነበር ፤ ዛሬ ግን የመጓጓዣ ችግር ስለሌለ የመከራው ጊዜ አልፏል ። በዚህ አጋጣሚ ለቅዱስነትዎ የማስታውሰው ሲሆን ከዚህ ቅዱስ ቦታ የምትገኙ መላው ክርስቲያን ፤ በተለይ ደግሞ የእሬንጋታል አብያተ ክርስቲያናት ተጠሪዎች ስብሰባ እያደረጋችሁ የራሳችሁን ችግር በራሳችሁ ብትፈቱት መልካም መስሎ ይታየኛል ።

ለቅዱስነትዎ ሙሉ ጤንነት ፤ ለአርመን ቤተ ክርስቲያንና ሕዝብ ፍቅርና አንድነት እንዲሰጥልን እግዚአብሔርን እንለምናለን ።

በራሴና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ስም የፍቅር ምልክት የምትሆን ይህችን አነስተኛ ስጦታ ለቅዱስነትዎ ሳበረክት ደስታ ይሰማኛል ።

ከንግግሩ በኋላ ቅዱስነታቸው ለብፁዕ ወቅዱስ የአርመን ፓትርያርክና ለሁለት ሊቃነ ጳጳሳት የመታሰቢያ ስጦታ አደረጉ ። ለፓትርያርኩ የተበረከተው ስጦታ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ሥልጣኔና ታሪክ የሚገልጽ ከእንጨት የተሠራ የአክሱም ሐውልት ቅርጽና እንዲሁም መዳይ ከነዕጣኑ ሲሆን ለሌሎቹ ለሁለት የአርመን ሊቃነ ጳጳሳት ደግሞ ከእንጨት የተቀረፀ ትልልቅ የጳጳሳት የእንጨት መስቀልና የብር የእጅ መስቀል ነበር ።

ከንግግሩና ከስጦታው በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ የአርመን ፓትርያርክ ስለተደረገላቸው ስጦታ በማመስገንና እንዲሁም ስለ ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት አንድነት በመጥቀስ የመልስ ንግግር ካደረጉ በኋላ የለስላሳ መጠጥ ግብዣ ተደርጐ በዚያ የሚደረገው ሥነ ሥርዓት ፍጻሜ ሆነ ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ከአርመን ፓትርያርክ ቀጥሎ ያጋዙት የግሪኩን ፓትርያርክ ነበር የግሪክ ፓትርያርክ በመንበረ ፓትርያርክ ናቸው «እንኳን አደረሰዎ» በማለት አጸፋውን ለመመለስ ከመንበረ ፓትርያርኩ ሲደርሱ የግሪኩ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ያዕቆብ ቢንቲሪቴ በክብር ተቀብሏቸው ። ሁለቱም ፓትርያርኮች በመንበረ ፓትርያርኩ ሳሎን እንደተገኙ ብፁዕ ወቅዱስነታቸው ስለተደረገላቸው መልካም አቀባበል በማመስገንና ስለዴር ሡልጣንም ጉዳይ በመጥቀስ ንግግር አደረጉ ።

### የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ንግግር ሙሉ ቃል

በክርስቶስ ወንድሜ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ያዕቆብ ቢንቲሪቴ ከሁሉ አስቀድሜ በትንሣኤው ሰላምታ እንኳን ) ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሰዎ እላለሁ።

ነቢዩ ዳዊት « ናሁ መናይ ወናሁ አዳም ሶበ ይሄልዉ አኃው ኅቡረ » ብሎ እንደተናገረ ( መዝሙር ፻፴፪ የትንሣኤን በዓል ከናንተ ከወንድሞቼ ጋር በማክበሬ ከምንጊዜም የበለጠ ደስታ ይሰማኛል ።

ይህች የሰላም ከተማ ኢየሩሳሌም ክርስቶስ የማዳን ሥራውን ያከናወነባት ፤ በክርስቶስ ደም የተቀደሰች ታላቅ ከተማ ናት ። ብዙ ጊዜ መከራ ቢደርስባትም ሃይማኖታዊ ቅርሷ አልተለወጠም፤ ክርስቲያኖችም ተለይተዋት አያውቁም ፤ ከነዚህም መካከል ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ይገኙባቸው እንደነበር በ፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኢየሩሳሌም የነበረው የላቲን ቤተ ክርስቲያን አባት ጄሮኒሞስ ጽፏል ።

ይህም የጄሮኒሞስ የምስክርነት ቃል ለእኛ ለኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ታላቅ ኩራት ነው ፤ ምንም እንኳ እንደዚህ እንደዛሬ መጓጓዣ ባይኖርም አባቶቻችን በበረሀ ሁለት ወር ሦስት ወር እየተጓዙ እየመጡ ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር በመተባበር ቅዱሱን ቦታ በመጠበቅ በኩል የበኩላቸውን ድርሻ ሲያበረክቱ ኖረዋል ። ወደፊትም ይኖራሉ ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፤

ቤተ ክርስቲያን የሰላም ቤት ናት ሰላም የሚገኘውም ፍትሕና እኩልነት ሲኖር ብቻ ነው ። ይሁን ያላወቁ አንዳንድ ሰዎች ያገኑታችንን ምልክት ክርስቶስን የመሰያ ምልክት አድርገው ቤተ ክርስቲያንን ሰላም አሳጥተዋት ኖረዋል ። ዛሬ በቤተ ክርስቲያን በመጠኑም ቢሆን ሰላም አለ ሊባል ይቻላል ፤ ክርስቲያኖች ይረዳዳሉ ፤ ይጠያየቃሉ ። ወደ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መለስ ብለን ብንመለከት ግን በቤተ ክርስቲያን ብዙ አሳዛኝ ድራማ ይታይባት ነበር ፤ የርስ በርስ ስም መጠፋፋት ነበር ፤ ለወገን ለጎሳ በማድላት ሃይማኖት ለበስ የሥልጣን ሽሚያ ነበር ፤



www.ethiopianorthodox.org

ይህም የክርስቲያኖች የርስ በርስ ጠብ ለነግን እንዳሙቻ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ መዝግቦታል ።

እግዚአብሔር ይመስገን ዛሬ ይኸ ሁሉ የለም ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከአፍሪካ መጀመሪያይቱ ስት ሆን በየጊዜው ከውጭ በሚደረግባት ወረራ የክርስትናን ትምህርት ለመላው አፍሪካ ለማዳረስ አልቻለችም፤ ምኞቷን በሥራ ለመግለጥ ቀቲትቢያ ዳገታትም አፍሪካውያን ወንድሞችን ወደ ክርስቶስ መንጋ ለማስገባት ከባድ ኃላፊነት ያለባት መሆኗ ይሰማታል።

እኛ ኢትዮጵያውያን ካባት በወረደው ባህላችን እንግዳ መቀበልን እንወዳለን ፤ ሰውን እናከብራለን ። በሃይማኖታችን ላይ የሚዘምተውን ግንእን ታገሰውም ።

ስለዚህ ነው የማንም ተፅዕኖ ሳይኖርብን ሃይማኖታችንንና ሥርዓታችንን ጠብቀን የምንኖረው ።

በዚህ በቅዱስ ቦታ የሚኖሩ ወንድሞቻችን ስለ ትድስናዎ ደግነት እና ትህትና በሰፊው ገልጠው ነግረውናል ፤ እኔም የሰማሁትን ሁሉ ባይኔ በማየቴ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ ።

ነዚህ አጋጣሚ ትድስናዎን የምለው ለርግው ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት አቡነ ዮሐንስ ጳውሎስ ፪ኛ ልባዊየሆነ የወንድምነት ሰላምታ እንዲያቀርቡልኝ ነው ።

ለቅዱስነትዎ ሙሉ ጤንነት እንዲሁም ለመላው ሕዝብ ፍቅርና አንድነት እንዲሰጥልን የቤተ ክርስቲያን አምላክ ፈቃዱ ይሁን ።

አባ ተክለ ሃይማኖት

ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ።

በራሴና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ስም ይህችን አነስተኛ ስጦታ ለቅዱስነትዎ ሳበረክት ደስታ ይሰማኛል።

ከንግግሩ ፍጻሜ በኋላ ቅዱስነታቸው ለላቲኑ ፓትርያርክ ከእንጨት የተሠራ ትልቅ የጠረጴዛ መስቀልና ሙዳይ ከነዕጣኑ ፤ ለረዳቱ ጳጳስ ደግሞ ከእንጨት የተቀረፀ የእንገት ዕፀመስቀል ስጦታ አደረጉ ። ከንግግሩና ከስጦታውም በኋላ የላቲኑ ፓትርያርክ ስለተደረገው ስጦታ በማመስገን የመልስ ንግግር አደረጉ ። ከዚህ በኋላ በዚያ የሚደረገው ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞ መልስ ሆነ ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በተመሳሳይ ሁኔታ ወደ ግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ በመሔድ ብፁዕ አቡነ ቬኒዲክቶስን እንኳን አደረስዎ በማለት ጠይቀዋል። ቅዱስነታቸው ከመንበረ ፓትርያርኩ እንደደረሱ ብፁዕ አቡነ ቬኒዲክቶስ በየኢየሩሳሌም የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የክብር አቀባበል አደረጉላቸው ።

ሁለቱ ፓትርያርኮች በመንበረ ፓትርያርኩ ሳሉን እንዳረፉ ቅዱስነታቸው ስለክግሪክና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መልካም ግንኙነትና ስለ ደርሡልጣንም ጉዳይ በመጥቀስ የሚከተለውን ንግግር አደረጉ ።

ለግሪክ ፓትርያርክ ፤

በክርስቶስ ወንድሜ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቬኔዲክቶስ ፤

ፓትርያርክ ዘኢየሩሳሌም ፤

ብፁዕ ወቅዱስ ፤ ከሁሉ አስቀድሜ እንኳን ለብርሃን ትንሣኤው አደረስዎ እላለሁ ። «ወንሰግድ ውስተ መካነ ኀበ ቆመ እግረ እግዚእነ» መዝ ፻፴፩ ፯ ብሎ ዳዊት እንደተናገረው ፤ የዓለም ክርስቲያኖች ሁሉ ወደዚች ቦታ እየመጡ በክርስቶስ መስቀል ፊት ይሰግዳሉ ፤ ከነዚህም አንዱ እኔ ነኝ ።

ብፁዕ ወቅዱስ፤ ምንም እንኳ ብዙ ፀዋትወ መከራ በየጊዜው ቢደርስባችሁም ከቅዱስ መቃብሩ እንለይም ብላችሁ በመቆየታችሁ ፤ ትእግሥታችሁ የሚያስመሰግን ነው ። ስለዚህም እኛ እናንተን የምንመለከታችሁ በትንሣኤ ሌሊት በዚህ መቃብር ራስ ጌና ግርጌ ተቀምጠው እንደታዩት መላእክት ነው ። እነዚያ መላእክት የክርስቶስን ትንሣኤ እንዳበሠሩ እናንተም ባለማቋረጥ በመቃብሩ አጠገብ ቆማችሁ «ክርስቶስ ተንሥቷል» እያላችሁ ስትመሰክሩ ትኖራላችሁ ።ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ጥርጣሬና ፍርሃት የሚያሲታየውንም ዓለም እይዞህ አትፍራ አትጠራጠር ክርስቶስ ተንሥቷል እያላችሁ ስታጽናኑት ትኖራላችሁ ። ይህም ታላቅ የሐዋርያት ተግባር ነው ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፤

በዚህ በቅዱስ መቃብር ዙሪያ ከሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት አንዷ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ናት ፤ በዚህ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መነኮሳትና መነኮሳይያት እንዲሁም ምዕመናን ከወንድሞቻቸው ክርስቲያኖች ጋር በመግባባትና በመተባበር በናንተ በክርስቲያን ወንድሞቻቸው ርዳታ ችግራቸውን እንደሚወጡት ተስፋ እናደርጋለን ።

የኢትዮጵያና የግሪክ ሕዝብ ነፃነት ምን እንደሆነ ስለሚያውቅ በሃይማኖትም በፖለቲካም የባዕድ ቀንበር መሸከም አይወድም ። ስለዚህ ነው ከግሪኮች ጋር ብዙ የመንፈስ ዝምድና ያለን፤ የኢትዮጵያና የግሪክ ሕዝቦች በመከራም ጊዜ አይለያዩም ።

የኢጣሊያ ፋሽስት ኢትዮጵያን በግፍ በወረረ ጊዜ በኢትዮጵያ የሚኖሩ እያሉ ግሪኮች ከኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸው ጋር አምስት ዓመት ሙሉ በበረሀ በአርበኝነት እንደቆዩ እናውቃለን።በሀገራችን አነጋገር «ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጐረቤት» እንደሚባለው እዚህ ለሚኖሩ ወንድሞቻችን ኢትዮጵያውያን ከኛ ይልቅ የምትቀርቧቸው እናንተ ናችሁ ፤ በክርስቲያኖች መካከል አለመግባባት ቢፈጠርም በቤተሰብ ዓይን መታየት አለበት ፤ እኛ ክርስቲያኖች በመካከላችን የሚፈጠረውን ማናቸውንም ችግር በስምምነት ለመፍታት ካልሞከርን ለሌሎች መጎቲያ መሆናችንን ማወቅ አለብን ።

ለክርስቶስ መመስገኛ እንጂ መሰደቢያ እንዳንሆን ጥንቃቄ ያስፈልገናል ። ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሁና ሰውና እግዚአብሔርን ሰውና ሰውን ባስታረቀባት ከተማ አስታራቂ ጠፍቶ ክርስቲያኖች ርስ በርሳቸው ሲጣሉ ማየት አሳዛኝ ነው ፤ አሁንም ብፁዕነትዎ እየመከረና እየተቆጣ በክርስቲያኖች መካከል ጠብ እንዳይፈጠር ቢያደርግና ቢያስታርቅ በደሙ የዋጀት የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሰላም የሰፈነባት ትሆናለች ።

ለብፁዕነትዎ ጤንነት ፤ ለመላውም ዓለም ፍቅርና ሰላም እንዲሰጠልን የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን ።

አባ ተክለ ሃይማኖት

ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ

በራሴና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ስም የፍቅር ምልክት ይህችን አነስተኛ ስጦታ ለብፁዕነትዎ ሳበረክት ደስታ ይሰማኛል ።

ከንግግሩ ፍጻሜ በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ለብፁዕ አቡነ ቬኒዲክትስ የአክሱም ሐውልት ቅርጽ ያለው ከእንጨት የተሠራ ስጦታ አደረጉላቸው የጉልጉታገበዝ ለሆኑት ጳጳስ ደግሞ ከእንጨት የተቀረፀ የጳጳስ የእንገት መስቀል ስጦታ አድርገውላቸዋል ። ከስጦታው በኋላ ብፁዕ አቡነ ቬኒዲክትስ ስለተደረገላቸው ስጦታ በማመስገን የመልስ ንግግር አደረጉ። ከዚህ በኋላ በዚያ የሚደረገው ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞ መልስ ሆነ ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በዚህ ዕለት (ሚያዝያ ፩ ቀንና ሚያዝያ ፪ ቀን ፫፪ ዓ ም) በተከታታይ የእሥራኤልን ፕሬዚዳንት ክቡር ሚስተርይስሐቅ ሾናንን የሀገር አስተዳደርና የፖሊስ ሚኒስትሩን ክቡር አቶ ዮሴፍ አርን አቡሀሲርን የኢየሩሳሌምን ከተማ ከንቲባ አቶ ቴዲፖሊክን በየጽሕፈት ቤታቸውአ ነ ጋ ግ ረ ዋ ል ። የእሥራኤል ተራ ካህናት ( ችፍ ረባይ) ዮሴፍአሻአብድይ ንም ተቀብለው አነጋግረዋል።ብፁዕ ወቅዱስነታቸው ክቡር ፕሬዚዴንቱንም ሆነ ሌሎችን ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት ባነጋገሩበት ጊዜ የክብር አቀባበል አድርገውላቸዋል ። በንግግሩም ወቅት ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም የረጅም ጊዜ ታሪክና ይዞታ ያላትመሆኗን በመግለጽ ስለዴር ሡልጣን ጉዳይ አንስተውበሰፊውተወያይተዋል ።

በዚህም ጊዜ ከባለሥልጣኖቹ የተነገረው ቃል ስለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያላቸውን ከፍተኛ ግምትና በሁለቱ ሕዝቦች መካከል የነበረውና ያለው ጥንታዊና ታሪካዊ ግንኙነት ወደ ፊት እንደሚቀጥል ያላቸውን ጽኑ እምነት የሚገልጽ ከመሆኑም በላይ ስለ ዴርሡልጣን ጉዳይ የሚታየውም ሁኔታ የእሥራኤል መንግሥት የዴር ሡልጣንን ጉዳይ የሚመለከተው ከፍትሕ አንጻር መሆኑን የሚያረጋግጥ ነበር ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዴር ሡልጣን ላይያላት ይዞታ በታሪክም በማስረጃም የተረጋገጠ ስለሆነ ምን ጊዜም የይዞታዋ ባለቤት ሁና እንደምትኖር የኢትዮጵያውያን ሁሉ ጽኑ እምነት ነው

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ባለሥልጣኖቹን ባነጋገሩበት ወቅት የሊቃነ ጳጳሳቱና የጳጳሳቱ ልዑካን ከመገኘታቸውም በላይ ስለ ቅዱስነታቸውክብር የለስላሳ መጠጥ ግብዣ ተደርጓል ።

በንግግሩ መጨረሻ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ለባለሥልጣኖቹ የመታሰቢያ ስጦታ አድርገዋል ። ክቡር የእሥራኤል ፕሬዚዳንትና ሌሎቹም የመንግሥት ባለሥልጣኖች በበኩላቸው ለቅዱስነታቸው የመታሰቢያ ስጦታዎችን አበርክተዋል ። ቅዱስነታቸው በተለይ የእሥራኤልን ሊቀ ካህናት ባነጋገሩበት ወቅት አንድ የግዕዝ ብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ስጦታ ያደረጉላቸው ሲሆን ረቢውም በበኩላቸው የዕብነ በረድ ገበታ ያለው በዕብራይስጥቋንቋ የተጻፈ አንድ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ለብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ አበርክተዋል ።

የእሥራኤል የሃይማኖት ሚኒስትር ዳይሬክተር ጄኔራል ሚስቴር ሊፐል የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩን የኢየሩሳሌም ጉብኝት ምክንያት በማድረግ በዚሁ ቀን ማታ በፐላዛ ሆቴል የእራት ግብዣ አድርገዋል ። በግብዣውም ላይ የአርመን ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክና ሌሎችም የሃይማኖት መሪዎች የመንግሥት ባለሥልጣኖችና የውጭ ሀገር መንግሥታት ቆንሲሎች እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው ሌሎች የክብር እንግዶች ተገኝተዋል ። በግብዣውም ላይ ዳይሬክተር ጄኔራሉ ስለ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ የኢየሩሳሌም ጉብኝት የተሰማቸውን ደስታ በመግለጽ ንግግር አድርገዋል ። ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩም ስለተደረገላቸው መልካም አቀባበል የተሰማቸውን ደስታ በመግለጽ ለንግግሩ መልስ ሰጥተዋል ። በመጨረሻም ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ለዳይሬክተር ጄኔራሉ የመታሰቢያ ስጦታ ያደረጉ ሲሆን ፤ ዳይሬክተር ጄኔራሉም በበኩላቸው ለብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ የመታሰቢያ ስጦታ አበርክተውበዚያ የሚደረገው ሥነ ሥርዓት ፍጻሜ ሁኗል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ከቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ሆነ ከመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር ያደረጉት ውይይት በወዳጅነት መንፈስ የተካሔደና የነበረውንም ታሪካዊ ግንኙነት እንደገና የሚያድስ በመሆኑ የታየው ሁኔታ በጠቅላላ ጉብኝቱን ፍሬያማ አድርጉታል ።

ብፁዕ ወቅዱስነታቸው ከአብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ከመንግሥት

ወደ ገጽ ፲፯ ዞሯል



# የሴቶች ዓምድ

## ወይዘሪትዋ የቅኔ መምህር

ሴቶች በመንፈሳዊ ተግባር ሲሠለጥኑ ዕድገታቸውም በሃይማኖት ፤ በምግባር ሊሆን ይገባል ብለው የሚያምኑ ብዙ አገሮች ስለ ክርስትና ሃይማኖትም ሆነ ስለ ቤተ ክርስቲያናቸው ሥነ ሥርዓት (ሕግጋት) ያለ ምንም የጾታ ልዩነት ያሰለጥኗቸዋል ። ከዚህም የተነሣ

እንደየችሎታቸው ከወንድሞቻቸው እኩል በሥራ ቦታ ተመድበው ይሠራሉ በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ የሥራው ሁሉ ተካፋይ ይሆናሉ ።

በሃገራችን ግን ምንም እንኳ ሴቶች በሃይማኖታዊ ሥነ ምግባር ቢሰለጥኑና ቢያውቁ እስከ ዛሬ ድረስ ሴቶች ከሴትነት ማለትም ከማጀት ሥራቸው አልፈው በቤተ ክርስቲያን ሥራ ከወንዶች እኩል በሰለጠኑት ሥራ ተሰማርተው ቤተ ክርስቲያናቸውን አያገለግሉም ነበር ። እስከነ ተረቱ "ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ" እየተባለ ይተረት ነበር ።

እዚህ ላይ እርግጥ የማንክደው ነገር አለ ይኸውም በጣት የሚቆጠሩ ለዚያውም እፍቅሮተ ቤተ ክርስቲያን -አፍቅሮተ ትምህርት) ያላቸው እናቶች ጾታቸውን በመደበቅ ሴቶቹ እንደወንዶች ሱሪ በመታጠቅ ስማቸውን በመለወጥ የተማሩ ሴቶች ማለትም እንደነ መምህርት ወ/ሮ ኢየሩሳሌም ያሉት ድጓ ፤ ቅኔ ፤ መዝገበ ቅዳሴና የመሳሰሉትን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በመማር ዛሬ የመዝገበ ቅዳሴ መምህርት የሆኑትና ከአባታቸው በመማር የታወቁት የቅኔ መምህርት እንደ እነማሆይ ገላነሽ ያሉት በመብራት ፍለጋ ይገኙ ይሆናል ። ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያናችን ክርስቶስ ከትምህርቱ እንዳለያቸው ሁሉ እርሷም ያለ ፆታ ልዩነት እርእያውን ተከትላ አላስተማረችም ነበር ፤

ዛሬ ግን ጊዜው እየተሻሻለ ሲሄድ ሴቶችም እንደወንዶች በታወቀው መንፈሳውያን ትምህርት ቤቶች ገብተው መማር ተፈትኖ ዲኖቻቸው ይኸውና ለጊዜው አንዲት ወጣት ወይዘሪት ገብታ በመማር ላይ ትገኛለች ።

ስለዚህ በዛሬው አምዳችን በአክሱም ከተማ በሚገኘው ቅ/ያሬድ አዳሪ መንፈሳዊ ት/ቤት ገብታ ትምህርቷን የምትከታተለውን የወ/ት መብራት ዘሪሁን አጭር ታሪክ የመጀመሪያውን ክፍል እናቀርብላችኋለን ። በቅድሚያ ግን ታሪኳን ተከታትለው የላኩልንን መሪ ጌታ ኃይለሚካኤል ፀዳለ ማርያምን በአንባቢያን ስም እናመሰግናለን ።

በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያየ ሊቅነት ያላቸው ብዙ ሊቃውንት ሴቶች እንደነበሩ የሚታወቅ ነው ። በይበልጥ በቅኔ በኩል በርከት ያሉ ምሁራን እንደነበሩና አሁንም እንዳሉ እንረዳለን ።



የቅኔ መምህርዋ ወ/ት መብራት ዘሪሁን

በአሁኑ ጊዜ ካሉን ሊቃውንት ሴቶች መካከል ወይዘሪት መብራት ዘሪሁን ትገኝበታለች ። ወይዘሪት መብራት ዘሪሁን በ1947 ዓ.ም. ከአባትዋ ከዓይነ ማህበር ዘሪሁን ወ ዮሐንስ ከእናቷ ከወሮ እቴነሽ ፍስሐ በአክሱም ከተማ ተወለደች ገና 3 ዓመት ሳይሞላት በደረሰባት የዓይን ህመም ምክንያት ዓይንዋ ታወረ አብዛኛውን ጊዜ ሰውን የሚጐዳው ኡረተ-ልብ እንጂ ዑረተ-ዓይን አይደለምና ዕድሜዋ ለአቅመ ትምህርት ሲደርስ ከጥንታዊው የአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን በስተምሥራቅ ሆነው ከሚያስተምሩ ባህታዊ መምህር ፍሥሐ ኤልሳዕ ገብታ ትምህርትዋን ጀመረች ከእኚሁ መምህር ፦

1. ዳዊት

2. ውዳሴ ማርያምና መልክአ መልክአ

3. 5ቱ አእማደ ምሥጢር ተምራለች ቀጥሎም ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ባሰሩት መንፈሳዊ አዳሪ ት/ቤት ገብታ መ/ተ/ሃይማኖት አበበ ከሚባሉ የቅዳሴ መምህር ቅዳሴን ተምራለች ።

ከዚህ በኋላ የትምህርት ፍላጎትዋ ከፍ እያለ ዕውቀትዋ እየዳበረ በመሄዱ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ካወቁ በኋላ ከአዳሪ ቤቱ ገብታ እንድትማር በማድረግ አስፈላጊውን ሁሉ ካሟሉላትና በዚሁ ቅዱስ ያሬድ ት/ቤት ከሚገኙት ከታላቁ የመጻሕፍት ሀዲሳት የመጻሕፍት ብሉያትና ቅኔ መ/ር ከሆኑት ከመ/ር ገ/ጊዮርጊስ ገ እግዚአብሔር ዘንድ ቅኔ ጀመረች ወይዘሪትዋ ባላት የተፈጥሮ ብሩህ አእምሮ ቅኔውን ያለምንም ችግር ተያያዘች ማለት በሚገባ ተከታተለችው።ቅኔ

ቤት በገባች ልክ በ2 ዓመት ተቀኝታለች ። የተቀኘችው በቅኔ ማህሌት አይደለም ። በቆየው ልማድ መሠረት መምህርዋ እንግዲህ ተቀኚተሻል ባልዋት መሠረት ባደረገችው የቅኔ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት ነው እንጂ በቅኔ ማህሌት ላይ ብትቀኝ ኑሮ የቱን ያህል ያስደስት ነበር ? አሁንም ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ትምህርት ብቁ የሆኑትን ሴቶች በማኅሌት "ቅኔ እንዲቀኙ አብረው መዝሙር እንዲዘምሩ ለማድረግ ይቻል ዘንድ አንድ ውሳኔ አስተላልፋ የባለሞያዎችን ሴቶች መብት ብትጠብቅ ብዙ ተከታይ እንደምታገኝ ግልጽ ነው ።

ምን ያህልም የመማር የማወቅ ፍላጎት በሴሎች ዘንድ ያሳድር ነበር አሁንም ቢሆን ወደ ፊት ቢታሰብበት መልካም ነው ። ወደ ታሪኩ እንመለስና ወይዘሪት መብራት ቅኔውን እንደተቀ

ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org


# ዜና አብያተ ክርስቲያናት

**የኮፈሌ ቅዱስ ገብርኤል ቤት ክርስቲያን ታደሰ**

**አርሲ**

በአርሲ ክፍለ ሀገር በጭላሎ አውራጃ የኮፈሌ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በጊዜ ብዛት እድሣት ሳያገኝ ይኖር ስለነበረ ሰበካ ጉባኤ ከተቋቋመ ከ1968 ዓ.ም. ወዲህ ሕዝበ ክርስቲያኑ እራሱን ችሎ ቤተ ክርስቲያኑን እንዲያስተዳድር የተሰጠውን መብት አውቆ የቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ከውስጥና ከውጭ የተጓደሉትን አሟልቶ ከነአጥሩ አድሶ ምዕመናኑና አንዳንድ ግለሰቦች ከፍተኛ ገንዘብ በማውጣት መታደሱን የሰበካ ጉባኤው ገለጸ ።

እንዲሁም በሰበካው ጉባኤ አስተባባሪነትና ጥረት በየበአላቱ ምእመናኑ ተሰብስበው የስብከተ ወንጌል ትምህርት የሚሰጥበትና የሰበካው ጉባኤ ጽ/ ቤት የክርስትና ማስነሻ እነዚህን አቅፎ የሚይዝ ከፍተኛ አዳራሽ ለማሰራት በመንፈሳዊ ቆራጥነት ተነስቶ የሰበካው ጉባኤ ምእመናኑን በማስተባበር ገንዘቡንና ጉልበቱን በአጠቃላይ ብር 8586 (ስምንት ሺህ አምስት መቶ ሰማንያ ስድስት ብር) የፈጀ ቤት ተሰርቶ በመጠናቀቁ በከፍተኛ አገልግሎት ላይ መገኘቱንም የሰበካው ጉባኤ ም/ሊቀ መንበር ባላምባራስ በቀለ ደንበለው ጨምረው ገልጸዋል ።



የኮፈሌ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን

**ሸዋ**

**በዝዋይ 49 ካህናት ሠለጠኑ**

በዝዋይ ካህናት ማሰልጠኛ ውስጥ ለ3ኛ ጊዜ በሙያ ማሻሻያ ኮርስ የሰለጠኑ 49 ካህናት መጋቢት 20 ቀን 1972 ዓ.ም. የምስክር ወረቃታቸውን ከብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ እጅ ተቀብለዋል ።

**ጐንደር**

— አቶ ተስፋዬ ብዙአየሁ በጎንደር ከተማ ለደብረ መንክራት ቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ከ4807 (አራት ሽ ስምንት መቶ ሰባት) ብር በላይ የፈጀ የድምፅ ማጉያ ገዝተው የሰጡ መሆናቸውን መልአከ ገነት ዮሐንስ አምባው በላኩት ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል ።

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ የምስክር ወረቀት ሰጡ

**መቂ**

የኢሉባቦር ሀገረስብከት ጳጳስ ለ3ኛ ጊዜ በአንድ ወር የሙያ ማሻሻያ ኮርስ ለሰለጠኑ ካህናት መጋቢት 19 ቀን 72 ዓ.ም. የምስክር ወረቀት መስጠታቸውን የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት አስታወቀ ።

**ሎንዶን**

ጂም ፓትስ የተባሉ እንግሊዛዊ የመገናኛ ዘዴዎች አማካሪና የፊልም አዘጋጅ ስለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ መስቀሎችና ስለ አሠራራቸውም የሚገልጽ ባለ 16 ሜትር 24 ደቂቃ የሚፈጅ ባለ ቀለም ጥናታዊ ፊልም አዘጋጅተው አወጡ ።

ፊልሙም በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ መስቀሎች እንዴት እንደሚሠሩ ያሳያል ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትገለገልባቸው ልዩ ልዩ ቅርጽ ያላቸው መስቀሎች ከፍተኛ ቅርሶች ከመሆናቸውም ሌላ የምዕራቡ ዓለም እንዲያውቃቸው ለማድረግና ፡ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ተከታዮች ሁሉ እህት ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምባቸውን የመስቀሎች ዓይነትና ቅርጽ እንዲያውቁትና እንዲጠቀሙበት አዘጋጅተው ምክራቸውን ለግሰዋል ።

የዚህም ፊልም ድምፅ ከእንግሊዝኛና ከአረብኛ ሌላ በተለያዩ ቋንቋዎች እንደተዘጋጀና የፊልሙም ዋጋ ከአንድ ሽህ አንድ መቶ የኢትዮጵያ ብር በላይ እንደሚያወጣ የዓለም ክርስቲያናዊ የመገናኛ ዘዴዎች ማኅበር በ49ኛው ቁጥር ገለጸ ።

**ጀኔቭ**

ጥቂት አብያተ ክርስቲያናት የሰንበት ትምህርት ቤት እንደ ኢ.ዘ.አ. በ1780 ዓ.ም.አቋቁመው ነበር። ይህም ት/ቤት በዓለም ሁሉ ተሰራጭቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ መሆኑ ተገልጧል ።

ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



# በዓለ ሃምሳ

ከገጽ ፯ የዞረ

**ይህም የጽጌረዳ (የአበባዎች) በዐል ማለት ነው ይላሉ ፤ ምክንያቱም በሌሎቹ ክፍላተ ዓለም ይህ በዐል የሚውልበት ጊዜ በእኛ ሀገር እንደ መስከረም ወር የአበባዎች ጊዜ በመሆኑ በዚህ ዕለት ምእመናን ወደየቤተ ክርስቲያኑ የሚሄዱት በበለጠ አበባዎችን በመያዝ ሆኖ በመገኘቱ ይመስላል ። የሳምንታት በዐልም እየተባለ ይጠራል ፤ ምክንቱም እሑድ በክርስትና ሕይወት የሳምንቱ በዐል በመሆኑ ነው ። መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት (ለሐዋርያት) የወረደበት ዕለትም ይባላል ። ነጩ ወይንም ጸአዳው እሑድና የመሳሰሉት የበዐሉ መጠሪያዎች ናቸው ።**

**የበዐሉ አቋም ፤ በአይሁድ አፈጻጸም**

የዚህ በዓል አመጣጥ ረዘም ያለ የታሪክ ጉዞ ያለው በመሆኑ ከሙሴ መጻሕፍትና ከሌሎቹም መረዳት እንችላለን ።

ይህ በዐል ከፋሲካ በዐል በኋላ በሐምሳኛው ዕለት በአይሁድ የሚከበር መንፈሳዊ በዐል ነበር ። በበዐሉም ቀን ለፍሬው በኩራት መታሰቢያ የሚሆን (የሆነ) ያልቦካ የፓስካል ቂጣ በእግዚአብሔር ፊት ይቀርብ ነበር ። በዚህም በዐል አይሁድ ወላጆች የሌሉአቸውን ሕፃናት ፤ መበለቶችን ፤ መጻተኞችንና ሌዋውያንን እንዲያስቡ ይነገራቸው ነበር ። (ኦሪት ዘዳግም 16. 9 - 12 ፤ ኦሪት ዘፀአት 34.22)

ይህ በዐል የመከር መጀመሪያ ስለሆነ ፤ የፍሬው በኩር ለእግዚአብሔር ይቀርብ ነበር ። በዚህ ደንብ መሠረትም የፋሲካ በዐል በዋለ በሐምሳኛው ዕለት ስለአዝመራ ወይንም ስለ መከር ውጤት ለመጀመሪያ ጊዜ ሕግ የተሰጠበትን መነሻ በማድረግ በኢየሩሳሌም የነበሩ አይሁድና ሌሎችም በኢየሩሳሌም እየተሰበሰቡ እጅግ በጣም የደመቀ መንፈሳዊ የሆነ ዓመታዊ በዐላቸውን ያከብሩ እንደነበር የሙሴ መጻሕፍት ይነግሩናል ።

በሌላ በኩል ደግሞ በተጨማሪ ይህ ዕለት ሙሴ ከእግዚአብሔር ሕግን ለመቀበሉ የመታሰቢያ ቀን በመሆኑም ይነገራል ።

**ትንቢቱ እንዴት ተፈጸመ**

አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች በዚያው በብሉይ ኪዳኑ ዘመን ፍጻሜ ሲያገኙ (የአይሁድ ምርኮ ኤርምያስ 9.8 -11) ብዙዎቹ ደግሞ የተፈጸሙት ሁለተኛው አካል ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ፍጹም ሰው ሆኖ ከቅድስት ድንግል ማርያም በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ ሲሆን (ኢሳ. 7. 14) ሌሎችም ስለዳግም ምጽአቱና ስለመሳሰሉት የሚያመለክቱ ገና ያልተፈጸሙ ይገኛሉ (ኢሳ. 35 ፤ 1 - 8)

እግዚአብሔር በነቢዩ አፍ “መንፈሴን በውስጣችሁ አኖራለሁ በትእዛዜም አስኬዳችኋለሁ” ይላል (ሕዝቅኤል 36. 27)

በሌላ በኩልም “ከዚህ በኋላ እንዲህ ይሆናል ፡ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈሳለሁ ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢትን ይናገራሉ ፤ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ ፡ ጐበዛዝቶቻችሁም ራዕይ ያያሉ ፡ ደግሞም በእነዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎች ላይ መንፈሴን አፈሳለሁ” ይላል (ትንቢተ ኢዩኤል 2.28 - 30)

እንግዲህ ይህ ትንቢት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተነሣ በሐምሣኛው ፡ ባረገ በዐሥረኛው ዕለት በዐለ ሐምሳ (ጰንጠቆስጤ) በተባለው ዓመታዊ የአይሁድ በዐል ዕለት ማኅበረ ክርስቶስ በአንድ ልብ ለጸሎት በጸሎት በመትጋት ላይ እንዳሉ መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ ወረደ ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ ።

በዐለ ሐምሳ ከዚያን ጊዜ እንሥቶ በደመ ክርስቶስ የተመሠረተች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መሠረቷ በመንፈስ ቅዱስ የጸናበት የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ዕለት መሆኑ ታውቆ መዘክርነቱ በክርስትናው ዓለም በየዓመቱ በታላቅ መንፈሳዊ ስሜት ይከበር ጀምሮአል (ሮሜ. 8.9)

በዚያን ጊዜም በሙሴ ሕግ መሠረት ከፋሲካ በዐል በኋላ ሰባት ሱባዔዎች ቆይቶ የሚውለውን የመከሩን በዐል ለማክበር ከልዩ ልዩ ሀገሮች መጥተው በኢየሩሳሌም የነበሩ ሁላቸው በዚያን ዕለት ለሐዋርያት የተደረገውን በመመልከታቸው ድርጊቱ እጅግ በጣም አስገርሞአቸው ነበር ።

በሐዋርያት ሥራ እንደ ተጻፈው ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዕርገት በኋላ በዐሥረኛው ዕለት በተፈጸመው የአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሥራ አፈጻጸም ኃይል መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ስንረዳ ፤ በብሉይ ኪዳንም ዘመን የነበረውን የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሕይወት አቋም የሚመራው ይኸው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ከብሉይ ኪዳኑ መረዳት እንችላለን ።

**እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ማን ነው?**

እግዚአብሔር የአንድነት ፡ ሦስቴ የሦስትነት የአምላክ መጠሪያ ሲሆን ፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ከአንደኛው አካል ከእግዚአብሔር አብ ብቻ የሠረፀ ቅድመ ዓለም ከአብና ከወልድ ጋር የነበረ ቀዳሚነትም ሆነ ተቀዳሚነት የሌለው ከአብና ከወልድ ጋር ትክክል የሚሆን ከእነርሱም ጋር በትክክል ስግደትና ምስጋና የሚገባው ለሰው ሁሉ ሕይወትን የሚያድል የሥላሴ ሦስተኛው አካል ነው (1ኛ ቆሮ. 12.11)

በሁለተኛው አካል በቃለ እግዚአብሔር ወልድ ፍጹም ሰው መሆን ማለት በምስጢረ ሥጋዌ ትምህርት ከአይሁድ፣ ከክርስቲያናትና ከሌሎችም መካከል በየጊዜው መናፍቃን ቢታዩም ቅሉ ግን በተለይ ከዐራተኛው መቶ ዘመን መነሻ ጀምሮ በገሃድ ብዙ መናፍቃን ቢነሱም በአስቸኳይ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ሲወገዙ እንዲሁም ከላይ በተጠቀሰው መቶኛ ዘመን ፍጻሜ ገደማ መቅዶኒዮስ የተባለ መናፍቅ መንፈስ ቅዱስን ሕፁዕ (ጐደሎ) ብሎ መካዱና የኑፋቄውም ትምህርት በመሰራጨቱ ሃይማኖታቸው



www.ethiopianorthodox.org

የቀና የጸና አንድ መቶ ሐምሳ ቅዱሳን አበው ሁለተኛውን የዓለም ቤተ ክርስቲያን ጉባዔ እንደ ኤሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር በ381 ዓ.ም. በቁበጥንጥንያ አድርገው መቅዶንዮስን በማውገዝ "በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን ፤ እርሱም ጌታ ሕይወትን የሚሰጥ ከአብ የሠረፀ ከአብና ከወልድ ጋርም በአንድነት እንሰግድለታለን ፤ እናመሰግነዋለንም ፤ እርሱም በነቢያት አድሮ የተናገረ ነው" በማለት ሃይማኖታቸውን አጽንተው ወስነዋል ። (ጸሎተ ሃይማኖት)

በአንደኛው መቶ ዘመን ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ በመጠመቃቸው የቤተ ክርስቲያን መሠረት መጽናቱን ፤ የሐዋርያት ተልዕኮ መፋጠን ፤ የደቀ መዛሙርቱ የስብከት ዘዴ የተሻሻለ መሆኑን ወይንም ለውጥ ማግኘቱን ይህም መሻሻልን ያገኘው የስብከት ዘዴ "ኬሪግማ" መባሉን ከሐዋርያት ሥራ መረዳት እንችላለን ።

መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ በወረደበት ዕለትም ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ኢዩኤል የተናገረው ትንቢት ፍጻሜ ማግኘቱን መነሻ በማድረግ በኢየሩሳሌም ከተማ በበዓሉ ለነበሩ ሁሉ ክርስቶስን ማስተማሩ ወይንም ስለ ክርስቶስ መመስከር ጀመረ ። በኢዮኤል ትንቢታዊ አነጋገር የመንፈስ ቅዱስ ለሁሉም መሰጠት ጉዳይ በብዙዎቹ እስራኤላውያን ዘንድ ተሰምቶና ታይቶ የማይታወቅ አዲስ ነገር በመሆኑ በፆታ፣ በዕድሜና በማኅበራዊ የኑሮ አቋም ልዩነት ሳይደረግና ሳይኖር ሁሉም ሰው በእግዚአብሔር ፊት አንድ ይሆናል የሚለው ትንቢት እጅግ በጣም አስደንቆአቸው ነበር ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም በዚያ ቦታ የተሰበሰቡት እያንዳንዳቸው ንስሐ ገብተው መጠመቅ እንዳለባቸውና ክርስቶስን አዳኛቸው አድርገው እንዲቀበሉት ከዚያም ኃጢአታቸውን ይቅር እንደሚላቸውና የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ እንደሚቀበሉ ደፍሮ በኃይል መሰከረ ።

በዚህ ጊዜ በሐዋርያው በቅዱስ ጴጥሮስ ትምህርትም በአንድ ጊዜ ሦስት ሺህ ነፍሳት በክርስቶስ አመኑ ። ደቀ መዛሙርቱም በዕውነት ስለዕውነት መመስከር የቻሉት በመንፈስ ቅዱስ በተጠመቁ ጊዜ መሆኑን ከሥራቸው ውጤት መረዳት እንችላለን ። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስን ከመቀበሉ በፊት በሊቀ ካህናቱ ቤት አካባቢ በአንዲት ሠራተኛ ሴት ፊት ክርስቶስን ሦስት ጊዜ እንደ ካደው ቅዱስ ወንጌል ይነግረናል (ማር.14.72) ግን በበዐለ ሐምሳ እለት በመንፈስ ቅዱስ ተመልቶ ሲናገር የማንንም ዛቻና ግልምጫ ማስፈራራትም ከምንም አልቆጠረውም (የሐ. ሥራ 2 ፤ 11 - 42)

በዚሁ ዕለት በሐዋርያው የስብከት ዘዴ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የማኅበረ ክርስቶስ የአባላት ቁጥር ከአንድ መቶ ሃያ ወደ ሦስት ሺህ አንድ መቶ ሃያ ከፍ ማለቱን እንመለከታለን ። እነዚህም ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ተመልተው ፤ ሞገስን አግኝተው ፤ አላማቸውን አውቀው፣ አንድነታቸውን አጽንተው እግዚአብሔርን በማመስገን አንድ ሁነው የፍቅር አጋፔ(የፍቅር ዳቦ) በጸሎት ቆርሶ በመመገብ በሕዝቡ ፊት ሁሉ መመላለሳቸውንና እግዚአብሔርም የክርስቲያናትን ቁጥር ለቤተ ክርስቲያን በየጊዜው ይጨምር እንደነበር ከሐዋርያት ሥራ መረዳት እንችላለን (የሐ.ሥራ 2. 47 የቤተ ክርስቲያን መሥራች ጌታችን መድኃኒታችን ሲሆን ንብረትነቷም የክርስቶስ ነው ።

በአንደኛው መቶ ዓመት ከትንሣኤ በኋላ በሐምሳኛው ዕለት ከመንፈስ ቅዱስ በተገኘው በረከትና ኃይል የቤተ ክርስቲያን መሠረት መጽናቱን በሐዋርያት ሥራ እንመለከታለን ። (2 ፤ 1-41)

የመጀመሪያው የማኅበረ ክርስቶስ ቁጥርም በየጊዜው እየጨመረ በመሄዱ ቁጥራቸው ከስምንት ሺህ በላይ ሆነ

እነዚህም በየጊዜውና በየደረሱበት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በሥጋ ሞቶ መነሣቱን ላላወቁና ላልሰሙት ሁሉ በማስረዳታቸው በሐዋርያት ስብከት መስፋፋት ምክንያትም ክርስቲያናት ባልሆኑ አይሁድና በክርስቲያን መካከል ባለመግባባት ታላቅ ክርክርና ውዝግብ በመፈጠሩ በዚህ ምክንያት ወይንም ይህ ምክንያት ሆኖ የክርስቲያናት ስደት መጀመሩን ከታሪክ እንረዳለን ። ይህም የስምንት ሺህ ክርስቲያናት ስደት ለክርስቶስ መንግሥት ስፋት ለስብከት ወንጌል ዕድገትና ልማት መልካም አጋጣሚ እንደነበርም በግልጽ እንረዳለን ።

በዚያን ጊዜ የነበረው የክርስቲያናት ኅብረተሰብ በመንፈስ ቅዱስ የታነፀ ስለነበር ምንም ዓይነት በደል ሳይፈጽሙ በመልካም ሥራቸው ብቻ የሚመጣባቸውን ሁሉ በመቀበል ስለክርስቶስ ፍቅር እስከ መቃብር መድረሳቸውን ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንረዳለን ።

የመጀመሪያይቱ አሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በዚህ አቋም በመንፈስ ቅዱስ የጸናችበት የጰንጠቆስጤ ዕለት በመሆኑ መዘክርነቱ በየዓመቱ ትንሣኤ በዋለ በሐምሳኛው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባረገ በዐሥረኛው ዕለት በታላቅ መንፈሳዊ ስሜት ይከበራል ።

<u>የበዐሉ ጥንታዊነት በክርስትናው እምነት</u>

ይህ ታላቅ የብሉይና የሐዲስ ኪዳናት በዐል የተከበረውና የሚከበረው ዓለም በተቀደሰበት በሳምንቱ መጀመሪያ ዕለት እሑድ ነበር ። በመሠረቱ እሑድ የዕረፍት ቀን የሆነው የሥነ ፍጥረት መነሻ በመሆኑ ሳይሆን የሳምንቱ የዕረፍት ቀንና የክርስቲያናት የሣምንት በዐል ሊሆን የቻለው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ሞቶ ሦስት መዐልትና ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር ቆይቶ የተነሣበት ዕለት በመሆኑ ነው ።

በየሳምንቱ መጀመሪያ የሚከበረው እሑድ የእምልኮት ቀን ሁኖ በክርስቲያናት በግልጽም ሆነ በስውር መከበር የተጀመረው ከሐዋርያት ጊዜ አንስቶ ሲሆን ግን እሑድ በአጠቃላይ ቅዱስ ዕለት ሁኖ ለሁሉም የሳምንቱ የዕረፍት ቀን እንዲሆን ያወጀው ታላቁ ቆስጠንጢኖስ በ321 ዓ.ም. ወይንም በ4ኛው መቶ ዘመን መነሻ ገደማ መሆኑን ታሪክ ይነግረናል ። ይህም ታላቅ የክርስትና በዐል ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የክርስትናውን ዓላማ በተከተለ በነ ሥርዓት መከበሩ ቀጠለ ።

ይህ የመንፈስ ቅዱስ በዐል እንደ በዐለ ትንሣኤ ጥንታዊነት ያለውና በክርስትናው ዓለምም ዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ በዐል መሆኑ ግልጽ ነው ፤ ምክንያቱም የዚህ በዓል አከባበር የተጀመረው ከሐዋርያት ጊዜ አንስቶ የአይሁድ በዐል በነበረበው በእለ ሐምሳ ላይ የክርስትናው በዐል ተመሥርቶ በመገኘቱ ነው ። ይህም በዐል የቅድስት ሥላሴ መሆኑ የማያጠራጥር ነው ።

ስለዚህ በዐል ጥንታዊነት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በአንደኛ ቆሮንቶስ በም. 16 በቁጥር 8 ላይ "ግን በኤፌሶን እስከ በዐለ ሐምሳ ድረስ እሰነብታለሁ" ይላል ። እንዲሁም ወንጌላዊው ሉቃስ በሐ.ሥራ በምዕራፍ 20 በቁ. 16 ላይ "ጳውሎስ በእስያ እጅግ እንዳይቀመጥ ኤፌሶንን ይተው ዘንድ ቆርጦ ነበርና ቢቻለውም በዐለ ሐምሳን በኢየሩሳሌም ይውል ዘንድ ይቸኩል ነበርና" በማለት ያስታውሰናል ። በሐዋርያት ውሳኔም ላይ በ5.20 ፤ በ8. 33 ላይ ይህኑ በዐል በመጥቀስ ተገዥዎች ወይንም ነፃነት ያልነበራቸው ከተለመደው አድካሚና ከባድ የዘወትር ሥራቸው ተላቀው በዚህ ዕለት ዕረፍት አድርገው መዋል እንደሚገባቸው ይናገራል ።

በሁለተኛው መቶ ዓመት የነበረው ፈላስፋውና ሰማዕቱ ጁስቲን (ወይንም) ዩስቲን ) ስለዚሁ በዐል ጥንታዊነትና ታላቅነት ተናግሮአል (አፖሎጂቲክ 1ም. 67)

በሦስተኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ገደማ (+ 202) የነበረው ቅዱስ ኢሬኔው ፤ አሁንም በሦስተኛው መቶ አመት የነበሩት ቴርቱሊያንና (+ 240) ኦሪጅን (+ 254) በስነ ጽሑፋቸው ይኸኑ ታላቅ

ወደ ገጽ ፳ ዞሯል

## የወጣቶች ዐምድ

# መንፈሳውያን ወጣቶች በመሠረተ ትምህርት ዘመቻው

በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የወጣቶች መንፈሳውያን ማኅበራት እየተቋቋሙ በመስፋፋት ላይ ስለሆኑ በመንፈሳዊውም ሆነ በሥጋዊ እውቀት የታነፁ ወጣቶች በብዛት ይገኛሉ።

ለምሳሌ ያህል ባለፈው ሚያዝያ ወር ቁጥር 31 ትንሣኤ መጽሔት እትም በዚሁ የወጣቶች ዓምድ ላይ እንደገለጥነው በሲዳሞ ክፍለ ሀገር ብቻ ከ35 በላይ የወጣቶች መንፈሳውያን ማኅበራት እንዳሉ መጠቆማችን ይታወሳል። እንግዲህ በዚህ ሁኔታ በዚህ ክፍለ ሀገር ውስጥ ባሉት መንፈሳውያን ማኅበራት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶች በአባልነት ተመዝግበው ይገኛሉ ብለን እንገምታለን ። እነዚህ ወጣቶች በየአብያተ ክርስቲያናቱ ካሉት ካህናት ጋር ተባብረው በየመሰብሰቢያ አዳራሻቸውና በየደጀሰላሙ በየሰንበቴ ቤቱም ጭምር የመሠረተ ትምህርት ዘመቻውን እንዲያካሒዱ የሚመለከተው ክፍል የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ እየሰጠ ቢጠቀምባቸው ጥሩ ውጤት ይገኛል ብለን እናምናለን ።

ይህንም ለምሳሌ ያህል የጠቀስነው በሌሎቹም ክፍላተ ሀገር ከዚህ የበለጡ የመንፈሳውያን ማኅበራት አባሎች ሊኖሩ ስለሚችሉ በየክፍለ ሀገሩ የሚገኙትን ሁሉ በመንፈሳውያን ወጣቶች አጠቃላይ ጉባኤና በቤተ ክህነት የወጣቶች ጉዳይ መምሪያ በኩል ጉዳዩን አጠናክሮ መስመር ለማስያዝ ቢሞከር መንግሥት ከሚያደርጋቸው ዘመቻ ጋር ተደምሮ ማይምነትን ለማጥፋት የሚደረገው ጥረት ግቡን እንደሚመታ የማያጠራጥር መሆኑን ለመግለጥ ያህል ነው።

በመሠረቱ በአዲስ አበባ ብቻ ከ 42 በላይ አብያተ ክርስቲያናት እንዳሉ ይታወቃል ፣ በነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ በያንዳንዳቸው የተጠናከሩ መንፈሳውያን የወጣቶች ማኅበራት አሏቸው ። በነዚህም ማኅበራት ያሉት አባሎች የትምህርት ደረጃቸው አብዛኞዎቹ ቢያንስ ከ6ኛ ክፍል በላይ እንደሆኑ ይታመናል ። እንግዲህ ሌላው ቀርቶ ከ8ኛ ክፍል በላይ ያሉትን እንኳን ከመሠረተ ትምህርት ዘመቻ መምሪያው የሚሰጠውን ሴሚናር ተከታተለው በመጠናቸው የተወሰኑ ማይማን ተረክበው በየአድራሻቸው ፣ የሰንበቴ ቤቱና በየደጀ ሰላሙ እንዲያስተምሩ ቢደረግና ለትምህርትም ማካሄጃ የተመደቡት መጻሕፍትና ቁሳቁሶች ሁሉ ቢሰጧቸው ወጣቶቹ ቀንም ሆነ ማታ ባላቸው ትርፍ ጊዜ ሁሉ ለማስተማር ዝግጁዎች እንደሚሆኑ አንጠራጠርም ።

ይህንን ለማለት የምንደፍረው ባየነውና በሰማነው በአጠቃላይ እስከዛሬ የታየውን ውጤት መነሻ በማድረግ እንጂ እንደዚሁ በተምኔት ብቻ ይሆናል ብለን በመገመት አይደለም ።

ለምሳሌ በዚህ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ እንኳን የደብረ አሚን ተክለሃይማኖት የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር አባሎች ገና አንደኛው ዙር የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ከመታወጁ አስቀድሞ ብዙ ማይማንን በማስነበብና በማስልጠን መጻፍና ማንበብ እንዲሁም የሒሳብ ስሌት አስተምረው አስመርቀዋል ። ይልቁንም 1ኛው ዙር የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ በተጀመረበት ዕለት ማለት ሐምሌ 1 ቀን 1971 ዓ.ም.አቶ ጉደታ ማሞ በትምህርት ሚኒስቴር የመሠረት ትምህርት ዘመቻ አስፈጻሚ መኮንን የደብሩ አስተዳዳሪና የሰበካ ጉባኤው አባላት እንዲሁም ጥሪ የተደ

ወደ ገጽ ፴ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# የብፁዕ ቅዱስ ...

ከገጽ ፲ የዞረ

ከፍተኛ ባለሥልጣናት ጋር የሚያደርጉትን ንግግር በዚህ ዓይነት ከፈጸሙ በኋላ በመርሐ ግብሩ መሠረት የቅዱሳት መካናት ጉብኝታቸውን በመቀጠል ኅዳር ሚያዝያ ፫ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም በኢየሩሳሌም ሰሜን ክፍል የሚገኙ ቅዱሳት መካናትን ጎብኝተዋል ።

## በኢየሩሳሌም ሰሜን ስለ ሚገኙት ቅዱሳት መካናት ጉብኝት ዓርብ ሚያዝያ ፫ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በቅዱስ ጉልጉታ የጀመሩትን የቅዱሳት መካናት ጉብኝት በመቀጠል ዓርብ ሚያዝያ ፱ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም በጥብርያዶስ በገሊላ ፤ በናዝሬትና በአካባቢው የሚገኙት ቅዱሳት መካናትን ለመጎብኘት በብፁዕ አቡነ ማትያስ መሪነት ቅዱስነታቸው በአቶሞቢል ፤ ልዑካኑ ደግሞ ከመንግሥት በተረበው ልዩ አቶቡስ ሁነው ከጠዋቱ በ፩ ሰዓት የምናሴ ዕጣ ወደ ሆነው ወደ ሰሜን ክፍል የጉብኝት ጉዞ በማድረግ በሰማሪያ ፤

ክርስቶስ እንዲት ሳምራዊትን ውሀ ቀጅ ያነጋገረበትንና በእሱዋም አማካይነት ስለዘለዓለማዊ የሕይወት ውሀ ለዓለም ትምህርት የሰጠበትን የያዕቆብን እዘቅት ፤ ከሰሉዋን በኋላ የእሥራኤል መንግሥት ሲከፋፈል የሰሜን ክፍል ነገሥታት ቤተ መንግሥት የነበረውንና የሐንስ መጥምቅ በሰማዕትነት እንገቱን የተቆረጠበትን ቦታ፤ ዝነኛውን የታቦርን ተራራና እርማጌዶንን ፤ የጥብርያዶስን ባሕር ፤ የርዳኖስንና ቅፍርናሆምን ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕብስት እብርከቶ የመገበበትን ቦታ ፤ ክርስቶስ በሠርግ ቦታ ተገኝቶ ውሀውን ወደ ወይን ጠጅ በመለወጥ የመጀመሪያውን ተአምር ያደረገበትን ቃና ዘገሊላን ፤ በቅፍርናሆም አካባቢ የአንቀጸ ብፁዓን ትምህርቱን ያስተማረበትን ኮረብታ፤በናዝሬት እመቤታችን ውሃ ስትቀዳ በቅዱስ ገብርኤል የተበሠረችበትን ቦታ ፤ የቀርሜሎስን ተራራና ሌሎችንም በዙሪያው የሚገኙትን ቅዱሳት መካናት ጎብኝተዋል። ጉብኝቱ ሙሉ ቀን የፈጀ ሲሆን ቅዱስነታቸው ከአደረጓቸው የጉብኝት ጉዞዎች ረጅሙና ብዙ ሰዓታትን የጠየቀው ይኸው ነበር ።

እነዚህ ታሪካውያን ቅዱሳት መካናት በልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት ይዞታ ሥር የሚገኙ ከመሆናቸውም በላይ ቤተ መቅደስም የታነፀባቸው ስለሆነ ሁኔታው ለዓለም ክርስቲያኖችና የሃይማኖት ሰዎች ሁሉ እጅግ በጣም አስደሳች ከመሆኑም በላይ ዓለም አቀፍ የቅዱሳት መካናትን ታሪክ በቀላሉ ለመረዳት አመቺ ሁኗል ።

## ደብረ ታቦር

በዚህ የሰሜን ክፍል ጉብኝት የዓለም ጐብኝዎች በይበልጥ ከሚያተኩሩባቸው ቅዱሳት መካናት አንዱ ሔይኸው ስለ ወበቱ ቅዱስ ያሬድ የዘመረለት የታቦር ተራራ ነው ።ወደዚህ ተራራ ላይ ለመውጣት ለከባድ የሕዝብ ማመላለሻ መኪናዎች አዳጋች ከመሆኑ የተነሳ ከተራራው ሥር እየተነሱ ጐብኝዎችን ወደ ተራራው ራስ ላይ የሚያጓጉዙ ታክሲዎች ስለተመደቡ ያለችግር ከተራራው ራስ ላይ ወጥቶ ለመጎብኘት ይቻላል ። የበረታም በእግሩ ሊወጣ ይችላል ። በተራራው ራስ ላይ በአሁኑ ጊዜ የላቲንና የግሪክ አብያተ ክርስቲያናት ቤተመቅደሶች ይገኙበታል ።

ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ በከፊል ወደዚህ ተራራ ይዞ ወጥቶ የዓይን ምስክር ሁነው ዓለምን እንዲያስተምሩ ለሚልካቸው ለእነዚህ ተማሪዎች በተራራው ራስ ላይ ብርሃነ መለኮቱን በገለጸና የአብ ልጅነቱንም በአስመሰከረ ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ ሐዋርያው ጴጥሮስ «ቤት ሠርተን በዚሁ እንኑር » ሲል መጠየቁ በቅዱስ መጽሐፍ ተጽፏል ። በእርግጥ ይህ ተራራ በመንፈሳዊ እንጻር ብቻ ሳይሆን በአተግመጡም የሰውን ልጅ የሚማርክ ስለሆነ ቅዱስ ጴጥሮስን ብቻ ሳይሆን ከላዩ ላይየወጣውን ሁሉ በዚያው ለመኖር የሚያስመኝ በተፈጥሮም ቅዱስ የሆነ ተራራ ነው ።

## ቅፍርናሆም

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ም/ ፲፩ ቁ/፳፫ እንደተናገረው ቅፍርናሆምን የሚጐበኝ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሰው የፈረሰውን ከተማና የወደቀውን የቤት ግንብ ሲመለከት «አንች ቅፍርናሆም እስከ ሰማይ ድረስ ከፍ ከፍ ብትይ ወደ መቃብር ትወርጂ ዘንድ አለሽ» ሲል ክርስቶስ ስለእሱዋ የተናገረው ቃል በትክክል መፈጸሙን ልብ ሊያደርግ ይችላል ትመካባቸው የነበረችው ማያቶች የትም ወድቀውና ተሸራርፈው ይታያሉ ግምቧ ወድቀዋል ፤ አጥሮቿ ፈርሰዋል በጠቅላላ የነበራት ሁሉ ውበት ጠፍቶ ባድማ ሁናለች ክርስቶስ ይህን ቃል ስለ እሷ የተናገረው ቅፍርናሆም የሕይወት ቃል ለመስማት የሚታበዩ ትዕቢተኞችና ጣኦተኞች የሚኖሩባት ከተማ በመሆኗ ስለነበር የቅፍርናሆም ጥፋት እሁንም ለትእምርት ይሆን ዘንድ በወደቀው ፍራሿ ሲታወስ ይኖራል ።

## ዮርዳኖስ

ጆርዳን ወይም ዮርዳኖስ ማለት ታሪክ እንደሚያስረዳው በዕብራይስጥ ዮሬድ ዳን» በአማርኛ «ወረደ ዳን» ማለት ነው « ዳን » የሚለውም ስም ከ፲፪ ነገደ እሥራኤል አንዱ የነገድ አባት ስም ነው ይህ ወንዝ በዓለም የታወቀና ዝነኛ የሆነው በትልቅነቱ ሳይሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅን ሁሉ ለመፈጸም በዮሐንስ እጅ የተጠመቀበትና የአብ ልጅነቱንም ለዓለም ያስመሰከረበት ወንዝ በመሆኑ ነው ክርስቶስ በዚህ ወንዝ የተጠመቀውም ባጋጣሚ ሳይሆን አስቀድሞ በተነገረው ትንቢትና ምሳሌ መሠረት ነው ትንቢቱም ምሳሌውም በትክክል ስለተፈጸመ የዮርዳኖስ ወንዝ በዚያ ከሚገኙበት ቅዱሳት መካናት አንዱ ሁኗል ።

ቅዱስነታቸው ልዑካኑን እስከትለው ይህን ወንዝ ለመጐብኘት ረጅም ጉዞ ያደረጉትም በዚህ ምክንያት ነበር ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ የሰሜን ክፍል ጉብኝታቸውን በዚሁ ከፈጸሙ በኋላ አዳር በኢየሩሳሌም ከተማ ሁኖ በበነጋው ቅዳሜ ሚያዝያ ፬ ቀን ፲፱፻ ዓ / ም/ ጉብኝታቸውን በመቀጠል ጌቴሴማኒን ዐፀደ ሐምልን ደብረ ዘይትን ጎብኝተዋል ። በጉብኝቱም ወቅት የግብር ጸሎት የተጸለየና ያሬዳዊ መዝሙርም የተዘመረ ከመሆኑም በላይ ብፁዕ ፓትርያርኩ ቃለ ወንጌል በማሰማት ጸሎተ ቡራኬ ሰጥተዋል ።

ደብረ ዘይት ማለት የወይራ ተራራ ማለት ሲሆን ይህ ተራራ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ ምሥጢረ ምጽአቱን የገለጸበት ፤ በመዋዕለ ስብከቱም ቀን በኢየሩሳሌም ሲያስተምር ውሎ ማታ ያድርበት የነበረና በኋላም ከሙታን በተነሣባዜ « ገሊላ እትድሙከሙ» ማለት ገሊላ እቀድማችኋለሁ ሲል በተናገረው መሠረት ለደቀ መዛሙርቱ የተገለጸበት ቅዱስ ቦታ ነው ።

## ዐፀደ ሐምል

ዐፀደ ሐምል ማለትም ደግሞ የተክል ቦታ ማለት ሲሆን ይህ ቦታ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሴተ ሐሙስ የጸለየበትና በኋላም ይሁዳ ይስቅሉት ዘንድ ይፈልጉት ለነበሩ ወገኖች ክርስቶስን ያስያዘበት ቦታ ነው ።

### ጌቴሴማኒ

ጌቴሴማኒ ማለት የዘይት መጥመቂያ ማለት ሲሆን ይህ ቦታ እመቤታችን ሞትን በቀመሰች ጊዜ በድን ሥጋዋ ያረፈበት ቦታ ነው ። ይህ ቅዱስ ቦታ በአርመንና በግሪክ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ይዞታ ሥር ያለ ሲሆን በቦታውም ላይ አንድ ከፍተኛ ዓለም አቀፍ የሆነ ቤተ መቅደስ የታነፀበት ስለሆነ ማንኛውም ጉብኝ ያለ ችግር የቦታውን ቅዱስነት መረዳት ይችላል ።

ከእንዚህ ቅዱሳት መካናት ጉብኝት በኋላ የጉብኝቱ መርሐ ግብር ተፈጽሞ ቅዱስነታቸው ወደመንበረ ጵጵስናው ተመልሰዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ እሑድ ሚያዝያ ፭ ቀን ፲፱ ዓ/ ም/ በደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት ገዳም ተገኝተው አስቀድሰዋል ። እንዲሁም በዚሁ ቀን የጥቁር እሥራኤል ተወካዮችን በመንበረ ሊቀ ጵጵስናው ተቀብለው እነጋግረዋል ።

ጥቁር እሥራኤል ነን በማለት ራሳቸውን ለዓለም በማዘተዋወቅ ላይ የሚገኙት እነዚህ ኅብረተሰቦች ቁጥራቸው ከ፪ሺ የማይበልጥ ሲሆን በባርነት ተሸጠው በአሜሪካ ይኖሩ የነበሩ አፍሪካውያን ዘሮች መሆናቸውን ራሳቸው ይናገራሉ ። እነዚህ ወገኖች በአሁኑ ጊዜ ወደ እሥራኤል ምድር መጥተው በናጌብ በረሃ ዲሞና በሚባል ቦታ ስለሰፈሩ ዲሞናዎች ይባላሉ ኅብረተ ሰባቸውም የሚመራው በ፲፪ ልዑካን (አለቆች) ነው ። የሚተዳደሩትም በራሳቸው ሕግና ሥርዓት ስለሆነ ኑሮአቸው ከሌላው የተለየ ነው ። በእምነታቸው አይሁዳውያንም ክርስቲያኖችም ሳይሆኑ የሙሴን ሕግ በመከተል በአንድ አምላክ የሚያምኑ ከመሆናቸውም በላይ ኢየሩሳሌም የአፍሪካ ክፍል እንደነበረችና ምድረ እሥራኤልን ለመውረስ ትንቢት የተነገረላቸው ትክክለኞቹ የአብርሃም ዘሮች የሆኑት እሥራኤላውያንም እነሱ መሆናቸውን ያምናሉ ። ለግሳመንም ይጥራሉ ከአለቆቹ አንዳንዶቹወደ ኢትዮጵያ መጥተው ጉብኝት አድርገው እንደነበር ከመናገራቸውም በላይ አድርገው እንደነበር ከመናገራቸውም በላይ ኢትዮጵያን የሚወዱና የሚያከብሩ ናቸው ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ የእነዚህን ኅብረተ ሰቦች ተወካዮች ባነጋገሩበት ወቅት የመታሰቢያ ስጦታ ያደረጉላቸው ሲሆን ልዑካኑም ለቅዱስነታቸው የመታሰቢያ ስጦታ አድርገዋል ።

በዚሁ ቀን ማታ ከምሽቱ ፪ ሰዓ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳም ማኅበር ሊቀ ጳጳስ ለብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ክብር በፕላዛ ሆቴል የክብር ግብዣ ተደርጓል ። በግብዣውም ላይ የአርመን ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ የመንግሥት ባለሥልጣናትና የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች የመንግሥታት ተወካዮችና ቆንሲሎች ተገኝተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ጉብኝታቸውን በመቀጠል ሰኞ ሚያዝያ ፮ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ/ም/ በግምቡ ውስጥ የሚገኘውን የኢየሩሳሌምን ከተማ ምዕራብ ክፍል ጐብኝተዋል ። ይህ ክፍል በአሁኑ ጊዜ እሥራኤላውያን የኢየሩሳሌምን ጥንታዊ ከተማ ታሪክ ለማግኘት ከፍተኛ የመሬት ቁፈራ የሚያደርጉበት ክፍል ሲሆን በምርመራውም ከፍተኛ ውጤት የተገኘበት ቦታ ነው ። ይህ ክፍል የአይሁዳውያን ቅዱስ ቦታ ስለሆነ የጉብኝቱ መሪ ሬቢ የሃዳንቡ ።

ጉብኝቱ እንደ ተፈጸመ ረቢው ስለ ቅዱስነታቸው ክብር የሻይ ግብዣ አድርገዋል ።

ቀጥሎም ቅዱስነታቸው በአሁኑ ጊዜ በእስላሞች እጅ የሚገኘውን የሰሎሞንን ቤተ መቅደስና ቤተ መንግሥት ጐብኝተዋል ከዚሀ በኋላ የጉብኝቱ ፍጻሜ ሆኖ ወደመንበረ ሊቀ ጵጵስናው ተመልሰዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በዚሁ ቀን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በአረመኔው ሂትለር ትእዛዝ በግፍ በተጨፈጨፉት ፮ ሚሊዮን እሥራኤላውያን ስም የቆመውን የመታሰቢያ ሐውልት በመንግሥት ተወካይ መሪነት ጐብኝተዋል ። ቅዱስነታቸው ሐውልቱን በጐበኙበት ወቅት ስለ ተፈጸመው ግፍ የሚያሳየውን የውስጥ ድርጅት በአስጐብኙ አማካይነት እየተዘዋወሩ ከተመለከቱ በኋላ በመጨረሻ በሐውልቱ ላይ የአበባ ጉንጉን አስቀምጠው የጉብኝቱ ፍጻሜ ሁኗል። በጉብኝቱ ፍጻሜ ቅዱስነታቸው በተዘጋጀው የክብር መዝገብ ላይ ፈርመዋል።

በዚሁ ቀን ማታ በ፲፪ ሰዓት ተኩል የአርመን እርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ያሬሽ ይድሪያን ስለብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ክብር በመንበረ ፓትርያርክቻው የክብር ግብዣ አድርገዋል ። በግብዣው ወቅት ብፁዕ ወቅዱስ የአርመን ፓትርያርክ ለቅዱስነታቸው የወርቅ የፓትርያርክ የአንገት መስቀልና የቅዱስ ጎልጉታ ቅርጽ የያዘ ከዕብን በረድ የተሠራ የመታሰቢያ ስጦታ አድርገውላቸዋል ። በግብዣው ላይ የመንግሥትና የአብያተ ክርስቲያናት ባለሥልጣናት ተገኝተው ነበር ።

በሚቀጥሉት ቀናት ማክሰኞና ረቡዕ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ዕረፍት ካደረጉ በኋላ ሐሙስ ሚያዝያ ፱ ቀን ፲፱፻ ዓ/ ም/ የቅዱሳት መካናት ጉብኝታቸውን በመቀጠል እያሪኮን ክርስቶስ ዓርባ መዓልትና ሌሊት የጾመበትን ገዳም ቆሮንቶስንና ሙት ባሕርን ጎብኝተዋል ። በዚሁ ጉብኝት ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በኢያሪኮ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ገዳም ከመጎብኘታቸውም በላይ በገዳሙ በሚገኘው የሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ጸሎተ ሠርክ አድርገዋል ፤ ከጉብኝቱም በኋላ የሰላሳ መጠጥ ግብዣ ተደርጓል ።

የኢያሪኮ ገዳም በመጀመሪያ ወይዘሮ አማረች ዋለሉ የተባሉ ኢትዮጵያዊት በገንዘባቸው ገዝተው ይኖሩበት የነበረ ቦታ ሲሆን ፤ በኋላ ግን ገዳም ሆና የኢትዮጵያውያን ማረፊያ እንዲሆን ቦታውን በመለገሣቸው ቤተ መቅደስ ታንጾበት የማኅበር ገዳም ሆኗል ። በኋላም ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ራስ እምሩና ራሳቸውም ወይዘሮ አማረችም በመተባበር ለገዳሙ ገቢ የሚያስገኝ የኪራይ ቤት ሠርተው በማበርከታቸው ገዳሙ በኢትዮጵያዊነት ለዘለዓለም እንዲኖር አድርገውታል ።

ከኢያሪኮ ጉብኝት በኋላ ቅዱስነታቸው የዕለቱን ጉብኝታቸውን ፈጽመው ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰዋል የኢያሪኮ ጉብኝት በኢየሩሳሌም ለሚደረገው የቅዱሳት መካናት ጉብኝት ፍጻሜ ስለሆነ ፤ በበነጋው ዓርብ ሚያዝያ ፲ ቀን ፲፱፻ ዓ/ ም/ ብፁዕ ወቅዱስ የኢየሩሳሌም ጉብኝታቸውን ፈጽመዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስነታቸው ጉብኝታቸውን ፈጽመው ከመመለሳቸው በፊት የገዳሙን ማኅበር በመንበረ ሊቀ ጳጳሱ አዳራሽ ሰብስበው ስለገዳሙ የሥራ ይዞታና ኅብረት ምክርና መመሪያ ሰጥተዋል ።

ቅዱስነታቸው በኢየሩሳሌም የሚያደርጉትን የቅዱሳት መካናት ጉብኝ ታቸውን ፈጽመው ሲመለሱ ብፁዕ አቡነ ማትያስ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ፤ የእሥራኤል የሃይማኖት ሚኒስቴር ዳይሬክተር ጀኔራልና የክርስቲያን ክፍል ኃላፊ ፤ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ጉዳይ መምሪያ ኃላፊና በአፍሪካ የክርስቲያን ክፍል ተወካይ ፤ በልዳ እይሮፕላን ማረፊያ ተገኝተው ሸኝተዋቸዋል ። ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ የኢየሩሳሌምን ከተማ ከመልቀቃቸው በፊት በቅዱስ ጉልጎታና በዴር ሡልጣን የኢትዮጵያ ገዳም ተገኝተው ጸሎት አድርሰዋል ።

## ብፁዕ ወቅዱስ ፓትሪያርኩ

የኢየሩሳሌም ጉብኝታቸውን ፈጽመው ሲመለሱ በአቴንስ የተደረገ አቀባበል ።

ሚያዝያ ፲ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ/ ም/ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ የኢየሩሳሌም ጉብኝታቸውን ፈጽመው ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ እግረ መንገዳቸውን በአቴንስ የ፫ ቀናት ጉብኝት አድርገዋል ። ቅዱስነታቸውን የያዘው የኢል አል እይሮፕላን ከ ጥዋቱ ፫ ሰዓት ተነሥቶ አቴንስ እይሮፕላን ማረፊያ ሲደርስ በግሪክ የኅብረተ ሰብእዊት ኢትዮጵያ አምባሳደር አቶ አስፋው ለገሠ ፤ የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የውጭ ጉዳይ ኃላፊ ብፁዕ አቡነ በርናባስ በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ መምሪያ ኃላፊና የፓንዴሊ ገዳም አበምኔት ብፁዕ አቡነ ክሪሶስቶሞስ፤በግሪክ የኢትዮጵያ ተማሪዎች በአቴንስ እይሮፕላን ማረፊያ ተገኝተው የክብር አቀባበል አድርገውላቸዋል ። ቅዱስነታቸው ከአይሮፕላን ወርደው በአይሮፕላን ማረፊያው ሳሎን ለጥቂት ጊዜ እረፍት ካደረጉ በኋላ ፤ በአቴንስ የ፫ ቀናት ጉብኝት ለማድረግ ለማረፊያ ወደ ተዘጋጀላቸው የፔንዴሊ ገዳም አመሩ ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትሪያርኩ በአቴንስ በቆዩበት ወቅት የግሪክን እርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ሱራፌልን ያነጋገሩ ከመሆኑም በላይ ፤ እርቦስ ፋጉስን ፤ የቂሣርያኒን ገዳም ቆሮንቶስን ጉብኝተዋል ። ቀጥሎም የግሪክ እርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ ቤትን ፤ ለግሪክ እርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ኮሌጅ መጋቢ የሆነውን የሪዛርዮን የካህናት ማሠልጠኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ ቤት ጐብኝተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖትና ብፁዕ አቡነ ሱራፌል ንግግር ባደረጉበት ወቅት በተለይ ቅዱስነታቸው ስለ ግሪክ እርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና ስለ ኢትዮጵያ እርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቆየ ግንኙነትና ትራድኦ በመጥቀስ ንግግር አድርገዋል ።

ከንግግሩ ፍጻሜ በኋላ ቅዱስነታቸው ለሊቀ ጳጳስ ሱራፌል አንድ ከእንጨት የተሠራ ትልቅ የመረጻዛ መስቀል ስጦታ አድርገውላቸዋል ። ብፁዕ አቡነ ሱራፌል ብፁዕ ወቅዱስ ፓትሪያርኩን እንኳን ደኅና መጡ በማለት የመልስ ንግግር ካደረጉ በኋላ ፤ ለቅዱስነታቸውና ለተከታዮቹም የመታሰቢያ ስጦታ አድርገዋል ። በመጨረሻም የለስላሳ መጠጥ ግብዣ ተደርጎአል ።

ቅዱስነታቸው ታሪካዊውን የቆሮንቶስን ከተማ በጐበኙበት ወቅት ፤ የቆሮንቶስ ሜትሮፖሊስ ብፁዕ አቡነ ፓንደለይሞናስ በክብር ተቀብለዋቸዋል ። ቅዱስነታቸው ቆሮንቶስ ከተማ እንደደረሱ በሜትሮፖሊቱ መሪነት የቆሮንቶስን ከተማ ሙዚየም እየተዘዋወሩ ከጐበኙ በኋላ ፤ ስለቅዱስነታቸው ክብር የለስላሳ መጠጥ ግብዣ ተደርጎ በዚያ የሚደረገው ጉብኝት ፍጻሜ ከሆነ በኋላ ፤ በቆሮንቶስ ከተማ አጠገብ አዲስ የተቋቋመውን የካህናት ማሠልጠኛ ት/ ቤት ጐብኝተዋል ።

ቅዱስነታቸው በዚሁ ት/ ቤት እንደደረሱ የማሠልጠኛው ት/ ቤት ተማሪዎችና መምህራን በሰልፍ ተቀብለዋቸዋል ። ቀጥሎም ቅዱስነታቸው የት/ ቤቱን የውስጥ ድርጅት እየተዘዋወሩ ከተመለከቱ በኋላ የለስላሳ መጠጥ ግብዣ ተደርጎ የጉብኝቱ ፍጻሜ ስለሆነ ፤ ቅዱስነታቸው ወደፔንዴሊ ገዳም ተመልሰዋል ።

በአቴንስ ከተማ የሚገኘውን የሪዛሪደን ሁለተኛ ደረጃ ት/ ቤት በጐበኙበትም ወቅት ተማሪዎቹና መምህራኑ በሰልፍ ተቀብለዋቸዋል ። ይህ ት/ ቤት እያሌ የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳትንና ሊቃነ ጳጳሳትን ያፈራ ከፍተኛ ት/ ቤት መሆኑ ታውቋል። ቅዱስነታቸው የት/ ቤቱን የውስጥ ክፍል በት/ ቤቱ ኃላፊ እየተዘዋወሩ ከጐበኙ በኋላ ፤ ለተማሪዎቹ ቃለ ምዕዳን ሰጥተዋል ። በመጨረሻም የለስላሳ መጠጥ ግብዣ ተደርጎ የጉብኝቱ ፍጻሜ ሆኗል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትሪያርኩ በዚሁ ዕለት የግሪክ እርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ ቤትን በጐበኙበትም ወቅት የቅዱስ ሲኖዶስ የውጪ ጉዳይ ኃላፊና ሌሎችም ጳጳሳት በክብር ተቀብለዋቸዋል ።

በጉብኝቱም ወቅት ስለ ቅዱስ ሲኖዶሱ አቋም ገለጻ ተደርጎላቸዋል በመጨረሻም የለስላሳ መጠጥ ግብዣ ተደርጎ የጉብኝቱ ፍጻሜ ሁኗል ።

ቅዱስነታቸው በአቴንስ በቆዩባቸው ቀናት በግሪክ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ምእመናንንና ተማሪዎችን በማረፊያ ቤታቸው ተቀብለው ያነጋገሩ ከመሆኑም በላይ ሚያዝያ ፲፪ ቀን ፲፱፻ ዓ/ ም/ እሑድ በአቴንስ የአርመን እርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው በአቴንስ ለሚገኙት ኢትዮጵያውያን ተማሪዎችና ምእመናን ቃለ ምዕዳንና ጸሎተ ቡራኬ ሰጥተዋል ።

በዚሁ ዕለት ከቀኑ በ፲ ሰዓትም በግሪክ የኅብረተ ሰብእዊት ኢትዮጵያ አምባሳደር አቶ አስፋው ለገሰ ስለቅዱስነታቸው ክብር በመኖሪያ ቤታቸው የሪሴፕሺን ግብዣ አድርገዋል ። በግብዣውም ላይ ጥሪ የተደረገላቸው የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣናትና በአቴንስ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተገኝተዋል ። በግብዣው ላይ በአቴንስ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ተወካይ ሀገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ ረሀብንና በሽታን ድንቁርናን ለማጥፋት የምታደርገውን ጥረት በመደገፍና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም በቅዱስነታቸው መሪነት የተሻለ ዕድል እንዲገጥማት በመመኘት ንግግር አድርገዋል ። ከዚህ በኋላ የግብዣው ፍጻሜ ሁኖ ቅዱስነታቸው ወደ ማረፊያ ቤታቸው ተመልሰዋል ።

### በጉብኝቱ ወቅት በአንዳንድ በጎ አድራጊዎች የተደረገ ልግስና

ቅዱስነታቸው አቴንስ በቆዩበት ወቅት በአቴንስ ከተማ የሚኖሩ አንድ አቶ ወልደ ሐናረታ የተባሉ ኢትዮጵያዊ በጐ አድራጊ ለልብስ ተከህኖ መግዣ እንዲያገለግሉት የሚውል ፶ሺ (አምሳ አምስት ሺ ድረኽማ (የግሪክ ገንዘብ) ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የለገሡ ሲሆን በዚሁ ከተማ የሚኖሩ የግርያም ማኅበርተኞች የሆኑ ኢትዮጵያውያን ደግሞ በማኅበራቸው ስም ፮ሺ (ስድስት ሺ) ድራኽማ ለተመሳሳይ ዓላማ ሰጥተዋል ። እነዚህ በጎ አድራጊዎች ያሳዩት በጐ ተግባር የሀገራቸውንና የቤተ ክርስቲያናቸውን ጽኑዕ ፍቅር የሚገልጽ በመሆኑ ቅዱስነታቸው ዕርዳታውን በደስታ ተቀብለውታል ። ይህ ዓይነቱ ተግባር መልካም ምሳሌነት ያለው ስለሆነ የእነዚህን በጐ አድራጊዎች ስም ቤተ ክርስቲያን ስታስታውሳቸው ትኖራለች።

ከሦስት ቀናት ጉብኝት በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ የአቴንስ ጉብኝታቸውን ፈጽመው ሚያዝያ ፲፬ ቀን ፲፱፻ ዓ/ ም/ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰዋል ። ቅዱስነታቸው ከአቴንስ እይሮፕላን ማረፊያ ሲነሱ በግሪክ የኅብረተ ሰብእዊት ኢትዮጵያ አምባሳደር ፤ በግሪክ እርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ተወክለው ብፁዕ አቡነ ክሪሶስቶምስ የፔንዴሊ ገዳም አበምኔትና የሲኖዶሱ የውጪ ጉዳይ ጸሐፊ ቆሞስ ዳማስቴስናስ የውጭ ጉዳይ ኃላፊ በግሪክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቤተ ክርስቲያን ክፍል ኃላፊ ፤ በግሪክ የኢትዮጵያ ተማሪዎች በአይሮፕላን ማረ

ወደ ገጽ ፳፤ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org



# የምእመናን ድምፅ

ይህ አምድ የኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤተ ክርስቲያን በአስተዳደር ተሐድሶ የምትራመድበትና የምትሻሻልበት ክ.ስቲያኖች ስለ ቤተ ክርስቲያናቸው በቀና መንፈስ አስተያየት የሚያቀርቡበት ነው ። በዚህ ዓምድ ሊቀርቡ የሚገባቸው ጽሑፎች የቤተ ክርስቲያናችን ውሳኔዎች ሳይሆኑ የግለሰቦች አስተያየት መሆናቸውን የዓምዱ ተከታታዮች በቅድሚያ እንዲያውቁልን እንፈልጋለን ።

አዘጋጅ ነቅዓ ጥበብ ወንድም  የስልክ ቁጥር 11-66-16  የመልእክት ሣ.ቁ. 3137  አዲስ አበባ

በዛሬው የምእመናን ድምፅ ዓምዳችን ለማቅረብ የፈለግነው ከአዲስ አበባ አድባራት አብያተ ክርስቲያናት ምእመናን መካከል የመቃብር ቦታ የሌላቸውን አብያተ ክርስቲያናት ምእመናን የሚመለከት ሲሆን ለዚህም መፍትሔውን ይሰጡናል ብለን የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አስተዳዳሪ ሊቀ ሥልጣናት ገብረማርያም ፈለቀንና የደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት አስተዳዳሪ መምህር ዘካርያስን ጠይቀን ያገኘነውን መልስ ለዝግጅታችን ተከታታዮች አቅርበናል ።



የመ/ፀ/ቅ/ሥ/ካቴድራል አስተዳዳሪ ሊ/ሥልጣናት ገ/ማርያም

የምእመናን ድምፅ፡-ሊቀ ሥልጣናት ገ/ማርያም በአካባቢ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ምእመናን የመቃብር ቦታ ስሌለላቸው ሰው በሞተ ጊዜ በባለ ወልድ ቤተ ክርስቲያን ቅጽረ ግቢ ለመቅበር ይዘው መምጣታቸው ግልጽ ነው ። ታዲያ አንዳንድ ምእመናን ለመቃብር ቦታ ገንዘብ ክፈሉ እሉን እያሉ የሚናገሩ አሉ ይህ እውነት ነው ?

ሊቀ ሥልጣናት የአራቱ አብያተ ክርስቲያናት ምእመናን ኮሚቴ መርጠው ለጽዳት ጠባቂዎች ዘበኞች እንዲከፍል በመነጋገር ላይ ናቸው እንጂ በተናጥላ የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ አስተዳደር ገንዘብ ክፈሉ ብሎ ምእመናንን የጠየቀበት ጊዜ የለም ። ለወደፊትም የኮሚቴውን ውጤት ነው የምንጠብቀው እንጂ በእኛ በኩል ለብቻ አንጠይቅም ።

የምእመናን ድምፅ የመቃብር ቦታ የሌላቸው ምእመናን የመቃብር ቦታ ወደአላቸው አብያተ ክርስቲያናት ለመቅበር ሲያመጡ ይከለከሏቸዋል የሚል አነጋገር አለ መምህር ዘካርያስ በእናንተ በኩል እንዴት ነው ።?

መምህር ዘካርያስ ፡- በኛ በኩል አልከለከልንም ወደፊት የመቃብር ቦታ እስካልጠበበ አንከለክልም።ግን አንዳንዶቹ እንደሚሉት ሳይሆን የመቃብር ቦታ ጽዳቱ እንዲጠብቅ ቁጥጥር ለማድረግ ትምህርት እንሰጣለን ።

የምእመናን ድምፅ የሰበካ ጉባኤን ደንብ ያላሟሉ ምእመናን እክል አጋጥሟቸው ለመቅበር ሲመጡ መቆጣጠሩም መልካም ይመስለኛል ። ምክንያቱም ከአካባቢ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ምእመናን ጋር ተወያይቶ ለጽዳቱ አጠባበቅ ሆነ ለሌላም አገልግሎት ስለሚውል ነው ስለዚህስ ምን አስተያየት አለዎ ?

ሊቀ ሥልጣናት የሰበካ ጉባኤን ደንብ ያላሟላ መታወቂያ የሌለው ከሆነ ቁጥጥር ይደረጋል ተመዝግቦ ካልተገኘ የተወሰነ ገንዘብ ይከፍላል ምክንያቱም በቃለ አዋዲ ደንብ ም.7 ንኡስ አንቀጽ 50 ያስረዳልና ነው ። እያንዳንዱም ካህን በሰበካ ጉባኤ ተመዝግቦ አስተዋጽኦ ያላሟላውን እንዲያስተምርና እንዲቆጣጠር የሰበካ ጉባኤ ደንብ ም. 7 ፡ ንኡስ አንቀጽ 52 ያዛል ።

የምእመናን ድምፅ ፡- የመቃብር ቦታ የሌላቸው ምእመናን ወደ እናንተ ቤተ ክርስቲያን ለመቅበር ሲመጡ በሰበካ ጉባኤ ያልተመዘገቡ ከሆነ ገንዘብ ትጠይቋቸዋላችሁ ወይስ አትጠይቋቸውም ከሌላው ቤተ ክርስቲያን እንደሚጠየቅ ተረድተናል በእናንተ በኩል እንዴ ነው ?

መምህር ዘካርያስ በበኩላችን በሰበካችን ያለውን ምእመን መመዝገቡና አለመመዝገቡን ካጣራን በኋላ ተመዝግቦ ከተገኘ በነፃ እንፈታለን ካልተመዘገበ የተወሰነ ገንዘብ እናስከፍላለን ከሌላ ሰበካ ሲቀበር ብቻ የሚመጡትን ግን ተከታትሎ ማስፈጸም ያለበት የአጥቢያው ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት ስለሆነ አንጠይቅም ።

የምእመናን ድምፅ ስለመቃብር ቦታ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት የተላለፈ ውሳኔ አለ? ወይስ የለም ካለስ ውሳኔው የሚለውን ቢያብራሩልኝ ?

ሊቀ ሥልጣናት ከፓትርያርኩ ልዩ ጽ/ቤት የተላለፈ ውሳኔ አለ ውሳኔውም የተላለፈው ሰኔ 11 ቀን 1971 ዓ.ም. ሲሆን የሚለውም ቃል እንደሚከተለው ነው‘‘የመቃብር ቦታ ያላቸው አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የመጣውን የሙታን አስከሬን ዋጋ ካልከፈላችሁ አናስቀብርም በማለት መቃብር መከልከላቸው ከባድ ቅራኔ አስከትሏል ለተባለው የመቃብር ቦታ በአሏቸው ቦታ ጽዳትና ለጥበቃው አገልግሎት የሚያስፈልገውን ክፍያ በየሰበካ ጉባያቸው አጥንተውና ተስማምተው በመወሰን እንዲከፍሉ ሆኖ በሰበካ ጉባኤ የተመዘገበና አስተዋጽኦውን በየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን የከፈለ ምእመን ሲሞት ጸሎተ ፍትሐት በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ተደርሶለት አስከሬኑ የመቃብር ቦታ ወደአለበት ቤተ ክርስቲያን ሲመጣ ዋጋ ሳይጠይቅ በነፃ እንዲቀበር ’’ይላል በዚህ መሠረት ነው እኛም የምንሠራው ።

የምእመናን ድምፅ ከአካባቢያችሁ አብያተ ክርስቲያናት ምእመናን ጋር ስለ መቃብር ቦታ ተወያይታችሁአል ወይስ አልተወያያችሁም ።

መምህር ዘካርያስ ከፓትርያርኩ ልዩ ጽ/ቤት በተላለፈው ውሳኔ መሠረት ምእመናን ችግር እንዳይገጥማቸው ለደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤልና ለጽርሐ ጽዮን ጉላ ቅዱስ ሚካኤል አስተዳዳሪዎች መስከረም 30 ቀን 1972 ዓ.ም.በ ቁጥር 31/72 ደብዳቤ አስተላልፈን ነበር እነርሱ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው እስከአሁን ድረስ ልንወያይና አንዳንድ ውሳኔም ልናስተላለፍ አልቻልንም ።



የደብረ አሚን ተ/ሃይማኖት አስተዳዳሪ መ/ዘካርያስ

የምእመናን ድምፅ ዝግጅት ክፍል

ምእመናን የቤተ ክርስቲያን መምሪያ መቀበልና መፈጸም ሲገባቸው አንዳንዶች የሰበካ ጉባኤን ደንብ ያላሟሉ ምእመናን ቤተ ክርስቲያንን ባልሆነ ወሬ ሊያጠፉ አይገባቸውም ። ከላይ ጠይቀን ባገኘነው መልስ ለመቃብር ቦታ ክፈሉ ያልንበት ጊዜ የለም የሚል ነው። ታዲያ ይህ ከሆነ ምእመናን ለአንዲት ቤተ ርስቲያን አስተዳደር ቀርቦ በመወያየትና የሚፈልገውን በማሟላት ፋንታ ከዳር ሆነው ትችት የሚያቀርቡትን አንዳንድ ሰዎች ከዚህ አድራጐታቸው እንዲቆጠቡ እናሳስባቸዋለን ፤ በቤተ ክርስቲያንም በኩል ያልተሟላ ግልጋሎት የሚያደርግ ከሆነ የዛሬይቷ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የምእመናንንም መብት ጭምር የሚያንፀባርቅ ስለሆነ በቃለ አዋዲው ደንብ መሠረት ተወያይተው መፍትሔ እንደሚያገኙለት እንተማመናለን ።

በሌላ በኩል ደግሞ በቀረበው ጥያቄና መልስ አስተያየት የሚያቀርቡ ምእመናን ካሉ ዓምዱ በደስታ የሚቀበል መሆኑን እንገልጻለን ።

# ቅዱስ ሚካኤልና ተልእኮው

ከገጽ ፰ የዞረ

ይመከራታል ። ይልቁንም በየወሩ ይዘክሩት የነበረው የቅዱስ ሚካኤል በዓል በተለይም ኅዳርና ሰኔ 12 ቀን የሚከበረው የቅዱስ ሚካኤል በዓል እንዳይታጐል ሚስቱን አጽናንቶና አደራ ብሎአት ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ ። በዚህ ጊዜ የምዋቿ ሚስት ነፍሰ ጡር ነበረች ።

ከጥቂት ቀን በኋላ የምትወልድበት ቀን ደረሰና ታመመች ምጥ ተይዛ በጭንቅ ላይ ሳለች ወደ እግዚአብሔር ጸለየች ፤ እግዚአብሔርም ጸሎትዋን ሰማና በስሙ የምትመጸውትለትንና የምትማጸንበትን መልአክ ቅዱስ ሚካኤልን ላከላት ወዲያውኑ ሲያዩት የሚያስደስት መልከ መልካም የሆነ ወንድ ልጅ በሰላም ወለደች ጭንቀቷን ያስወግድላት ዘንድ የመጣው ቅዱስ ሚካኤል ሕፃኑን ባረከው ሕፃኑ ከአደገ በኋላ የዚያን ክፉ ባለጸጋ ሀብትና ንብረት በሙሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሚወርስ መልአኩ ተናግሮ ነበር በዚህ ጊዜ ባለጸጋው በመስኮት ያይና ይሰማ ስለነበረ በኃዘን ተዋጠ ።

ሕፃኑ የአሥር ዓመት ልጅ ሲሆን ያ ምሕረት የለሽ ባለጸጋ እንዴት አድርጎ ሕፃኑን እንደሚገድለው ያወጣ ያወርድ ጀመር አንድ ቀን የሕፃኑን እናት ለጅሽን ለእኔ ስጭኝ እኔ ጥሩ እያበላሁ እያጠጣሁና እያለበስኩ አሳድገዋለሁ ለአንቺም ለችግርሽ ገንዘብ እሰጥሻለሁ በማለት አታለላት ። እርስዋም የባለጸጋውን ተንኮል ስላልተረዳች የሰጣትን ገንዘብ ተቀብላ ልጅዋንሰጠችው ።

‘‘ያ’’ ጨካኝና ምሕረት የለሽ ባለጸጋ በሕፃኑ ቁመት ልክ የዕንጨት ሣጥን ሠርቶ በሣጥኑ ቆልፎ ከባሕር ጣለው ሕፃኑን የያዘው ሣጥን በእግዚአብሔር ኃይል በውኃ ላይ እየተንሳፈፈ በሕፃኑ ላይ ምንም ጉዳት ሳይደርስበት ብዙ ጊዜ ተጓዘ ። በዚያ አንድ ሰው ሣጥኑን ከባሕር ዳር አግኝቶ ወደ ቤቱ ወስዶ ቢከፍተው ሕፃኑን በሕይወት አገኘው ፤ እርሱም‘‘ዘረከብክዎ እማይ’’ ከውሃ ያገኘሁት ሲል ‘‘ባሕራን’’ ብሎ ሰየመውና እንደ ልጅ አድርጎ አሳደገው ። ባሕራንን ከውሃ የጣለው ጨካኙሰው ሥራው ንግድ ስለነበረ አንድ ቀን ባሕራን ወደሚኖርበት አገር ለንግድ ሄደ ። እንደ አጋጣሚ ባሕራን ወደሚኖርበት ቤት በእንግድነት ገባ ባለቤቱ ልጁን ‘‘ባሕራን’’ ብሎ ሲጠራው ሰማ ስሙም ስለ አስደነገጠው የስሙን ትርጓሜ ባለቤቱን ጠየቀው ፤ ባለቤቱም ልጁን ከባሕር እንዳገኘውና በዚህ ምክንያት ‘‘ባሕራን’’ ብሎ እንደሰየመው ገለጸለት በዚህ ጊዜ ያ ክፉ ባለፀጋ ደነገጠ ። ምን ማድረግ እንደሚገባው ያወጣ ያወርድ ጀመረ ። ወዲያው አንድ ሐሳብ መጣለትና ለባለቤቱ ጥያቄ አቀረበ ጥያቄውም ከቤቱ የረሣሁት ነገር ስላለ ይህንን ልጅ ወደ ቤቱ ልላከው የድካሙን ዋጋ እከፍላለሁ የሚል ነበር ፤ ባለቤቱም የእንግዳውን ተንኮል አያውቅምና



www.ethiopianorthodox.org

በጥያቄው ተስማማ ፣ ልጁን እንዲልከው የባለቤቱ ፈቃድ መሆኑን ሲረዳ ደብዳቤ ይጽፋል ፣ ደብዳቤውም "ይህንን ደብዳቤ ይዞ የመጣውን ሰው ማንም ሰው ሳይሰማ ገድላችሁ ቅበሩት" የሚል ነበር ።

ባሕራን ጦማረ ሞቱን ተሸክሞ ወደ ተላከበት አገር ሲሄድ የአንድ ቀን መንገድ ሲቀረው ቅዱስ ሚካኤል በሰው አምሳል ተገለጠለት ። የት እንደሚሄድም ጠየቀው ፤ ባሕራንም አንድ ባለጸጋ ሰው ወደቤቱ እንደላከውና የእርሱን መልእክት ለማድረስ እንደሚሄድ ነገረው ፤ እስኪ ደብዳቤውን አሳየኝ አለው ባሕራንም ደብዳቤውን አውጥቶ አሳየው ፤ መልአኩ ባየው ጊዜ "ማንም ሰው ሳያይና ሳይሰማ ገድላችሁ ቅበሩት ይል የነበረው" ይህን ደብዳቤ ይዞ ለመጣው ሰው ልጄን እገሬትን ሰጥቸዋለሁና እንደደረሰ አጋቡት ቤቴን ንብረቴንና ሀብቴንም ሁሉ አውርሸዋለሁና ሁሉን ስጡት በቤቱና በንብረቴ ሁሉ የፈለገውን ያድርግ አትከልክሉት" በሚል ጽሑፍ ተተካ ባሕራን ደብዳቤውን ይዞ ከባለጸጋው ቤት ደረሰ ፤ እንደ ደረሰም የደብዳቤው ቃል ተፈጸመለት ከዚህ በኋላ ባሕራን ዓሥራቱን በኩራቱን እያወጣ በቅዱስ ሚካኤል ስም ቤተ ክርስቲያን አሳንጾ እግዚአብሔርን በማገልገል ነዳያንን በመርዳት የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ በቅቶአል ።

ከዚህ ላይ ባሕራን በተቈለፈ ሣጥን በባሕር ሲጣል ያለ አየር ብዙ ቀን እንዴት ሊቆይ ቻለ ? ደግሞስ ያልደከመበትን የሰው ሀብት እንዲወርስ እንዴት የእግዚአብሔር ፈቃድ ሊሆን ቻለ ? የሚል በአንባቢያን አእምሮ ይፈጠር ይሆናል ። መልሱ ግን እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ ነው ። ስለሆነም እርሱ ሕይወት ሰጥቶ የፈጠራትን ነፍስ አየር በሌለበት መጠበቅና ማኖር እንደሚችል እናምናለን ። እንዲሁም በገንዘባቸው እንደሚገባ የማይሠሩበት ባለጸጎች ሁሉ በማይገባ የሰበሰቡት ሀብት ለሌላ ተጠቃሚ እንደሚሰጥ በቅዱስ መጽሐፍ ተጽፎ አል መዝ. 48 ፥ 10 ሉቃ. 12 ፥ 21

መላእክት የተፈጠሩት ለተልእኮ እንደሆነና ተልእኮአቸውም በሁለት አቅጣጫ ማለት ለምሕረት ወይም ለመዓት እንደሚሆን ተገልጦአል ፤ አንዱ መልአክ ፤ መልአከ ምሕረት ወይም መልአከ መዓት ሁኖ ሊላክ ይችላል ። ስለ እግዚአብሔርና ስለ ጽድቅ የሚገፉ ምእመናን ወደ አሉበት መልአከ ምሕረት ሁኖ ለማዳን ለማጽናናት ለተራድኦ ሲላክ እግዚአብሔርን ባለመፍራት ጽድቅን ባለመቀበል ፍርድን በማጣመም ሌሎችን የሚበድሉና የሚያንገላቱ ወደ አሉበት ግን መልአከ መዓት በመሆን ለተግሣጽ ፤ ለቅጣትና ለጥፋት ይላካል።

ይህንን ለመረዳት ቅዱስ ሚካኤል ለእስራኤል መልአከ ምሕረት ፤ ለሰብአ ግብፅ መልአከ መዓት ፡ ለሕዝቅያስ ነመልአከ ሣህል ፡ ለሰናክሬም መልአከ ኃጉል በመሆን እንደተላከ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጦአል ከዚያም ወዲህ እንደ ባሕራን ላሉት ግፉዓን ለአድኅኖ ሲላክ እንደ ከፋው ባለጸጋ ላሉት ገፋዕያን ለተግሣጽ እንደሚላክ በቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ተጽፎአል ።

ስለዚህ መላእክት ለምሕረትና ለተራድኦ ወደ ሰዎች እንዲላኩ ሰዎች ታዛዦችና ዕውነተኞች መሆን አለባቸው መላእክትን ለምሕረት ወይም ለመዓት የሚጋብዝ የሰዎች መታዘዝና አለመታዘዝ ነው ። ይህም ከታወቀ እያንዳንዱ ምእመን ሌላውን ከመበደል ቢታገሥ የመላእክት ተልእኮ ለምሕረት ብቻ ይሆናል ።

ከሌሎች መላእክት ይልቅ ቅዱስ ሚካኤል መልአከ ምሕረት ወሣህል ነው እንዲያውም በርኅራኄው ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ይነጻጸራል ። "ንዒ ሠናይትየ ምስለ ገብርኤል ፍሡሕ ወሚካኤል ከማኪ ርኅሩኅ እመቤቱ ሆይ ደስ ከሚያሰኘው ከገብርኤልና እንደ አንቺ ርኅሩኅ ከሆነው ከሚካኤል ጋር ነዪ" ተብሎ ተጽፎአልና።

ራደ አስረስ

## በዐለ ሃምሳ ...

ከገጽ ፲፫ የዞረ

የክርስትና በዓል ያስታውሱናል ።

በሦስተኛው መቶ ዓመት ፍጻሜ ገደማ "ኤልቤራ" በተባለው ቦታ በተደረገው የጉባኤ ውሳኔ በ43ኛው አንቀጽ፣ እንዲሁም በአራተኛው መቶ ዓመት ማለት እንደ ኤሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር በ325 ዓ.ም. በኒቂያ በመጀመሪያው ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን የጉባዔ ውሳኔ በ20ኛው አንቀጽ በዚህ በዓል ስግደት ማድረግ እንደማይገባ ያስጠነቅቃል ።

በአራተኛው መቶ ዓመት የነበረው ቅዱስ ባስሊዎስ ስለዚሁ በዓል ሰፋ ያለ ሐተታ በስነ ጽሑፍ አስፍሮአል ። ቅዱስ ኤጲፋንዮስና ሌሎችም ቅዱሳን አበው ስለዚሁ በዐል አከባበር የስነ ጽሑፍ መረጃዎችን ትተውልናል።

ይህ በዐለ ጰራቅሊጦስ በጥንታዊነቱ ብቻ ሳይሆን በዐቢይነቱም ከበዐለ ትንሣኤ ቀጥሎ የሁለተኛነት ደረጃ የያዘ መሆኑን ታሪክ ይነግረናል ። ከዚህም በዐል ዋዜማ ጀምሮ በዐሉ ፍጻሜ እስከሚያገኝበት ድረስ ለግብረ አሕዛብ ተስማሚ የሆኑት ዳንኪራዎች ፤ እስፔክታኩሎችና የመሳሰሉት ሁሉ በትያትር ቤቶች ፤ በኦፔራዎች ፤ በኦፔራታዎች እንዳይከናወኑና እንዳይታዩ የተከለከሉ እንደነበር ከክርስትናው የኪነ ጥበብ ታሪክ እንረዳለን ።

ክርስቲያናት ከዚህ በዐል ዋዜማ ጀምረው የደስታ ምልክቶች በሆኑ ነገሮች ማለት እንደአበባዎችና በመሳሰሉት የቤቶቻቸውን ውስጥና ውጭ ያስጌጡቸው እንደነበር አሁንም ከክርስትናው የኪነ ጥበብ ታሪክ መረዳት እንችላለን ።

ዛሬም ቢሆን በምሥራቅ ኤውሮፕ የሚገኙ ክርስቲያናት በዚሁ ዕለት ኑክ" ከሚባለው ዛፍ (ይህም ዛፍ በሀገራችን የሚገኝ አይመስለኝም) ቅርንጫፎቹን እየያዙ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ ፤ ሰብስበውም በመቅደሱ ደጃፍ ያስቀምጡታል ። ጸሎተ ቅዳሴው ከተፈጸመ በኋላም ቄሱ ዝንጣፊዎቹን ይባርክና ለምእመናን ያከፋፍላቸዋል ። እነርሱም ይህኑ ዝንጣፊ በመያዝ ወደ የቤታቸው ይመለሳሉ ። ይህም መንፈስ ቅዱስ እንደ እሳት በሐዋርያት ላይ የመውረዱ ምሳሌና መታሰቢያ አድርገው መቅረባቸው መሆኑ ይነገራል ።

በመሠረቱ የበዐሉ አመሠራረትና አመጣጥ ይህ ሆኖ ሳለ ለመታሰቢያነቱ በየዓመቱ በሚከበረው በዚህ ታላቅ የክርስትና በዐል አንዳንድ "ጰንጤቆስጤ" በሚል ስያሜ ኒዎ - ፕሮቴስታንት የሆነ የሃይማኖት ድርጅት በመመሥረት በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን መካከል የዕምነት ትምህርታቸውን ለማሠራጨት በመጣር ላይ ይገኛሉ ። በበዐሉ ስያሜ የሚጠራው የአምልኮትድርጅትም መቼ ነው የተመሠረተው ? መሥራቹስ ማን ነው ? ብለን ብንጠይቅ ይህ የሃይማኖት ድርጅት የተጀመረው አሁን በቅርብ በያዝነው መቶኛ ዓመት መጀመሪያ ማለት በ 1906 ዓ.ም. ገደማ መሆኑን ታሪኩ ይነግረናል ።

የዚህም የኒዎ - ፕሮቴስታንት ዶግማ (የሃይማኖት ትምህርት) የተመሠረተው በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅና በቋንቋዎች ትንቢትን መናገር በሚል መነሻነት ነበር ። ይህም የአንድ መቶ ዘመን እንኳ ታሪክ የሌለው የአምልኮት ድርጅት በአንዳንድ ሰዎች አማካይነት በአሜሪካ ፡ በኢንግላንድና በመሳሰሉት ሀገሮች በአጭር ጊዜ ውስጥ በታክቲክ መስራጨቱን ቀጠለ ።

እንግዲህ ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ሰባት ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሲኖሯት ከነዚህም አንዱና የመጀመሪያው (ምሥጢረ ጥምቀት" ነው ። ይህም ምሥጢር የክርስቶስ ወገን የሚያደርግ ሲሆን ይህም በመንፈስ ቅዱስና በእሳት መጠመቅ (ማቴ.3.11) ወይንም ከውሀና ከመንፈስ ቅዱስ መወለድ ነው (የሐ. 3.5)

በጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን ሦስቱ የመጀመሪያዎቹ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ማለት ምሥጢረ ጥምቀት ፤ የአዲሱን አማኝ ሰውነት በቅዱስ ሜሮን የመቀባቱ ምሥጢርና ምሥጢረ ቁርባን እነዚህ ሦስቱም ምሥጢራት በቅደም ተከተል በአንድ ጊዜ ለአዲሱ አማኝ በቄሱ የሚፈጸሙ ናቸው ። ታዲያ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ማለት ከዚህ የተለየ ምን ምሥጢር አለ ?

ትንቢት የመናገር ስጦታ ለማንም የማይሰጥ የመንፈስ ቅዱስ በረከት ሁኖ በቀጥታ ከእግዚአብሔር የሚመጣውን የእግዚአብሔር አፍ ሁኖ መልእክቱን ማስተላለፍ ነው ። ስለዚህ ትንቢት የተዘጋጀ ስብከት አይደለም ። ያለ ዝግጅት ያለ ጥናት ከእግዚአብሔር የሚመጣ ነው ። የእግዚአብሔር ነቢይ ሆኖ ትንቢት ተናጋሪ ለመሆንም ብቃትን ፤ ንቃትን ፤ ፍጹምነትን ይጠይቃል ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ጠርቶ ለአገልግሎት በላካቸው ጊዜ በዕለት ሥራቸው ላይ የሚጠቀሙበትን መመሪያ ሲሰጣቸው ".... የምትናገሩት በዚያች ሰዓት ይሰጣችኋልና እንዴት ወይስ ምን እንደምትናገሩ አትጨነቁ ፤ በእናንተ የሚናገር የአባታችሁ መንፈስ ነው እንጂ የምትናገሩ እናንተ አይደላችሁም" ይላል (ማቴ. 10.20)

ዛሬም እግዚአብሔር ሐዋርያቱን በተመሳሳይ መንገድ ስለሚመራቸው እኛም ለሐዋርያት የተሰጠውን የዘወትር ቋሚ መመሪያችን አድርገን እንድንጠቀምበት ያስፈልጋል ።

የበዐላት አከባበርም ከሰው ሕይወት ጋር ተያይዞ የመጣ ትርጉምና ዋጋ ያለው ስለሆነ ምሥጢሩንና መጠኑን አውቀን እናክብረው ።

ዶክተር ግርማ ወልደ ቂርቆስ

---

## ደብዳቤዎች

ከገጽ ፭ የዞረ

ግልጽ እንድታደርጊ እያሳሰብንሽ ዓላማሺን ግልጽ ካደረግሽ በኮሌጁ ገብተሽ ለመማር መቻል አለመቻልሽን በዚያን ጊዜ ጠይቀን በመጽሔታችን የምናወጣልሽ መሆኑን እንገልጻለን ።

▫▫▫▫

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ

አዲስ አበባ

አዛውንቶቻችን በሚል ርእስ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ዜናን እያዘጋጃችሁ ለአንባብያን የምታቀርቡት ሐተታ በጣም ጥሩ ነው ። ግን ያለፈውን ብቻ ከማተት በአሁኑ ጊዜ ተተኪ ሊቃውንቶች የሚገኙበትን መንገድ መቀስቀስ በይበልጥ ጥሩ ነው እላለሁ ።

ለዚሁም መግቢያ ሃሳብ ለማግኘት ያስችለኝ ዘንድ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አቅርቤአለሁ ።

1ኛ/ ለአንባብያን የሚቀርቡትን አዛውንቶች በዕውቀት የሚተካ ፤ ወይም እነሱ የገበዩትን ዓይነት ዕውቀት ለአሁኑ ትውልድ የሚያስተምሩ ስመ ጥሩ መምህራን ሆኑ ተቋሞች በኢትዮጵያ ውስጥ አሉ ወይ?

2ኛ/ ካሉስ የት ነው የሚገኙት?

3ኛ/ እነሱንስ ለማበረታታት ከሚመለከተው ክፍል የተደረገው ጥረት ምን ያህል ነው?

ሙሉጌታ መለሰ ከደ.ማ.

● አቶ ሙሉጌታ መለሰ ፤ ከሁሉ በፊት መጽሔታችንን ተከታትለው በማንበብ ይህንን ጠቃሚ ጥያቄ በማቅረብዎ እናመሰግናለን ።

ከሁሉ በፊት በመጽሔታችን ያለው ዓምድ ሊቃውንቶቻችን የሚል እንጂ አዛውንቶቻችን የሚል አይደለም ።

ስለፍሬ ጥያቄው 1ኛ ያለፉትን ሊቃውንት ታሪክ ብቻ ሳይሆን ያሉትንም ሊቃውንት ታሪክ ጭምር እናቀርባለን ወደፊት እንዲያውም ያሉትን ሊቃውንት ታሪክና አገልግሎት በሰፊው የምናቀርብ መሆናችንን በደስታ እንገልጻለን ።





www.ethiopianorthodox.org

እነርሱን የተኩ ሊቃውንትም ሆነ የ ትምህርት ተቋሞች አሁንም አሉ ፤ ለም ሳሌ የአራቱ ጉባዔያት መምህር በጎንደ ር ከተማ በማስተማር ላይ ይገኛሉ ት/ ቤቱም እንደነበረ አለ ። በሌላው በኩል ም የዜማው ማስመረቂያ ቤተ ልሔም መምህራኑም ከቀድሞው ባልተለወጠ ሁኔታ መምሕራንን በማስመረቅ ሲገኝ ከዚሁ ቦታ ጥቂት ራቅ ብሎ የሚገኘው የዝማሬ መዋስዕቱ ማስመረቂያ ዙ ር አንባ ስራውን እንደቀጠለ ይገኛል ።

በአጠቃላይ የቅኔ መምሕራንና ት/ ቤቶች በጐጃም ፤ በጐንደር በሌሎቹም ክፍላተ ሀገር ከቀድሞው ባልተለወጠ ሁኔታ ሊቃውንቱ ሊቃውንትን እየተኩ የሚገኙ መሆናቸውን እገልጽልዎታለ ሁ ።

ግን በ3ኛው ጥያቄዎ እነርሱን ለማበ ረታታት በሚመለከተው ክፍል የተደ ረገ ጥረት አለወይ ? የሚለው እስከአ ሁን ድረስ የተደረገውን ጥረት የሚመ ለከተው ክፍል እንዲያብራራልን ጥ ያቄዎን እንዳለ አውጥተነዋል ።

~•~

የአምላካችን ጸጋና በረከት ከናንተ ጋር እንዲሆን የዘወትር ምኞቴ ነው ።

ከዚህ የሚቀጥሉትን ጥያቄዎች እን ደምትመልሱልኝ ባለሙሉ ተስፋ ነኝ።

1ኛ/ አንድ ሰው በዚህ ዓለም ሲኖር መ ላ ዘመኑን በኃጢአት በክሎ ይኖራል እንበል ነገር ግን የተጠቀሰው ሰው ተ ጠምቆ ስለ ኃጢአት በመሥራት ኑሮ በሰሙነ ህማማት ከዚህ ዓለም ቢለይ ይጸድቃል ወይስ ይኰነናል ።

2ኛ/ አንድ ሰው ከተጠመቀ በኋላ ኃ ጢአት ከሠራ የንስሐ ጥምቀት መ/ቁደ ር መጠመቅ ይኖርበታል እንጂ እንደ ት ማለቴ የመጽሐፈ ክርስትና ጥምቀት እንዴት ለመጠመቅ ይችላል ይህንም የጠቀስኩት አንዳንድ ቀሳውስት የንስ ሐ ልጆቻቸውን ኃጢአት ሠርተናል መ ቁደር እንጠመቅ ሲሉ የተጠቀሰውን የ ጥምቀት ጠበል ነው ሲጠምቁ እማየው ይህ ሊሆን ይችላል?

3ኛ/ በዘመናችን ጾም እየተሻረ ከመ ሄዱ የተነሣ በጾመ ሁዳዴና በሌሎቹም አጽዋማት ከብት እየታረደ ሥጋ እንደ ጐመን ሲቀረደድ እንመለከታለን ይህ ህም እርስዎ ካሉበት ከተማ ጀምሮ እኔ እስካለሁበት ከተማ ድረስ የሥጋ ሱቆ ች ተከፍተው ጾም ሲሻር የቤተ ክህነት ኃላፊዎች ዝም ብሎ ማየት ተገቢ ነው?

በሌሎች ከተሞች ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ሥጋ እንዳያርድ የተከለከሉ አሉ ለምሳሌ በወሎ ክፍለ ሀገር በደሴ ከተ ማ ለጐብኝት ሄጀ ተዘዋውሬ ተመልክ ቻለሁ ታዲያ ይህ ሁሉ የሥጋ መታረድ በተጠቀሰው በደሴ ከተማ የለም በአዲ ስ አበባና በሞጆ ብቻ ነው የጠነከረው እኔ በዚህ ከተማ የንስሐ ልጆቼ ተበሳ ጩብኝ ምክንያቱም እገሌ ከበላ እገሌ ካረደ በማለት በድብቅ ተለቀቁበት እኔ እድፈቱን ሁሉ በማወግዝበት ጊዜ አላደረኩም አልፈጠርኩም ይላሉ እባ ክዎት የትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ ይ ህን ሁኔታ በማበጠር መልሱን በፍጥነ ት ይላኩኝ የመጽሔትዎ ተከታታይ ቄስ ተመስገን ደምሴ ።

-ቄስ ተመስገን ደምሴ ስለአቀረቧቸ ው ጥያቄዎች እናመሰግናለን ያቀረቧ ቸው ጥያቄዎች ሁሉ ተገቢዎች ናቸው

1ኛ/ የሰው ልጅ ሊድን የሚችለው በመ ጠመቁ ብቻ አይደለም የሚድነው በጥ ምቀት ያገኘውን ልጅነት በሚገባ ጠብ ቆ ከኃጢአት ነጽቶ ሲኖር ነው ስለዚህ በሰሙነ ሕማማትም ሆነ በሌላ ጊዜ ቢ ሞት ኃጢአት ሠርቶ ንስሐ ሳይገባ ከሞ ተ ይኰነናል እንጂ ሊጸድቅ አይችልም።

2ኛ/ ጠያቂው እንዳሉት ኃጢአት በ ሠሩ ቁጥር መጽሐፈ ቄደር እየደገሙ ማጥመቅ ተገቢ አይደለም መጽሐፈ ቄ ደር የሚታዘዝላቸው ኃጢአቶች እጅግ በጣም ከባድ ለሆኑ ብቻ ነው እንጂ ለ ማንኛውም ኃጢአት መጽሐፈ ቄደር እንዲደገም የሕግ መጽሐፋችን አያዝ ምና በኃጢአቱ ሁሉ መ/ ቄደር የሚደ ግሙ ቀሳውስት ካሉ እንዲታገሡ እናሳ ስባለን ።

3ኛ/የቤተ ክርስቲያን ኃላፊዎች ሥ ጋ በጾም መብላት ክልክል መሆኑን ለአ ማኞች መናገር ነው እንጂ እንደ ሥጋ ዊ ዳኛ እሥር በገመድ አግባ በግንድ በማለት ሊያስገድዱ አይችሉም ሐዋር ያትም ሥራቸው ማስተማር እንጂ ማስ ገደድ እንዳልሆነ ሲያስረዱ "ንሕነ ንነ ግር ወኢንዘ ብጥ" እኛ እንናገራለን እ ንጂ አንደባደብም ብለዋል ።

ጠያቂው ሌላውን እየተመለከቱ የን ስሐ ልጆቼ ተበላሹብኝ ብለዋል አንድ ሰው ገደል ገብቶ ሲሞት ሌላውም አብ ሬ ተንከባልዬ ልሙት አይልም ወደጥ ፋት ገደል እየተሽቀዳደሙ የሚገቡትን ሰዎች ተከትለው እንዳይገቡ ልጆችዎን በትምህርት የመጠበቅ ኃላፊነት አለበ ዎትና ጠንክረው ይጠብቁ አላደረኩም አልበላሁም እያሉ በድብቅ ቢበሉ የሚ ጐዱት ራሳቸውናቸውና ለድብቁ ተ ግባር እርስዎ ኃላፊነት የለብዎትምና የሚያዩትን ብቻ ይቃወሙ እንጂ በድ ብቅና በአሉባልታ ተሠርቷል እየተባለ በምዕመናኑ ላይ የሚቀርበውን አይቀ በሉ ።

## የቅኔ መምህር

ከገጽ ፲፩ የዞረ

ኞች ለተወሰኑ ወራቶች የውዳሴ ማርያም እና የቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ ስትማር ቆይታ አሁን በቅኔ መምህርነት ለመመ ረቅ ቅኔውን በማስተካከል አገባብ ትቀ ጽላለች ።

ይቀጥላል

ብርሃን ተድላ



## የብፁዕ ወቅዱስ ...

ከገጽ ፲፯ የዞረ

ያው ተገኝተው የክብር አሸኛኘት አድ ርገውላቸዋል ። ቅዱስነታቸው በግሪክ ቤተ ክርስቲያን አስተናጋጅነት የሰንበ በቱበትን ጊዜ ከመልቀቃቸው በፊት ለገዳሙ ኃላፊና ለሌሎቹም የመታሰ ቢያ ስጦታ አድርገዋል ።

**ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ጉብኝታቸውን ፈጽመው ሲመለሱ በቦሌ አይሮፕላን ጣቢያ የተደረገ አቀባበል**

ታቸውን ፈጽመው ሲመለሱ በቦሌ አይሮፕላን ጣቢያ የተደረገ አቀባበል።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይ ማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በኢ የሩሳሌምና በአቴንስ የሚያደርጉትን ጉብኝት ፈጽመው ሚያዝያ ፲፱ ቀን ፸፪ ዓ/ ም/ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ ቤት አስቀድሞ በወ ጣው መርሐ ግብር መሠረት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት፣የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ ቤት ባለሥልጣናትና ሠራተኞች፣የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐ ዋርያዊ ድርጅት ሠራተኞች፣ የአድባ ራት አለቆች ፣ ካህናትና ምእመናን በቦሌ ዓለም አቀፍ አይሮፕላን ጣቢያ ተገኝተው ከፍ ያለ የክብር አቀባበል አድርገውላቸዋል ። በዚህም ጊዜ ሕ ፃናት ዕቅፍ አበባ ለቅዱስነታቸው አበርክተዋል ። ቅዱስነታቸው ከአ ይሮፕላን ወርደው በአይሮፕላን ጣ ቢያው ልዩ ሳሎን እንደአረፉ ስለጉብኝታቸው ከጋዜጠኞች ለቀረ በላቸው ጥያቄ መልስ ሰጥተዋል ። በሰጡትም መልስ በኢየሩሳሌም ያደ ረጉት ጉብኝት አስደሳችና መልካም ውጤት ያለው መሆኑን ገልጸዋል ። ከዚያም በክብር ታጅበው ቅድስተ ቅዱ ሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን እንደደ ረሱ በሥፍራው ተሰብስቦ ይጠባበቅ የነበረው ሕዝብ በጭብጨባና በል ልታ እንዲሁም ፤ ከአዲስ አበባ አድባ ራት የተውጣጡ ልብሰ ተክህኖ የለ በሱ ካህናትና መዘምራን በዝማሬ ተቀ በሏቸው ።

ቅዱስነታቸው ቤተ መቅደስ ገብ ተው የምስጋና ጸሎት ካቀረቡ በኋላ በመንበረ ፓትርያርኩ ስለ አቀባበሉ በተዘጋጀው የክብር ቦታ እንደተገኙ ጥንግ ድርብ ለብሰው በአደባባዩ የተ ሰለፉ መዘምራን ።

«ብፁዕ ወቅዱስ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ዘሐወፅካ ለኢየሩሳሌም ምስለ ሊቃነ ጳጳሳቲነ ከመወርኀ ንጹሕ ወከመ ኮከብ ብሩህ በጸሎትከ ትድኀን ወኢትማስን ሀገር »

የሚለውን ግሥ ገሠው ለሃያ ደቂቃ ያህል አሸበሸቡ ፤ የካህናቱ ማኅሌ ታዊ ሽብሸባ እንደተፈጸመ የሰላም አባት እንኳንደህና መጣህ «የሚል ከወጣቶች መዘምራን የቀረበ አስደሳች መዝሙር ተሰማ ፤ መዘምራኑ ከአዲስ ጣበባ አድባራት የወጣቶች መንፈሳ ውያን ማኅበራት የተውጣጡ ሲሆኑ በአቀባበሉ ላይ ረጅምና ነጭ የሰልፍ አብስ (ዩኒፎርም) ለብሰው በራሳቸው ላይ ቀጸላ አድርገው በሰልፍ በመቆም ያሰሙት መዝሙር ሕሊናን የሚመስጥ ሲሆን በሁኔታው ቤተ ክርስቲያን በወ ጣቶች በኩል ያላትን የወደፊት ተስፋ ፍጹም የሚያደርግ ነበር ።

ከመዝሙሩ በኋላ በመርሐ ግብሩ መሠረት በመጀመሪያ አቶ መርሥኤ ኀዘን አበበ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ተ/ ዋና ሥራ አስኪያጅ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩን እንኳን ደኅና መጡ በማለት በመላው የቤተ ክህነት ሠራ ተኞች ስም ንግግር አደረጉ ።

አቶ መርሥኤ ኀዘን አበበ የጠቅ



ቅዱስነታቸው በቦሌ አይሮፕላን ማረፊያ ሣሎን ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጡ

ላይ ቤተ ክህነት ተ/ ዋና ሥራ አስኪ ያጅ ባደረጉት ንግግር « ቅዱስነትዎ ለጉብኝት ከሔዱበት ሀገር በሰላም እንዲመለሱ ከ፲፰ ሚሊዮን በላይ የሚ ሆኑ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስ ቲያን ተከታዮች ሁሉ ምኞትና ጸሎት ስለነበር የቅዱስነትዎ በሰላም መመለስ የመላው ምእመናን ታላቅ ደስታ ነው።

ቅዱስነትዎ በቅድስት ሀገር ያደረ ጉት ጉብኝት ለቤተ ክርስቲያናችን፣ ታላቅ ክብር ስለሆነ ሁላችንንም ደስ ብሎናል» ብለዋል ። ኢየሩሳሌም ጌታ ችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን በቅዱስ ደሙ የዋጀባት ቅድስት ሀገር ስለሆንች በዚህች ቅድስት ሀገር ክርስቶስ ከል ደቱ እስከ ዕርገቱ እያሌ ተአምራት ያደረገባቸውን ታሪካውያን ቅዱሳት መካናትንበይፋ በመጐብኘትና ስለዴር ሡልጣን ገዳም ጉዳይም በከፍተኛ ደረጃ ለመነጋገር ይህ ዓይነቱን ታሪ ካዊ ጉዞ በማድረግ የመጀመሪያው ፓትርያርክ ቅዱስነትዎ በመሆኑ ለዚህ ታሪካዊ ጉብኝት የመጀመሪያው ባለ ታሪክ ቅዱስነትዎ ነው ፤ ቤተ ክርስቲ ያን ራስዋን ለመቻል ጥረት በምታደ ርግበት በአሁኑ ወቅት የቤተ ክርስ ቲያን መሪዎች የሰለጠኑና የተደራጁ ሀገሮችንና አብያተ ክርስቲያናትን ለመጐብኘት የሚያደርጉት የውጭ ሀገር ጉብኝት ለቤተ ክርስቲያናችን ታላቅ ጥቅም ያስገኛል በማለት የቅ ዱስነታቸው ጉብኝት ያስገኘውንና የሚያስገኘውን ውጤት በሰፊው ከገ ለጹ በኋላ በንግግራቸው መጨረሻ ላይ ከሁለት ዓመት በፊት በነበረው ጊዜያዊ ጉባኤ የቤተ ክርስቲያን ሊቃ ውንት ተሰባስበው ለቤተ ክርስቲያና ቸው እንዲሠሩ ሙከራ ቢደረግም እስከ አሁን ሙከራው ውጤት ባለመ ስጠቱ የቤተ ክርስቲያን ሥራ ሊቃና አለመቻሉን በማሳሰብ ምንጊዜም የሊቃውንት መሰባሰብ ለቤተ ክርስቲ ያን ችግር መድኀን መሆኑን የሚጠ ቁምና ሕሊናንም የሚቀሰቅስ አንድ መወድስ ቅኔ አበርክተዋል ።

የአቶ መርስኤ ኀዘን አበበ ንግግርና ቅኔ እንደተፈጸመ በመርሐ ግብሩ ቅ ደም ተከተል መሠረት በሐዋርያዊ ድርጅት ሠራተኞች ስም አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ እንዲሁም የተለያዩ ሊቃ ውንት ስለቅዱስነታቸው ጉብኝት የተ ሰማቸውን ደስታ በመግለጽ ንግግር ካደረጉ በኋላ ሌሎች የተለያዩ ሊቃው ንት ደግሞ እየቀረቡ መወድስ ቅኔ አበ ርክተዋል ።

ከዚህ በኋላ ብፁዕ አቡነ ጐርጐር ዮስ የሸዋ ሀገረ ስብከት ጳጳስና ከተከ ታዮቹ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት አንዱ ስለጉብኝቱ መልካም ውጤት በመግ ለጽ ንግግር አደረጉ ።

ብፁዕ አቡነ ጐርጐርዮስ በተለይ ስለ ዴርሱልጣን ገዳም ጉዳይ ባደረ ጉት ንግግር የዴርሱልጣን ገዳምችግር ሊፈጠር የቻለው በጉብኝታውያን ብቻ ሳይሆን ከእኛም እያያዝ ጉድለት ጭ ምር ነው ፤ እኛበሚገባ መያዝ ባለመ ቻላችን የተነሳ በጐልጐታ ከ፮ አብያ ተ ክርስቲያናት በላይ ተወስደውብ ናል ፤ ስለዚህ አሁንም የዴርሱልጣን ገዳማችንን እንዴት እንያዘው ? በሚ ለው ጥያቄ ላይ ተወያይተን ለወደፊቱ መደራጀት አለብን ብለዋል ። በአቴ ንስ ስለተደረገው ጉብኝትም ብፁዕ አቡነ ጐርጐርዮስ ሲናገሩ ብፁዕ ወቅ ዱስ ፓትርያርኩ አቴንስ ሲደርሱ በግ ሪክ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያልታ ሰበ አስደሳች አቀባበል እንደ ተደረገ ላቸውና በአቴንስ ከተማ የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ እንግዳ መቀበያ በሆነው ገዳም የማረፊያ ቦታ በማዘጋ ጀትም በክብር እንደአስተናገዱዋቸው አስረድተዋል ። የውጭ ሀገር ሰዎች በተለይ በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ላይ ስላላቸው አድናቆት ብፁዕ አቡነ ጐርጐርዮስ ለተሰበሰበው ሕዝብ ሲና ሩ ቅዱስነታቸው በምናኔና በተባሕ ትዎ ሰውነታቸውን ገዝተው የኖሩ መ ሆናቸው በሀገር ውስጥ በግልጽ የታ



ቅዱስነታቸው በአቀባበሉ ሥነ ሥርዓት ላይ ቃለ ቡራኬ ሲያደርጉ



www.ethiopianorthodox.org

ወቀ ቢሆንም የውጭ ሀገር ሰዎችም ጸቸውንና አመጋገባቸውን አይተው ሰብዓዊ ፍጡር እንደዚህ ተመገቦ ከእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል ካልተሰጠው በቀር መኖር የማይችል መሆኑን ተገንዝበው በቅዱስ ነታቸው መንፈሳዊ ሕይወት መደነቃቸውን ገልጸዋል በመጨረሻም ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ለተሰበሰበው ሕዝብ ቃለ ቡራኬ ሰጥተዋል ። ቅዱስነታቸው ባሰሙት ቃለ ቡራኬ በጉብኝታቸው ወቅት ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር ሆነው ክርስቶስ ከተወለደበት እስከ ተጠመቀበትና እስከ ተሰቀለበት እንዲሁም ከተነሳበት እስከ አረገበት ጊዜ ድረስ ያደረገውን ሁሉ ለድኅነት ዓለም ሥራየፈጸባቸውን ቅዱሳት መካናትን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስም ጎብኝተው በመመለሳቸው የተሰማቸውን ደስታ ገልጸዋል ። ተጥሎም ቅዱስነታቸውበአቴንስ ስለ አደረጉት ጉብኝት በመቀጠል አቴንስ ከተማ ሲገቡ በግሪክ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣናት የተደረገላቸው የወንድነት አቀባበልና መስተንግዶ ከልብ ያስደሰታቸው መሆኑን አስረድተዋል ። በጉብኝታቸውም ወቅት ባዩት ሁሉ ደስ የተሰኙመሆናቸውን ቢገልጹም በተለይ የካህናት ማሰልጠኛው ት/ ቤት እጅግ በጣም ያስደሰታቸው መሆኑን ጠቅሰው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ተከታዮች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ካህናትና አብያተ ክርስቲያናት ያሏት ስትሆን አንድም እንኳ ቀዋሚ የካህናት ማሰልጠኛ ኮሌጅ የሌላት መሆኑን በቅሬታ በማስታወስ በተቻለ መጠን የካህናት ማሰልጠኛ ኮሌጅ እንዲኖራት ጥረት የሚደረግ መሆኑን አብስረዋል። እንዲሁም በዚህ ጉብኝታቸው በአቴንስ ከተማ የሚገኘውን የቤተ ክርስቲያኒቱን ማተሚያ ቤትና ቅዱስ ጳውሎስ በግብረ ሐዋርያት ም- ፲፯ ቁ- ፲፱እንደተገለጸው በክርስትና ዓለም ላይ አስደናቂ የሆነውን ትምህርታዊ ንግግር ያደረገበትን አርዮስ ፋጉስንና እንዲሁም ቆሮንቶስን በመጎብኘታቸው የተሰማቸውን ደስታ ቅዱስነታቸው ባሰሙት ቃለ ቡራኬ ገልጸዋል ። ከዚህ በኋላ የአቀባበሉ ሥነ ሥርዓት ፍጻሜ ሁኖ ሠርሀተ ሕዝብ ሁኗል ።

በዚህ ዕለት ከቀኑ በ፯ ሰዓት ስለቅዱስነታቸው የአቀባበል ክብር በመንበረ ፓትርያርኩ አዳራሽ የምሳ ግብዣ ተደርጓል ፤ በግብዣውም ላይ ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት በኢትዮጵያ የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስና ሌሎችም ጥሪ የተደረገላቸው የእድባራት አለቆች ተገኝተዋል ።

# ዜና አብያተ ክርስቲያናት

ከገጽ ፲፪ የዞረ

200ኛ ዓመቱን በመጪው ጥቅምት ወር ላይ በፈረንሳይ በተለይ አቬን በተባለች ከተማ ለአንድ ሳምንት እንደሚያከብር ታውቋል ። በበዓሉም ላይ የዓለም አብያተ ክርስቲያናትና የዓለም ሉተራውያን ፌዴሬሽን ከፍተኛ ባለሥልጣኖች የሚገኙ ሲሆን በተጨማሪም ከ120 - 150 ሰዎች በበዓሉ ላይ ተካፋይ እንደሚሆኑ ኢ.ፒ.ኤስ የተባለው ጋዜጣ በ11/47ኛ ቁጥሩ ገለጸ ።

**ሎንዶን**

የሮማ ፓፓና አዲሱ የካንተር ቨሪው ሊቀ ጳጳስ (የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ) በግንቦት ወር በአክራ ተገናኝተው በአንድ ላይ እንደጸለዩና እንደተወያዩ ከሎንዶን ተገለጸ ።

ሁለቱ የአብያተ ክርስተያናት መሪዎች በአክራ ሊገናኙ የቻሉት የአፍሪካ አህጉርን ሲጐበኙ በነበሩበት ወቅት መሆኑን ኢ.ፒ.ኤስ ገለጸ ።



# ሊቃውንታችን

የታላቁ ሊቅና የብፁዕ አቡነ ሚካኤል የቀድሞ ስማቸው መምህር ክፍለ ገሪማ /ዜና ሕይወት

የጐንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በ1878 ዓ.ም. ግንቦት 7 ቀን ከመሪጌታ ወልደ ኪዳንና ከወይዘሮ ደስታ በወሎ ክፍለ ሀገር ግሸን በተባለው አምባ ተወለዱ ።

ሥርዓተ ጥምቀት የተፈጸመላቸውና ከመንፈስ ቅዱስ ልጅነትን የተቀበሉት ሰኔ 17 ቀን በጻድቁ በአባ ገሪማ ዕለተ በዓል በመሆኑ ስማቸው "ክፍለ ገሪማ ተባለ ስምን መልአክ ያወጣዋል እንደተባለው ወደፊት ዝርዝር ሁኔታው እንደሚያስገነዝበው ሁሉ የአባ ገሪማ የቅድስና እንዲሁም የብሕትውና ተግባር ሁሉ በመጀመሪያ ክፍለ ገሪማ በተባሉት በብፁዕ አቡነ ሚካኤል ሕይወት ላይ ሊያንፀባርቅ ቻለ ።

<u>በትምህርት መስክ ያስገኙት ውጤት</u>

በዚያው በተወለዱበት በግሸን የንባብ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በግብረ ዲቁና ሲያገለግሉ ፤ እንዲሁም የመንፈስ አገልግሎታቸውን እስተዋፅኦ በቅንነትና በትህትና ሲያበረክቱ ቆይተው በዚያው በወሎ ክፍለ ሀገር በሚገኘው በቦሩ ሜዳ ከመምህር ደስታ በኋላ አቡነ አብርሃም/ በሦስት ዓመት ውስጥ የመጻሕፍተ ሐዲሳትን ትርጓሜ አጠኑ ፤

ከዚህም በኋላ ወደጐንደር ሔዱና ከታወቁት ሊቅ ከአለቃ ዘዮሐንስ የፍትሐ ነገሥት ትርጓሜ አደላድለው አወቁ ፤ እንደገናም መካነ ኢየሱስ ከነበሩት ከአለቃ ወልደ ሚካኤል መልሰው መላልሰው የትርጓሜ ሐዲሳት ትምህርታቸውን በሚገባ አድርገው አጠናከሩት ከአለቃ ወልደ ሚካኤል መልሰው አሥራ አራቱን መጻሕፍተ ቅዳሴ ትርጓሜ ተማሩ ።

<u>በምርምርና በብህትውና</u>

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ከላይ እንደተመለከተው ሁሉ በጐንደር ትምህርታቸውን ከተከታተሉ በኋላ ወደምርምርና ብህትውና ዓለም ተሠማርተው በደሴተ ጣና በሚገኙት ታሪካውያን ገዳማትና በታላላቁ አድባራት እየተዘዋወሩ ከሊቃውንቱ ጋር በቅርብ ቃል በቃል በመነጋገርና ቅዱሳት መጻሕፍትን በመመልከት ዕውቀታቸውን በምርምር ከማዳበራቸውም በላይ የሚዘዋወሩባቸው ቦታዎች ቅዱሳት መካናት እንደመሆናቸው የጸሎትና የብሕትውና ተግባራቸውን በዚህ አጋጣሚ ለመከታተልና የቅድስናቸውን መሠረት ለመጣል ችለዋል ።

<u>ከትምህርት ከምርምር ወደ ማስተማር</u>

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል አስቀድሞ በትምህርት ፤ ቀጥሎ በምርምር ስልትና ሒደት የተገነባው ዕውቀታቸው ጉባኤ ዘርግተው በማስተማር ለኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው እንዲተላለፍ ስለፈለጉ ከ1910 ዓ.ም.ጀምሮ ትርጓሜው መጻሕፍትን ማስተማር ጀመሩ ፤ የትምህርትና የምርምር ሰው ከመሆናቸው ጋር በትዕግሥት በተባሕትዎ ፤ በጸሎት በሰጊድ የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ከቀን ወደቀን የደቀ መዛሙርቶቻቸውን ቁጥር ሊያሳድግላቸው ቻለ ።

በተለይ የቅዳሴ ትርጓሜ የምርምርና የአተረጓጐም ይዘታቸው በጣም ተፈላጊና ተወዳጅ ስለነበረ የአሥራ አራቱን ቅዳሴያት ትርጓሜ ለመማር በዙሪያቸው የሚከቡአቸው ደቀ መዛሙርት በጣም ብዙዎች ነበሩ ከነዚሁም መካከል ቅዳሴውን በሙሉ ትርጓሜ ተርጉመውና አደራጅተው ያቀረቡትና እንዲታተም ያደረጉት አለቃ አፈወርቅ ዘለቀ ይገኙባቸዋል ።

<u>ምንኩስና</u>

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ገና በሕፃንነት ዕድሜያቸው ጀምሮ ቅዱስ ጳውሎስ ዓለም በእኔ ዘንድ የሞተች ናት ፤እኔም በዓለም ዘንድ የሞትኩ ነኝ ሲል የተናገረውን ቃል ተግባራዊ ማድረግ ስለነበረ በ1916 ዓ.ም ጥር 7 ቀን በደብረ ሊባኖስ ገዳም መነኮሱ ፤ ወዲያውኑ በዚ ዘመን በየካቲት 12 ቀን ከአዲስ አበባ ከተማ በግብፃዊው ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ የቅስና ማዕረግ ተቀበሉ ፤ አከታትለውም በላይ በተጠቀሰው ዓመተ ምህረት ወደኢየሩሳሌም ሂደው ቅዱሳት መካናትን እጅ ከነሡና ከቅዱሳን አበው ቡራኬ ከተቀበሉ በኋላ በ1917 ዓ.ም. በመስከረም ወር ወደአዲስ አበባ ተመለሱ ።

<u>ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ያበረከቱት የሥራ አስተዋፅኦ</u>

ብፁዕነታቸው አዲስ አበባ በሚገኘው በገነተ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ በማስተማርና በመንፈሳዊ አገልግሎት በነበሩበትም ወቅት የአሥራ አራቱን ቅዳሴያት ግዕዛዊ ንባብ ከነጠላ ትርጓሜ ጋር በማስተያየት ትርጉሙ ከታተመ በኋላ አብያተ ክርስትያናት ሁሉ እንዲገለገሉበት ተደርጓል ።

ይኅውም ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ በግዕዝ ብቻ የሥርዓተ ቅዳሴን ምስጢር ለማይከታተሉ ምእመናን ሁሉ ታላቅ ውለታ ነው ሊባል ይቻላል ፤ ብፁዕነታቸው በመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ከቅዳሴ ትርጓሜ ትምህርት ጋር ቀሳውስት ዲያቆናት በንባብና በቅዳሴ ዜማ ስልት በአጠቃላይም መንፈሳዊ አገልግሎትን በመስጠት ረገድ እንዲሠለጥኑ አድርገዋል ።

<u>ቀዊም ጸሎትና ሰጊድ</u>

ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ ጸሎታቸውን እንኳን ሌሊት አይገታውም የሚጸልዩት እየሰገዱና ላባቸው እንደውሀ እየፈሰሰ ነው ከቤተ እግዚአብሔር ሲጸልዩ አልፎ አልፎ እንኳ ከወንበር ላይ አይቀመጡም ፤ ግድግዳ አይደገፉም መደገፊያ አይፈልጉም እንቅ…



www.ethiopianorthodox.org

ቃቸውም በጸሎት ከፈጣሪያቸው በሚነጋገሩበት ጊዜ ምንም አይነት ከፍተኛ ጉዳይ ቢያጋጥም ጸሎታቸውን አቋርጠው አይናገሩም ፣ መጽሐፋቸውንም አያጥፉም ።

መድኃኒታችን ለሰው ልጆች ሲል በዚህ ዓለም የተቀበለውን መከራ ሁሉ ጊዜ ማሰብ የዘወትር ተግባራዊ ይዘታቸው ስለሆነ በየጊዜው በሚጸልዩት ጸሎት አንዱ የክርስቶስን ሕማማተ መስቀል የሚዘረዝረውንና ድርሳነ ማኅያዊ የተባለው መጽሐፍ ነው ፣ ማቅ ጨዋታ የመሰሰሉት ሁሉ በእርሳቸው ዘንድ በፍጹም ቦታ የላቸውም በጣም አስፈላጊ ለሆነ ጉዳይ እንጂ ለተራ ንግግር አንደበታቸው አይንቀሳቀስም ።

በሰሙነ ሕማማት የሚታይባቸው ፍጹም የሆነ ተመስጦም የዚህን ዓለም ከንቱነትንና ሕገ መላእክትን እንጂ ነገር አያሳስባቸውም ነበር ።

## መንፈሳዊ ሹመት

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በ1921 ዓ.ም.የትውልድ አገራቸው የግሸን ማርያምን ገዳም በመምህርነት ተሸሞው ለስምንት ዓመታት ያህል እያስተማሩ የትሩፋትና የገድል ተግባራቸውን እያከናወኑ ቆይተዋል ፣ ብፁዕነታቸው የግሸንን ገዳም በጣም እንደሚወዱአትና ሊለዩአት እንደማይፈቅዱም ሲነገረም ምክንያቱም የትውልድ አገርነቱ ብቻ ሳይሆን የክርስቶስ ግማደ መስቀል በዚያ በመገኘቱ እንደሆነ ታውቋል ።

## ራይስ ዘገዳማተ ኢየሩሳሊም

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በ1928 ዓ.ም. መስከረም 24 ቀን በኢየሩሳሌም ላሉት የኢትዮጵያ ገዳማት ራይስ ተብለው ተሾመው ሳሉ ግፈኛው የኢጣልያ ፋሽስት ኢትዮጵያን በግፍ ስለወረራት ብዙዎች ኢትዮጵያውያን በስደት ወደ ኢየሩሳሌም ሔደው ከዚያው ከገዳማቱ ስለሀገራቸው ነፃነት በሃዘንና በልቅሶ [illegible]ተዋል ።

[illegible] በተወረረችበት ጊዜ ስለገዳማቱ በቀረበባቸው ሕጋዊ ያልሆነ ክስ ስለሚሰጡት መልስ ከኢትዮጵያውያን ስደተኞችና የሥራ ረዳቶቻቸው አሳብ ቢሰጣቸው “አሳልፈው በሰጧችሁ ጊዜ የምትናገሩትን አታስቡ የምትናገሩት እናንተ አይደላችሁም” ያለውን መድኃኒታችን መምሪያ ተከትለው በተመከሩት ሳይሆን በተገለጸላቸው ራሳቸው በሰጡት መልስ ረትተው ተመለሱ ።

በዚያን ጊዜ በተባበሩት መንግሥታት ተወክሎ ኢየሩሳሌምን ያስተዳድር የነበረው የእንግሊዝ መንግሥት የጠላትን የኢትዮጵያን ገዥነት ሳያውቅ ከቆየ በኋላ ፖለቲካ አሸንፎት የኢጣልያ ንጉሥ የኢትዮጵያ ንጉሥ መሆኑን የእንግሊዝ መንግሥት ስለአወቀለት ከእንግዲህ ወዲህ በኢየሩሳሌም ያለው የኢትዮጵያ ቆንሲል እንዲዘጋ፣ሰንደቅ ዓላማውም እንዳይሰቀል ብሎ ስለአዘዘ ስደተኞቹና ምእመናኑ ሁሉ በታላቅ ሀዘንና ለቅሶ ላይ ሆነው በሚታዩበት ወቅት ከተናገሩአቸው ታሪካውያን ቃላት መካከል«ሰንደቅ ዓላማውን አሁን ጊዜው ፈቅዶ ቢያወርደው እንደገና ደግሞ ጊዜ ሲፈቅድ ያወጣዋል ይሰቅለዋል ተውት” ብለው የተናገሩት ትንቢታዊ ቃል ከዚህ ላይ ሊጠቀስ ይገባል ትንቢቱም ተግባራዊ መሆኑ ግልጽ ነው ።

## ለእስክንድሪያ ፓትርያርክ ምርጫ ተካፋይነታቸው

ብፁ አቡነ ዮሳብና ሌሎች ግብፃውያን መነኮሳት ለፓትርያርክነት እጩ ሆነው ብፁዕነታቸው ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ለምርጫው ድምፅ እንዲሰጡ ቢጠየቁ “እኔ ሁሉንም አላውቃቸውም የማላውቀውን ብመርጥ ምርጫው ልክ አይሆንምና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ የወደደውን ይምረጥ” ሲሉ ድምፅ ሰጥተዋል ።

## የጵጵስና ሹመታቸው

በ1938 ዓ.ም.በተደረገው የኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ምርጫ ከላይ እንደተገለጠው ሁሉ በትምህርት ሆነ በልዩልዩ የመንፈሳዊ ሥራ አስተዋጽኦ የተሟሉ ሆነው በመገኘታቸው በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በ1940 ዓ.ም. ሐምሌ 18 ቀን በብፁዕ አቡነ ዮሳብ እጅ ተቀብተው የጵጵስና ማዕረግ ሲቀበሉ ክፍለ ገሪማ የተባለው ስማቸው ተለውጦ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ተባለ ሀገረ ስብከታቸውም የጐንደር ከተማና አውራጃዎቿ ሆነ ።

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ለተቸገረ ለተራበና ለተጠማ ሁሉ የሚያዝኑና የሚለግሱ ስለነበሩ የወር ደሞዛቸውን በሙሉ ለአንድ ቀን ለበጐ አድራጐት ተግባር አውለው የሚፈጽሙና የቤታቸውን ወጭ ከመጠን በላይ የሚያጣብቡ ነበሩ ከዚህም የተነሣ የቤተሰቦቻቸው ጉዳት ስለታወቀ ቀለባቸውን ለቤት ወጪና ለችግረኞች የሚያከፋፍል ሞግዚት ተመድቦላቸው እንደነበረ ይነገራል ።

ለሐዋርያት በተሰጠው ስልጣን ስለምን እንሠራበትም ? ስለማለታቸው “ሐዲሳን አማንያን በልብስና በጥቃቅን ነገሮች የሚረዱበትን ሁኔታ ማጥናትና ውሳኔ መስጠት የአማንያንን ቁጥር ከዕለት ወደዕለት ሊያበረክተው ይችላል” በሚል አጀንዳ የጳጳሳት ጉባኤ ተከፍቶ በነበረ ጊዜ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል የክርስቶስ ስብከት ተከታይ ሊያገኝ የቻለው በምን ምክንያት ይመስላችኋል? የሚል ጥያቄ ለጉባኤው አቀረቡና በተአምራት ነው የሚል መልስ ስለተሰጣቸው ፣ መልካም መልስ ነው ታዲያ በሐዋርያት እግር የተተካንና በወንበራቸው የተቀመጥን እኛ ስለ ሦስት ክንድ አቡጀዲ ርዳታ መነጋገራችንን ትተን የተአምራት ሥራ ለመሥራት ያልቻልንበትን ሁኔታ እንመረምርምን ስላሉ ከፍጹም ሃይማኖታዊነት ጋር የተጐዳኘውን ይህን ጥያቄ ጉባኤው በእንክሮ አዳምጦታል ።

### ዜና ዕረፍት

ትምህርት ደግነት ትሩፋት ሃይማኖታዊነት የመሳሰሉት ደጋጎች ተግባራት



# የሃይማኖት ዐምድ

«ዓለሞች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ ፤ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን» (ዕብ. ፲፩፥፫) ።

## ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን

እግዚአብሔር የሁሉ ነገር አስገኝ የዓለማት ሁሉ ፈጣሪ ሁሉን ቻይ የሁሉ መጋቢ ዘለዓለማዊ ገዥ መሆኑን መለኮታዊ ባሕርዩን እንዲሁም አንድነቱንና ሦስትነቱን የሚገልጡ ዝግጅቶች ባለፉት ተከታታይ ቁጥሮች ከሞላ ጐደል ባጭር ትንታኔ መቅረባቸው ይታወሳል።

አለፍ ብሎም ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ ከተገለጠ ዘንድ የምሥጢረ ቤተ ክርስቲያንን ይዘት ባጭሩ መመርመር አስፈላጊ ይሆናል ስለዚህም ካሁን ጀምሮ ለወደፊት በተከታታይ በሚወጡት ቁጥሮች ስለ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ምንነትና አፈጻጸም ባጭሩ እንመለከታለን ።

እነርሱም በቁጥር ሰባት ያህል ሲሆኑ በተለይ አራት ያህሉ 1/ “ምሥጢረ ጥምቀት 2/ ምሥጢረ ሜሮን 3/ ምሥጢረ ቁርባን 4/ ምሥጢረ ንስሐ” የሚባሉት ትንሽ ትልቅ ሴት ወንድ ፣ የሚል መለዮ ሳይኖር ለሁሉም የሚያስፈልጉ ናቸው ። እነዚህም በዓለም አቀፍ ደረጃ የክርስትና እምነት ተከታዮች የሆኑ ሁሉ ስለሚጠቀሙባቸው ታላላቅ ምሥጢራት ናቸው ተብለው ይታመንባቸዋል ።

የነዚህ ተከታዮች 1/ ምሥጢረ ክህነት 2/ ምሥጢረ ተክሊል 3/ ምሥጢረ ቀንዲል የተባሉት እነዚህ ሦስቱ ለሚፈልጉ ግለሰቦችና ለተለያዩ ሰዎች ብቻ እንጂ ለሁሉም በወል ወይም በጋርዮሽ የሚሰጡ የወል ድንጋጌዎች አይደሉም ለምሳሌ የሰው ዘር የተባለው ሁሉ ካህን መሆን አይችልም ማለትም ክህነት በተለይ ይህን አገልግሎት ለመቀበል ፈቃደኞች ሆነው ለተመረጡ ወይም መንፈሳዊ ጥሪ ለተደረገላቸው ግለሰቦች ብቻ የሚሰጥ ነው እንጂ ማንም ሰው በግድ ተይዞ የሚቀበለው ጉዳይ አይደለም ዕርግጥ በቀድሞው ጊዜ አብዛኛው ካህናት በክህነት ተግባር የሚያገለግሉበት እንደደመወዝ የሚቆጠር አስበ ክህነት ራሱ መሬትና ከመሬት የሚገኝ ሰብል (ሀብት) ስለነበር መሬቱን ወይም ርስቱን ለሌላ አሳልፎ ላለመስጠት ሲል በቂ ትምህርት ሳይኖረውና መንፈሳዊ ጥሪ ሳይደርሰው ለሰሞነኛነት ግብር ሲባል ብቻ በውድም በግድም ማለት የሚገባውም የማይገባውም ሥልጣነ ክህነት በመቀበል አለቦታው ቤተ ክርስቲያንን በማጣበብ በማኅሌቱ መቋሚያና ጽናጽል አቀባይ ነፋስ ከልካይ አወዳሽም ቀዳሽም ላኪና ተላላኪም በመሆን ራሱን ለማዋል በመፍጨርጨር ብቻ የሚኖር እንደነበር ይታወሳል ።

“በአባቴ መቅደስ ደግሞም በእናቴ እንዳሻኝ ልሁን እንደ ብልሃቴ” አለ እየተባለ የሚነገረው ከዚህ የተነሣ መሆኑ ነው ።

እንዲሁም የጋብቻን ምሥጢር ብንመለከት የሰው ዘር የተባለ ሁሉ ያገባል ወይም እንዲያገባ ይገደዳል ማለት አይቻልም ። ዘር ለመተካትና የዚህን ዓለም ጣዕመ ህላዌ መኖር) ለማደራጀት የሚፈልግ ካልሆነ በቀር ተገድዶ ያገባ ዘንድ የሚታዘዝ የለም ። ምሥጢረ ቀንዲል የሚባለው በተለይ ለሕሙማን ብቻ የሚውል ሰለሆነ ለማንኛውም አማኝ የግዴታ ጉዳይ ሆኖ አይፈጸምም ።

ከነዚህ ሰባት ምሥጢራት ጋር ደግሞ የሰው ዘር የሆነ ሁሉ በየጊዜው በተደጋጋሚ የሚፈጽማቸው ቁርባንን ንስሐንና ቀንዲልን የመሳሰሉ አሉ ክህነት ጥምቀትና ሜሮን ግን አንድ ጊዜ ከተሰጡ በኋላ የሚደጋገሙ አይደሉም ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት ለኃጢአት ማስተሠሪያ በተሠራች በአንዲት ጥምቀት እናምናለን ሲሉ 318 ሊቃውንት የደነገጉበት (የወሠኑበት) ምክንያት ይኀው ነው ። የክህነቱም ጉዳይ መደገም እንደማይገባው በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ አምስት ረሰጠብ 47 በሰፊው ተተንትኖ ይገኛል ።

ዳሩ ግን ከ4ኛው ጉባኤ ኬልቄዶን ገዞርወት በኋላ በየጊዜው የተለያየ ቀኖናዊ ልዩነት በመፍጠር የሚያፈነግጡ የአንዳንድ ማኅበረ ምዕመናን -አብያተ ክርስቲያናት) ቀኖና ተከታዮች እነዚህን የማይደገሙ ምሥጢራት በመደጋገም ሲፈጽሟቸው ይገኛሉ ለምሳሌ ክህነትንና ጋብቻን እንደሚደግሙና ለዚህም ማስረጃ ብለው ከቅዱሳት መጻሕፍት ከሚያቀርቡት አንዱ በትንቢተ ህዝ 4-22 ያለው ስለሆነ አንብቦ መረዳት ይቻላል ። በሌላም በኩል “በዝሙት ምክንያት ካልሆነ በቀር ማንም ሰው ሚስቱን መፍታት አይገባውም የሚለውን ቃለ ወንጌል ትርጉም እንደሚሰማማቸው አድርገው በመመ ት በዝሙት ምክንያት ከሆነ እርስዋን ፈትቶ ሌላዋን በሕግ ማግባት እንደሚችል ይተርካሉ ። የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች የሆኑ ሊቃውንት ግን ይህ የማይፈቀድበትን ሥርዓትና ድንጋጌ ከነትርጉሙ ወስነው የጋብቻንና የክህነትን መደጋገም ያወግዛሉ ።እኛም የነርሱን ሥልጣን ተቀብለናልና ወበእንተዝ አውገዝ ነ ወአሠርነ” እንላለን ።

ነገር ግን በተለይ በጋብቻ በኩል ያለውን ምሥጢር እንደገና በሌላ መልኩ አገላብጠን ብንመለከተው ከሁለቱ የኑሮ ጓደኛሞች አንዱ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ወይም ሚስት ብትሞት ከሕገ ምንኩስና ወይም ከብሕትውና ኑሮ አንዱን ካልመረጡ በቀር እግብተው ለመኖር እንደሚችሉ በ1 ቆሬ.7 ተመልክቶአል።ሆኖም በሚስት መሞት የፈረሰ ክህነት በሕገ ምንኩስና ወይም በብቸኝነት ኑሮ ካልተተካ በቀር ሊደገም የማይችል መሆኑ መታወቅ አለበ

ይቀጥላል



www.ethiopianorthodox.org

# ምን እንርዳዎ ?

ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፤ ለችግራቸው መፍትሔ የሚሰጡበት ፤ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።




አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ

ስልክ ቊጥር 11-66-16

የፖ.ሣ.ቁ. 31-37

አዲስ አበባ


ለትንሣኤ መጽሔት የምን እንርዳዎ ዐምድ አዘጋጅ
አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ኦር/ተዋ/ቤተ ክርስቲያን በ81 (በሰማኒያ አንድ) ቅዱሳት መጻሕፍት እንደምትመራ ይታወቃል በሌላው አህጉር ውስጥ ያሉት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮችስ በዚሁ በ 81 ነው ወይስ የተለየ እላቸው የተለየ

2ኛ ይህ መጽሐፍ ቅዱሳችን ማለት 81 ለምን እንደ ሌላው መጽሐፍ ቅዱስ ለምዕመናኑ በገበያ ላይ ውሎ እንድናውቀው አይደረግም ።

3ኛ/ በትንሣኤ መጽሔት በቁ. 29 ላይ በእመቤታችን ላይ አክሊል የሚጭኑላት ማንና ማናቸው? አንዱ አብ ብዬ ሁለተኛውን መንፈስ ቅዱስ እንዳልል መንፈስ ቅዱስ ከላይ በርግብ አምሳል ይታያልና ነው ትርጉም ለመስጠት ስለ ቸገረኝ ይህን ጥያቄ አቅርቤአለሁ ከትህትና ጋር ።

ታደሰ ማሞ

አቶ ታደሰ ማሞ ይህን የመሰለ ጠቃሚ ጥያቄ በማቅረብዎና የመጽሔታችንም ተከታታይ በመሆንዎ እናመሰግናለን ።

ኋላ ጥያቄው የሰማንያ አንዱ ቅዱሳ ...ጉዳይ ከማቅረ ቢ በፊት በ1953 ዓ.ም ስለታተመው 79 መጻሕፍት ስለያዘው ታላቁ መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ነገሮችን ላቅርብልዎ። ምክንያቱም አሁን ስለቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር በምንዘረዝርበት ጊዜ በታተመው በታላቁ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከቤተ ክርስቲያናችን የመጻሕፍት አቆጣጠር ውጭ የሆኑ አንዳንድ መጻሕፍት ስለአሉ ጥያቄው እንዳያዳግምዎ ለማድረግ ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን 81 ቅዱሳት ማጻሕፍት አሉዋት ። ግን እርስዎ እንዳሉት እስከ አሁን ድረስ ሁሉም በአንድነት ተጠርዘው አልታተሙም ። ለመጀመሪያ ጊዜ በ1953 ዓ.ም. የታተመው ታላቁ መጽሐፍ ቅዱስም ሰማንያ ሃንድ ሳይሆን ሰባ ዘጠኝ ነው ። ያውም ሆኖ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት አቆጣጠር ተከትሎ የታተመ አይደለም ። ምክንያቱም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ስለ አላዘጋጀችው ነው ።

ነገሩ እንዲህ ነው ። የዚሁ መጽሐፍ አዘጋጅ ኮሚቴ በግላዊ ትዕዛዝ ተቋቁሞ ሲሠራ ቆይቶ በሶስት ኮፒ በእጅ ተጽፎ እንዲጠረዝ ወደ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ይላካል ቤተ ክርስቲያንም ስለዚሁ መጽሐፍ አንድ ደብዳቤ ተጽፎላት እንደነበረ አንድ የቤተ ክህነት ባለሥልጣን የነበሩ ሲናገሩ "መጽሐፍ ቅዱስ ለማሳተም በማዘጋጀት ላይ ነንና ተራውን አውጥታችሁ በቅደም ተከተል አዘጋጅታችሁ ላኩልን" የሚላ ነበረ የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖችም ለዚህ የሰጡት መልስ "ከዋናው እርማት ቤተ ክርስቲያን ሳትጠየቅ በተራው ማውጣት ብቻ መጠየቅዋ ያሳዝናቸው መሆኑን በመግለፅ ተራ ማውጣቱንም የማይችሉ መሆናቸውን መልስ የሰጡ መሆናቸውን አስረድተውኛል ። ኮሚቴውም ያዘጋጀው መጽሐፍ ሰባ ዘጠኙን ብቻ ወይም ሰማንያ አንዱን እንደሆነ ለመረዳት የኮሚቴውን አባሎች ፈልጌ ማግኘት ባለመቻሌ ለማረጋገጥ አልቻልኩም ።

እንግዲህ እርስዎ እንደጠየቁት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የምትቀበላቸው 81 መጻሕፍትና የምሥራቅ ኦርቶዶክሳውያን የሚቀበሉዋቸው መጻሕፍት በቁጥር የተለያዩ ናቸው ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የምትቀበላቸው የሚከተሉት ናቸው ።

<u>መጻሕፍተ ብሉያት</u>

| | |
|---|---|
| 1. መጻሕፍተ ሙሴ | 5 |
| 2. መጽሐፈ ኢያሱ | 1 |
| 3. መሣፍንት | 1 |
| 4. መ. ሩት | 1 |
| 5. መጽ.ሳሙኤል 1-2 | 2 |
| 6. መጽ.ነገሥት 1-2 | 2 |
| 7. 1ኛ ዜና መ. | 1 |
| 8. 2ኛ ዜና መ. | 1 |
| 9. እዝራ ነህምያ | 1 |
| 10. እዝራ ሱቱኤል | 1 |
| 11. እዝራ ካልዕ | |
| 12. ጦቢት | 1 |
| 13. ዩዲት | 1 |
| 14. አስቴር | 1 |
| 15. 1ኛ መቃብያን | 1 |
| 16. መቃብያን 2ኛና 3ኛ | 1 |
| 17. መጽሐፈ ዮሴፍ ወ/ኮርዩን | 1 |
| 18. መጽሐፈ ኢዮብ | 1 |
| 19. መዝ. ዳዊት | 1 |
| 20. መጻሕፍተ ሰሎሞን | 5 |
| 21. መጽ.ሲራክ | 1 |
| 22. መጻሕፍተ ነቢያት | 16 |
| ድምር | 46 |

ይሆናል

<u>መጻሕፍተ ሐዲሳት</u>

| | |
|---|---|
| 1. ወንጌላት 4 | |
| 2. ግብረ ሐዋርያት | 1 |
| 3. መልእክታተ ጳውሎስ | 14 |
| 4. " ጴጥሮስ | 2 |
| 5. " ዮሐንስ | 3 |
| 6. " " ያዕቆብ | 1 |
| 7. መልእክተ ይሁዳ | 1 |
| 8. የዮሐንስ ራዕይ | 1 |
| 9. መጻሕፍተ ኪዳን | 2 |
| 10. ሥርዓተ ጽዮን | 1 |
| 11. ትዕዛዝ | 1 |
| 12. ግፅው | 1 |
| 13. አብጥሊስ | 1 |
| 14. ቀለሚንጦስ | 1 |
| 15. ዲድስቅልያ | 1 |

ድምር 35+46 81 ይሆናሉ

ሌሎቹ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት 81 ለመሙላት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚጨምሩዋቸው የሚከተሉት ናቸው ።

1ኛ/ መጽ.እዝራ ሱቱኤል 1
2ኛ/ መጽ. እዝራ ካልዕ 1
3ኛ/ መጽሐፈ ጦቢት 1
4ኛ/ ዮዲት 1
5ኛ/ 1ኛ መቃብያን 1
6ኛ/ 2-3 መቃብያ 1
7ኛ/ ዮሴፍ ወልደ ከርዮን 1
8ኛ/ ተግሣፅ 1
9ኛ/ መጽሐፈ ሲራክ 1
10ኛ/ ሄኖክ 1
11ኛ/ ባሮክ 1
12ኛ/ መዝሙረ ሰለስቱ ደቂቃ 1
13ኛ/ ጸሎተ ምናሴ 1
14ኛ/ ዘና ሶስና 1
15ኛ/ ዜና ቤል ወደራጐን 1
ድምር 15

ከ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ጋር ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት 15ቱ ሲደመሩ 81 ይሆናሉ ማለት ነው ።

ያም አለ ይህ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ አንድ ስትሆን በቅዱሳት መጻሕፍት መለያየቱም ጠቃሚ ስለማይሆን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ቢያስብብበት መልካም ነው እንላለን ።

የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ 49 ብሉያት 27 ሐዲሳት

ድምር 76 ትቀበላለች

እግረ መንገዳችንን የሌሎችንም አብያተ ክርስቲያናት መጻሕፍት እንመልከት ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን

46 ብሉያት
27 ሐዲሳት

በድምሩ የምትቀበላቸው 73 መጻሕፍት ናቸው

የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ ከዚህ በላይ ከዘረዘርናቸው መጻሕፍት ዝቅተኛ የሆነ የቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር አላቸው ።

ይኀውም ብሉያት 39
ሐዲሳት 27

ድምር 66 መጻሕፍትን ይቀበላሉ ፤ እንግዲህ ለምሳሌ ያህል ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸውን አቀረብን እንጂ የሌሎችም የተለያየ ነው ።

ታዲያ ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፉ መሆናቸው እየታወቀና ሁሉም እያመነበት የያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት መጻሕፍት ልዩነት መታየቱ ጥሩ አይደለም ይህ ልዩነት ተወግዶ አንድነት ሊመሠረት የሚችለው በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ጥረት ሳይሆን በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ትጋትና ጥረት ስለሆነ ወደፊት አንድነት እንደሚፈጠር አንጠራጠርም ።

2ኛው ጥያቄ ቅዱሳት መጻሕፍት ታትመው በገበያ ላይ አለመዋላቸው እኛም እንደርስዎ የምንቸገርበት ጉዳይ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያናችን ስለዚሁ ጉዳይ አስባበት በቅርብ ቀን መጽሐፉን ለተከታታዮቿዋ እንደምታቀርብ ተስፋ በማድረግ ጥያቄዎን የሚመለከተው ክፍል እንዲመለከተው አውጥተንልዎታል ።

ስለሦስተኛው ጥያቄ ደግሞ ለቅድስት ድንግል ማርያም አክሊል ሲጭኑላት በትንሣኤ መጽሔት ቁጥር 29 ላይ የሚታዩት እግዚአብሔር አብና እግዚአብሔር ወልድ ናቸው ። ለዛሬው በዚሁ ይብቃን አይመስልዎትም ።




www.ethiopianorthodox.org

## ወጣቶች ...

ከገጽ ፲፰ -የዞረ

ረገላቸው እንግዶች በተገኙበት በርከ
ት ያሉ ማይማን ማስመረቃቸው በጊዜ
ው በዜና ማሠራጫዎች ተገልጧል ።

የደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ወጣ
ቶች በዚህ ብቻ አላበቁም ። ከምረቃው
ማግሥት ጀምረው እንደገና ሌሎች ማ
ይማንን አሰልጥነው ከሦስት ወር በኋ
ላ እንደዚሁ በተመሳሳይ ሁኔታ አስመ
ርቀዋል ። በዚሁ ወቅት አቶ ጉደታ ማሞ
የትምህርት ሚኒስተሩን በመወከል በድ
ጋሚ ተገኝተው አስመራቂዎቹን ወጣ



የደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት አስተዳዳሪ የምስክር ወረቀት ሲሰጡ

ቶችና ተመራቂዎቹን ማይማን በማመ
ስገን ሰፋ ያለ ማብራሪያና ትምህርት ሰጥ
ተዋል ። በንግግራቸውም ወጣቶቹ ያካ
ሄዱት የትምህርት ዘመቻ ቀደም ሲል
ቤተ ክርስቲያን በማስተማር በኩል
ግንባር ቀደም ሆና መቆየቷን የሚያስ
ገነዝብ ከመሆኑም በላይ አሁን አገራች
ን ማይምነትን ለማጥፋት ለምታደርገ
ው ዘመቻ በተጨማሪ ኃይል ነው ሲሉ
አድናቆታቸውን ገልጠው ነበር ። የደ
ብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት መንፈሳው
... ቶች በምረቃው ዕለት ለሕዝቡ
... አሁንም ያለማ
ቋረጥ ዘመቻውን በማካሄድ ላይ መሆ
ናቸውን ጠይቀን ተረድተናል ። ስለዚ
ህ ለሌሎችም መንፈሳውያን ማኅበራት
መልካም ምሳሌ ሆነዋል እንላለን ።

በመገናኛ የተገለጠውንና ጎላ ብሎ
የታየውን ለመናገር ያህል የደብረ አሚ
ን መንፈሳውያን ወጣቶችን ምሳሌ አድ
ርገን ለመጠቆም ሞከርን እንጂ በአቅ
ማቸው መጠን እያስተማሩ ለብዙ ማይ
ማን የእውቀት ብርሃን የፈነጠቁ ብዙ
መንፈሳውያን ወጣቶች እንዳሉ እናው
ቃለን ። ሌላው ቀርቶ ከዚህ በፊት የመ
ሠረተ ትምህርት ዘመቻው ከመታወጁ
ቀደም ሲል ወደከፋ ክፍለ ሀገር ለሥራ
ጉዳይ በሄድንበት ወቅት በጅማ ከተማ
ውስጥ የደብረ ሰላም ኢየሱስ መንፈሳ
ውያን ወጣቶች ከትምህርት ቤታቸው
ሲመለሱ ባለቸው ትርፍ ጊዜ ውስጥ
በሸፍት ተመድበው በቤተ ክርስቲያኑ
ቅጥር ግቢ ውስጥ ማይማንን በተለይም
ከትምህርት ቤት ያልገቡትን ወጣቶች
እየሰበሰቡ ሲያስተምሩ አይተን በጊዜ
ው በድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣችን ዜናው
ን ማውጣታችን ይታወሳል ያመልካም
ተግባር አሁንም በዚህ ዘመቻ ወቅት
እንደማይቋረጥ ተስፋ እናደርጋለን ።

መንፈሳውያን ወጣቶች በማስተማር
በኩል የሚያደርጉት ተሳትፎ በዚህ
ብቻ የሚገታ ሳይሆን በየትምህርት ቤ
ታቸው በቀበሌና በሌሎችም ድርጅቶ
ች ከኅብረተሰቡ ጐን ተሰልፈው የሚ
ያካሂዱትን ዘመቻ በቀላል የሚገመት
ባይሆንም በመንፈሳውያን ማኅበራት
ያበረከቱትን የሥራ ድርሻ ብቻ ለመጠ
ቆም ሞክረናል ። ስለዚህ ጉዳዩ የሚመ
ለከታቸው ክፍሎች በነገሩ አስበውበት
ለዚህ ብቁ የሚሆኑትን መንፈሳውያን
ወጣቶች እየመለመሉ ተገቢውን ትም
ህርት እንዲሰጡ ቢያዘጋጁአቸው ጠቃ
ሚ ውጤት ይገኛል ብለን ስለምናምን
ይታሰብበት እንላለን ከዚህም ጋር ለት
ምህርት የሚያገለግሉት መጻሕፍትና የ
ትምህርት መግሪያዎች ሁሉ ተሰጥተዋ
ቸው በየቤተ ክርስቲያኑ ባሉት አመቺ
ቦታዎች ሁሉ ቢሰለፉ ከነሱ ከሚጠበቀ
ው የበለጠ ውጤት እንደሚገኝ ተስፋ
አለን ። ይልቁንም ባለፈው አጉል አስ
ተሳሰብና መጥፎ ልማድ የተነሣ ማንበ
ብና መተርጐም እንጂ መጻፍ የማይች
ሉ አባቶች ካህናት በየደብሩ ሊኖሩ ስለ
ሚችሉ እነሱም የሂሳብ ስሌትና መጻፍ
እንዲለማመዱ መልካም አጋጣሚ ነው
ና የሰበካ ጉባኤ አባሎችና ካህናትም ለ
ዚህ መልካም ተግባር እንደሚተባበሩ
እናምናለን ።

ኢሳይያስ ወንድማገኘሁ

## ልማት በቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን በልማት በኩል የምታ
ደርገው ጥረት እንዲሁ በልማድ ሳይሆን
ለመጀመሪያ ሰው "በፊትህ ወዝ እንጀ
ራህን ብላ የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝ
በመከተል ነው ።

በዚህ መሠረት እነ ቅዱስ ጳውሎስ
ቀን ወንጌልን በማስተማር ሌሊት ድን
ኳንን በመስፋት ጊዜያቸውን ሲጠቀሙ
በት ከመኖራቸውም በላይ የወንጌል
ንም ብርሃን በመላው ዓለም ለማሰራጨ
ት ችለዋል ።

ቤተ ክርስቲያን በዚህ ብቻ ሳትወ
ሰን በከብት ርቢም በኩል ከፍተኛ ድር
ሻ እንዳላት ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል
ያስረዳል "ወይንን ተክሎ ፍሬውን የማ
ይበላ ማን ነው ? መንጋውንስ እየጠበቀ
ወተቱን የማይጠጣ ማን ነው ? 1ኛ
ቆሮ. 9፡7 ።

ይህንንም መሠረት በማድረግ በሐመ
ረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት የተጀመረው የከ
ብት ርቢ እንዴት እንደ ተጀመረ የሐ
መረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያ
ንን አስተዳዳሪና የሰበካ ጉባኤውን ሊቀ
መንበር መምህር ፍሥሐ ቡሩክን አነጋ
ግረናል ።



የሐመረ ኖህ ኪ/ምሕረት አስተዳዳሪ

ትንሣኤ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ
ዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የወጣው አዲስ
ቃለ አዋዲ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ
ማንኛውም ልማት እንዲቋቋም ያዛል
ስለዚህ በቃለ አዋዲው መሠረት በዚህ
በሐመረ ኖኅ የተቋቋመ ልማት እንዳለ
ቢገልጹልን ?

መምህር ፍሥሐ ቡሩክ አዎን የከብ
ት ርቢ ልማትና ት/ቤትን አቋቁመን
በመሥራት ላይ እንገኛለን ልማቱም
የተጀመረው እንደሚከተለው ነው ።

የከብት ርባታው የሚቋቋምበትን
ቦታ ለማስፈቀድ በአካባቢው ለሚገ
ኘው በከፍተኛ 11 ቀበሌ 02 አመልክ
ተን ቀበሌውም ለከተማ ልማትና ቤት
ሚኒስቴር አስተላለፈልን ። የከተማ
ልማትና ቤት ሚኒስቴርም በራሱ
መሐንዲስ ቦታውን አስጠንቶ ከሰጠን
በኋላ መዘጋጃ ቤት ቦታውን በፕላን
እንዲያነሳ ትእዛዝ አስተላለፈልን ።
ከዚህ በኋላ በሚገባ ቦታው ፕላን ተነሥ
ቶ የቦታው መጠን 3700 ሜትር ካሬ
መሆኑን ገልጾ ቦታውን ከልሎ አስረከ
በን ።

ቦታውን ከተረከብን በኋላ ቦታው
ለከብት እርባታ ተስማሚ መሆኑን ቀድ
ሞ የዓሣ ልማትና የሥጋ ቦርድ የነበ
ረው እንዲያጠናልን ጠየቅንና እሱም
ለከብት ርቢ ተስማሚ መሆኑን በደብ
ዳቤ አረጋገጠልን ።

በዚህ ጊዜ ልማቱን የምናከናውንበ
ትን ቤት ለማሠራት $43822 ከ02
(አርባ ሦስት ሺ ስምንት መቶ ሃያ ሁለ
ት ብር ከሁለት ሳንቲም )ወጭ አድ
ርገን የቤቱን ሥራና የቤቱን አጥር
አጠናቅቀን ይህንን ሥራ ካጠናቀቅን
በኋላ በመጠኑ የከብትን ርቢ ጀምረ
ናል የከብት ርቢውንም ለመጀመሪያ
ጊዜ 4 ላሞችን በመግዛት ነው የጀመር
ነው ይሁን እንጂ እነሱን በሚገባ ተንከ
ባክበን በመያዛችን ባሁኑ ጊዜ እነሆ 20
ወላጅ ላሞች ፣ 1 ኮርማ ፣ 7 ጊደሮች ፣
4 ጥጆች በጠቅላላ ብዛታቸው 32 ደር
ሰው ይገኛሉ ።

ትንሣኤ 4 ላሞች ገዝታችሁ 32 ያህል
ብዛት ሊያመጡ የቻሉት እርባታው ከተ
ጀመረ ስንት ዓመት ቢሆነው ነው ።

መምህር ፍስሐ ርባታውን ከጀመ
ርን አጭር ጊዜ ነው የሆነ ሆኖ በሽታ
እንዳይዛቸው በምግብም እንዳይጐዱ
ጥዋትና ማታ እየተቆጣጠርን ስለምንን
ከባከባቸው ቶሎ ቶሎ ይወልዳሉ ። በዚ
ህም ምክንያት በጥቂት ጊዜ ውስጥ ቁጥ
ራቸው ከፍ ሊል ችሎአል ።

መቼም የከብት ርቢ የሚፈለገው
በወተት ለመጠቀም ጭምር መሆኑ
ግልጽ ነው ታዲያ ትርፍ አላገኘንም
ትርፋችን የሚወለዱ ጥጆች ብቻ
ናቸው ። ምክንያቱም ከወተቱ ሽያ
ጭ የሚገኘው ገንዘብ የከብቶቹን
ቤት የሚጠርገውና በየሰዓቱ እየተቆ
ጣጠረ ሣርና ውኃ የሚሰጣቸው እረ
ኛ ደመወዙን የሚያገኘው ከዚያው
ስለሆነ ለከብቶቹ መኖና መድኃ
ኒት የሚገዛውም ከወተቱ ሽያጭ በተ
ገኘው ገንዘብ ነው ስለዚህ የወተቱ
ሽያጭ ገንዘብ ከወጭ ስለማያልፍ
እስከአሁን ትርፍ የለውም ።

ትንሣኤ ፡- ለመሆኑ ስንት ሊትር ወተ
ት እንደሚታለብና ስንት ሊትር ወ
ተት እንደሚሸጥ እንዴት ሊታወቅ
ይችላል ?

መምህር ፍሥሐ ወተቱን የሚሸጥና ለ
ዚሁም ተቆጣጣሪ ሂሳብ ክፍል ስላለ
ከዚህም ሌላ በየዕለቱ ስንት ሊትር
እንደታለበና ስንት ሊትር ወተትም
እንደተሸጠ የሚቆጣጠሩ 4 ሰዎች
ስላሉ የዚህ ችግር የለብንም ገቢውን
በሚገባ እናውቀዋለን ።

ትንሣኤ ፡- የከብት ርቢ እንዴት እንደ
ተጀመረ ሲያብራሩልኝ ትምህርት
ቤቶችም እንዳሉ ጠቁመውኝ ነበር
ስለዚህ አሉ የተባሉት ትምህርት
ቤቶች ምን ዓይነት ትምህርት የሚሰ
ጥባቸው ናቸው ? ለመምህራኑስ ደ
መወዝ የሚከፍላቸው ማን ነው ?

መልስ ፡- እብያተ ትምህርቱ ሁለት ና
ቸው በእነዚህም የሚሰጡት የትምህ
ርት ዓይነቶች 1ኛ ጸዋት ወ ዜማ ሲ
ሆን ሁለተኛውም የቅዳሴ ዜማ ትም
ህርት ነው ። ለመመ...





www.ethiopianorthodox.org

ወዝ የሚከፍላቸው የሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ጽ ቤት ነው ። ለመምህራኑ ብቻ ሳይሆኑ ትምህርቱን የሚከታተሉ 15 ተማሮችም ብትርፍ ጊዜያቸው ቤተ ክርስቲያኑ ስለሚያገለግሉ ለእነርሱም ጭምር ደመወዛቸውን የሚከፍለው ይኸው ቤተ ክርስቲያን ነው ።

**ትንሣኤ ፡-** ስለ ወደፊቱ ልማት ያላችሁ ዕቅድ እንዴት እንደሆነና ከዚህም በፊት ለሥራ ማከናወኛ ያወጣቻሁትን ገንዘብ በአጠቃላይ ቢያብራሩልኝ?

**መምህር ፍስሐ ፡-** የወደፊት ዕቅዳችን በሚፈቅድልን መጠን ከዚህ በበለጠ ለማስፋፋት ሐሳብ አለን እንዲያውም በከብት ርቢ ሳንወሰን ሌሎችንም ልማቶች ለማቋቋም ሰፊ ዕቅድ አላን ። ለማጠቃለል ያህል ከዚህ በፊት ለልማት ሥራ ወጭ ያደረግነው ገንዘብ የሚከተለው ነው ።

| | |
|---|---|
| 1ኛ/ ለላሞቹ ቤት መሥሪያ | 43822.02 |
| 2ኛ/ ላሞቹ የተገዙበት | 20491.95 |
| (3ኛ/ ለላሞች መኖ (ሣር) | 14542.26 |
| 4ኛ/ ልዩ ልዩ መድኃኒት የተገዛበት | 142.80 |
| 5ኛ/ ላሞቹን ለሚጠብቁ እረኞች | 1800.00 |
| በድምሩ | 96999.02 |

ነው ሲሉ አስረድተዋል ።

አዎ ቤተ ክርስቲያናችን ጥንትም ሆነ ዛሬ በተለያዩ የልማት ዘርፎች እየተሰማራች ስትጠቀም ቆይታለች ለወደፊትም ቢሆን ትጠቀምበታለች ። እንዲያውም በሀገራችን ውስጥ ድርብ ሥራ ይሠራሉ ከሚባሉት መካከል በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የሚገኙ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ካህናት ናቸው ቢባል ከእውነት የራቀ አይደለም ምክንያቱም ኅብረተሰብ በሚያርፍበት ወቅት እነርሱ ሰዓታት ፣ ማኅሌት በመቆም ቀድሶ በማቁረብ የሞተ ሰው በመፍታት ኅብረተሰቡን ያገለግሉና በሥራ ሰዓት ደግሞ እንደሌላው ኅብረተሰብ በልማት [illegible]ው ሠርተው ራሳቸውንና ወገናቸውን ሀገራቸውን ይረዳሉ ።

ከዚህም ሌላ በከብት ርቢም ቢሆን እንደሌሎቹ ከብትን ያረባሉ ስለዚህ ልማት ለቤተ ክርስቲያናችን እንግዳ ነገር ስላይደለ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የምንገኘው ካህናት ሁሉ በከብት ርቢም ሆነ በተግባረ እድ እነሱንም በመሳሰሉት ማለት ለቤተ ክርስቲያን ገቢ ያስገኛል ተብሎ በሚታመንበት ሁሉ እየተሰማራን የቤተ ክርስቲያናችንን ልማት ለማስፋፋት የያንዳንዳችን ግዴታ መሆኑን አውቀን በዚሁ መሰለፍ አለብን እንላለን ።

ክንፈ ርግብ ማርቆስ

## ሊቃውንቶቻችን ...

ከገጽ ፩፮ የዞረ

ት ሁሉ ሥጋ የለበሰውን ሰው ከሞት ኃይል ሊያድኑት ስለማይችሉ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል እንደቅዱስ ጳውሎስ የጽድቅ ሥራቸውንና እሽቅድምድማቸውን ፈጽመው በ1952 ዓ.ም. ጥቅምት 4 ቀን በግሸን ማርያም ገዳም አርፈው ከዚያው ቀብራቸው ተፈጽሟል ፤ በኢጣልያ ፋሽስት ወረራ ጊዜ ኢየሩሳሌም በስደት የነበሩት ወዳጆቻቸውና የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸው በ1954 ዓ.ም. ጥቅምት 4 ቀን በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ቅፅር ውስጥ መታሰቢያ ሐውልት አቁመውላቸዋል ፤ የብፁዕነታቸው ተግባራዊ ውጤት በጣም ሰፊ ሲሆን ይህ ከምሉዕ በከፍሉ እንጂ በአጠቃላይ የተጻፈ አይደለም ። አለቃ ዐምደ ጽዮን ተሰማ ፤

## ማሳሰቢያ

የኢትዮጵያ፡ ኦርቶዶክስ፡ ተዋሕዶ፡ ሐዋርያዊ፡ ድርጅት፡ መንፈሳዊ፡ መዝሙርና፡ መንፈሳዊ፡ ትምህርት፡ ለሚፈልጉ ሁሉ፡ የሚከተሉትን፡ ትምህርቶች፡ ያዘጋጃል።

1. የልደት፣ የጥምቀት፣ የትንሣኤን፡ መዝሙር፡(በጸናጽልና በከበሮ)
2. ሙሉ፡ ቅዳሴ
3. የተለያዩ፡ ጥንታውያንና፡ ዘመናውያን፡ መዝሙሮችን፤
4. በበገና፡ በመሰንቆና፡ በክራር፡ የተዘጋጁ፡ መዝሙሮችን፤
5. የሕማማትን፡ ሰዓታት፡ እንዲሁም፡ የወንጌል፡ ትምህርት እያዘጋጀ፡ ለሚፈልጉ፡ ያደርሳል።

ዋጋ፡- ካሴት፡ ይዘው፡ ለሚመጡ፡ ለእያንዳንዱ፡ ዋጋ፡ ሁለት፡ ብር፡ ብቻ፤ መዝሙሩን፡ ከነካሴቱ፡ ለሚጠይቁ፡ ሰባት፡ ብር፡ ብቻ በማስከፈል፡ መንፈሳውያን፡ ትምህርቶችንና፡ መዝሙሮችን፡ ያደርሳል።

አድራሻ፡- ቅድስት፡ ሥላሴ፡ ካቴድራል፡ አጠገብ ከ.ቀ. 11-66-16

ፓ.ሣ.ቁ.3137 አ.አ.

## ማሳሰቢያ

በሚያዝያ ወር 1972 ዓ.ም. በወጣው ቁጥር 31 ትንሣኤ መጽሔት "በጌታ መግነዝ ላይ የተደረገው ሳይንሳዊ ምርመራ የብዙ ሳይንቲስቶችን ጥርጣሬ አስ ወገደ" በሚል ርዕስ ስለጌታ መግነዝ ማውጣታችን ይታወሳል ።

ይሁን እንጂ መጽሔቱ ለሁሉም ሳይዳረስ በመቅረቱና የጠያቂዎችም ቁጥር እየበረከተ ስለሄደ በሐምሌ ወር 1972 ዓ.ም በሚወጣው ቁጥር 34 ትንሣኤ መጽሔት ታሪኩ ደግሞ የሚወጣ መሆኑን ለመጽሔታችን ተከታታዮች በደስታ እንገልጻለን ፤

የመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል ።



# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች ውድድር

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች ውድድር

የተወደዳችሁ የትንሣኤ መጽሔት ደንበኞችና የዚህ ዓምድ ተከታታዮች ፡ ከዚህ ቀጥሎ ያቀረብንላችሁ መለስተኛ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች ውድድር ነው ። ጥያቄዎቹን በትክክል ሠርተው ከ1-3ኛ ለሚወጡ አሸናፊዎች የሚከተሉት ሽልማቶች ተዘጋጅተውላቸዋል ።

1 ለመጀመሪያ ጊዜ በአማርኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ በቅርቡ የወጣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ፤
2 መጽሐፍ ቅዱስ (የአማርኛ ወይም የእንግሊዘኛ)
3 አዲስ ኪዳን (የአማርኛ ወይም የእንግሊዘኛ)

የጥያቄዎቹ መልሶች በአዲስ አበባና አካባቢ ነዋሪ ከሆናችሁ መጽሔቱ በወጣ እስከ 10 ቀን (ራቅ ባለ አካባቢ የምትኖሩ ከሆነ መጽሔቱ በወጣ በ15 ቀን መድረስ አለባቸው ።

ጥያቄዎች እነሆ፡-

1. ዮሴፍ በሕልሙ ሲሰግዱለት የተመለከተው ምን ምን ነገሮች ናቸው ?
2. ንጉሥ አርጤክስስ ታቅዶበት ከነበረ ሴራ ያዳነው ማን ነበረ ?
3. አራት ታላቅ አራዊት በሕልሙ የተመለከተ ነቢይ ማን ነበር ?
4. በምድረ እሥራኤል ዝናብ እንዳይጥል በጸሎት ያገደ ነቢይ ማን ነው ?
5. ያዕቆብ የእግዚአብሔርን ቃል በምን ይመስለዋል ?
6. በያዕቆብ መልእክት መሠረት ክርስቲያን መከራ በገጠመው ጊዜ እንዴት መቀበል አለበት ?
7. በያዕቆብ አገላለጽ ንጹህና ነውር የሌለበት አምልኮ ምንና ምንድነው ?
8. የጐደሉትን ቃላት ሙላ ፡
   ሀ. አጥብቀህ ________ ጠብቅ ፤ የ ________ መውጫ ከእርሱ ነውና ።
   ለ. ልብሱን እርስ በርሳቸው ________
   ሐ. ኑና ________ ይላል እግዚአብሔር ።
   መ. ልጆቼ ሆይ ፡ ________ እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ ።
   ሠ. አምላክ ሆይ ________ ማረኝ ።

ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልስ የሚገኝበትን መጽሐፍ፣ ምዕራፍና ቁጥር ስጥ ። እንዲሁም ተወዳዳሪዎች በሙሉ አድራሻችሁን በትክክል ጽፋችሁ መልሳችሁን ፡

ለኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር

የመ.ሣ.ቁጥር 1252 አዲስ አበባ ላኩ ።

www.ethiopianorthodox.org